

# የበረሃው ሰይፍ



## ሽብርተኝነትና አክራሪ እስልምና ምንጭና ዥረቱ

ኑረዲን ኢብን አል-መሲህ

# የበረሃው ሰደፍ

*ሽብርተኝነትና ሰክራሪ እስልምና ምንጭና ዥረቱ*

**አዘጋጅ፡ ኑረዲን ኢብን አል-መሲህ**

1ኛ **ዕትም - ጥቅምት** 2009

- ልዩ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመታት ሁሉ እንደ ጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቆጣጠር ናቸው፡፡
- ልዩ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በኢት. መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ከተዘጋጀው ነባር ትርጉም ነው፡፡
- የቅዱስ ቁርአን ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በሸኽ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅና በሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ተተርጉሞ በነጃሺ አሳታሚ ድርጅት ከታተመው የአማርኛ ትርጉም ነው፡፡

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

© 2016 Nuredin Ibn al-Masih

አስተያየቶቻችሁ በሚከተለው የኢ-ሜል አድረሻ ይደርሱናል፡-

christopherdgm@gmail.com

# ማውጫ

## መግቢያ

## ክፍል አንድ

## መሐመድ የእስልምና ጀማሪ


1 የመሐመድ ታሪክ ምንጮች ............................................. 1

- የመሐመድን ታሪክ ማወቅ ለምን አስፈለገ?
- አበይት ድርሳናት

2 የመሐመድ ግለ ታሪክ ............................................. 7

- የልጅነት ሕይወት
- ጋብቻ ከከዲጃ ጋር
- የመጀመርያው መገለጥ
- የሶሃቦች ስደት ወደ ምድረ ሐበሻ
- ሰይጣናዊ ጥቅሶች
- ስደት ወደ ያሥሪብ
- ሰይፍ የታጠቀው ነቢይ

3 የመሐመድ ውርሶች ............................................. 21

- ቁርአን
- ሱና


## ክፍል ሁለት

## ጥንታዊው ጂሃድና የዘመኑ የሽብር ስጋት


1 የጂሃድ ምንነትና ታሪክ ............................................. 30

- ጂሃድ በኸሊፋዎች ዘመን
- ኸል-ኸዋሪጅ - የመጀመርያው እስላማዊ የሽብር አንጃ
- በክርስቲያኖችና በአይሁድ ላይ የተመዘዘ ሰይፈ ጂሃድ
  - መሐመድ በአይሁድ ላይ የፈፀሙት ግፍ
  - የዚማ ቃል ኪዳን
  - የጂዝያ አከፋፈል ሥርዓት
  - የዚሚ ግዴታዎች
- ጥንታዊ የክርስቲያን ማዕከላትን መውረር
- የመስቀል ጦርነቶች (ክሩሴዶች)
- የከሸፉ ጂሃዶች
  - የቱርስ (የፖይቲርስ) ጦርነት
  - የቪዬና ከበባ

**2 ጂሃድ በአዲስ መልክ ..................................................62**

- የነፃነት መዘዝ
- ሽብርተኝነት - የጥንቱ ጂሃድ አዲስ ገፅታ
- ሊቃውንተ ሽብር
  - ኢብን ተይሚያ - የወሃቢዝም አያት
  - ኢብን አብደል ወሃብ - የወሃቢዝም አባት
  - ሰይድ ቁጥብ - የሽብርተኝነት መሐንዲስ
  - አብዱላህ አዛም - የዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት አባት
- 1979 - ዓለም አቀፋዊው ሽብርና ሦስቱ ክስተቶች
  - የኢራን አብዮት
  - የመካ ከበባ
  - የአፍጋኒስታን በሶቪዬት ሕብረት መወረር

**ክፍል ሦስት**

**ጂሃድና ኢትዮጵያ**

**1 ታሪክ እንደ ጂሃድ መሣርያ .........................................77**

- ከአል-ነጃሺ ታሪክ በስተጀርባ የሚገኝ ሤራ
- ውዳሴ አሕመድ ግራኝ

**2 ጂሃድ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ19ኛው ክ/ዘ ወዲህ ............... 94**

- የግብፅ ወረራዎች
- የሱዳን መሐዲዎች ጥቃት
- የልጅ ኢያሱ የማስለም ሤራ
- የፋሺስት ኢጣሊያ እስላማዊ ተልዕኮ
- የዚያድ ባሬና የሶማሊያ የሽብር ቡድኖች ሙከራ

**3 ወሃቢዝም በኢትዮጵያ ውስጥ...................................... 104**

- በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን
- በዘመነ ደርግ
- በዘመነ ኢህአዴግ

**የማጠቃለያ ሐሳቦች ....................................................110**

- መታወቅ ያለባቸው ወሳኝ እውነታዎች
- የአክራሪ እስልምናን አደጋዎች ለመቀልበስ የሚጠቅሙ ሐሳቦች
- ከክርስቲያኖች ምን ይጠበቃል?

**አባሪ 1፡ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ የደረሱ ጥቃቶች የቅርብ ዘመን ትዝታዎች ...................................................143**

**ዋቢ መጻሕፍት ........................................................146**

# መግቢያ

የልጅነት ዘመኔን ባሳለፍኩባት የገጠር ከተማ በአነስተኛ ዲናሞዎች የሚሠሩ ያልጠሩ ምስሎችን የሚያሳዩ ሁለት ቴሌቪዥኖች ነበሩ፡፡ ከሁለቱ አንዱ የእህቴ በመሆኑ እንደ ሌሎቹ የዕድሜ አቻዎቼ አምሳ ሣንቲም ለመክፈል አልገደድም ነበር፡፡ መስከረም 1 - 1994 ዓ.ም. (በኛ አቆጣጠር) የአዲሱን ዓመት ልዩ የበአል ዝግጅት ለመከታተል ቦታ ይዣለሁ፡፡ የአውዳመት ሙዚቃዎች፣ በአደይ አበባ ምስሎች የታጀቡት ማስታወቂያዎችና በአገር ባሕል አልባሳት ያጌጡት ጋዜጠኞች ቀልቤን ገዝተውታል፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚያውቀው የእንቁጣጣሽ ምትሃታዊ ስሜት ተመስጬ የቴሌቪዥኑን መስኮት አልፌ በመግባት የትርዒቱ አካል ሆኛለሁ፡፡ ነገር ግን ሲተላለፍ የነበረው ፕሮግራም ድንገት ተቋርጦ አንድ ሰበር ዜና መተላለፍ ሲጀምር በአደይ አበባ ከተሞላው መስክ ወጥቼ በጭስ በታፈነ የሕንፃዎች ፍርስራሽ ውስጥ ራሴን አገኘሁት፡፡

ጋዜጠኛው አለመረጋጋት በሚስተዋልበት ድምፅ "በኒውዮርክ በሚገኙት የዓለም የንግድ ማዕከል መንትያ ሕንፃዎች ላይ ጥቃት ተፈፀመ..." ይላል፡፡ አንድ ጢያራ እንደ ሚሳኤል እየተምዘገዘገ ከሁለቱ ውብ ሕንፃዎች በአንዱ አናት ላይ ሲቸከልና በጥቁር ጭስ የታጀበ ነበልባል ከሕንፃው ሲጉተለተል ታየ፡፡ ሁለተኛውም ተከትሎት በሌላኛው ሕንፃ ወገብ ላይ ተሰካ፡፡ እኒያ ውብና ግዙፍ ሕንፃዎች በውስጣቸው የነበሩትን ሕያዋን እንደያዙ ወደ ፍርስራሽነት ሲቀየሩ በድንጋጤና

በሰቀቀን ሆኜ ተመለከትኩ፡፡ ድርጊቱ የአሸባሪዎች ጥቃት ስለመሆኑ ግምት መኖሩን በመጠቆም ልብ ሰባሪው ሰበር ዜና አበቃ፡፡ ያ ሁሉ የአርማታ መርግ እላዩ ላይ የወደቀ ያህል ተሰምቶኝ መላው ሰውነቴ በድንጋጤና በኀዘን እየራደ ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ፡፡ የዚያ አረመኔያዊ ተግባር ሰለባ የሆኑትን ወገኖች ሰቆቃ በማሰብ እያነባሁ ወደ ወላጆቼ ቤት አቀናሁ፡፡

ስለ ጉዳዩ የማወቅ ጉጉት ስላደረብኝ በቀጣዮቹ ቀናት በእጄ መዳፍ ተለክታ የተሠራች በምትመስለው ራዲዮኔ ላይ ጆሮዬን በመትከል መከታተል ተያያዝኩኝ፡፡ ከአሥራ ዘጠኙ አሸባሪዎች መካከል አሥራ አምስቱ የሳዑዲ አረብያ ዜጎች መሆናቸውና ጥቃቱ በአልቃኢዳ መቀናበሩ ይፋ ሆነ፡፡

አሸባሪዎቹ ረጅም ጊዜ ከፈጀ ዝግጅት በኋላ ነበር አራት አውሮፕላኖችን በመጥለፍ ሁለቱን በኒውዮርክ ከሚገኙት የዓለም የንግድ ማዕከል መንትያ ሕንፃዎች ጋር ያላተሙት፡፡ በዚህ ጥቃት የአሜሪካ ኩራት የነበሩት መንትያ ሕንፃዎችና በዙርያቸው የነበሩት ሌሎች ሕንፃዎችም ተደርምሰዋል፡፡ ሦስተኛውን ወደ ዋሺንግተን በመውሰድ ከፔንታገን (የአሜሪካ የመከላከያ ዲፓርትመንት ዋና ማዕከል) ጋር በማላተም ሕንፃውን በከፊል ያፈረሱ ሲሆን ሌላኛውን ደግሞ ምናልባትም ከነጩ ቤተ መንግሥት ጋር ለማላተም እየበረሩ ሳሉ ከተሳፋሪዎች ጋር በተፈጠረ ግብግብ አውሮፕላኑ ባዶ ሜዳ ላይ ተከስክሶ በውስጡ የነበሩት ሰዎች ሁሉ አልቀዋል፡፡ በዚህ ጥቃት ወደ 3,000 የሚጠጉ ሰዎች ሕይወት ተቀጥፏል፤ ከ6,000 በላይ ቆስለዋል፡፡ አሥር ቢሊየን ዶላር የሚያወጣ ንብረት ከመቅፅበት የወደመ ሲሆን ጠቅላላ ኪሳራው ሦስት ትሪሊየን ዶላር ተገምቷል፡፡

ያኔ ገና በዕድሜ ለጋ ብሆንም የክስተቱ ትርጉም በመጠኑም ቢሆን ገብቶኝ ነበር፡፡ ነገር ግን አሸባሪዎቹ የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደሆኑ መነገሩ የሚዋጥልኝ አልሆነም፡፡ ምክንያቱም እኔ የማውቃቸው ሙስሊም ባልንጀሮቼ ሰላማውያን፣ ታማኞችና ደጎች ናቸውና፡፡ በአንድ ወቅት ወላጅ እናቴ ያለፍትህ ታስራ ከባድ ቅጣት ስትጠባበቅ ሳለች አንድ ሙስሊም ተፋልሞ ታድጓታል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ይኸው ሰው ከሞት አትርፏታል፡፡ እኔ የማውቃቸው ሙስሊሞች እንዲህ ናቸው፡፡ ፈጣሪያቸውን የሚፈሩ፣ የተቸገረን የሚረዱ፣ አድሎን የማያውቁ፣ ከብዙ ሰዎች የተሻለ መልካምነት የሚንፀባረቅባቸው ግሩም ማሕበረሰቦች! የአሸባሪዎቹ ድርጊት ከዚህ ጋር አልታረቅልህ አለኝ፡፡

የዓለምን ሰላምና ኢኮኖሚ ያሰባቀለው የመስከረም አንዱ ጥቃት ከተፈፀመ ዓመታት አለፉ፡፡ አሜሪካና አጋሮቿ በሽብርተኝነት ላይ ጦርነት ማወጃቸውን አስታውቀው አፍጋኒስታንና ኢራቅን በመውረር “ድላቸውን” አብሥረዋል፡፡ በአሸባሪነት የተፈረጁ ቡድኖችና ግለሰቦችም በየቦታው መታደናቸውን ቀጥለዋል፡፡ ዓለም ከዚያ ወዲህ እንደ ቀድሞ አልሆነችም፡፡ የኔም ዕድሜ ከፍ ብሎ የሰው ልጆች የሚፈፅሟቸውን ክፋቶች ትርጉም ለመገንዘብ የሚያስችል የአእምሮ ብስለት አዳብሬያለሁ፡፡ የመሰናዶ ትምህርቴን አጠናቅቄ የመግቢያ ፈተናውን በስኬት በማለፍ የአንደኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆኛለሁ፡፡

1999 ዓ.ም. ዓመቱን ሙሉ ከቤተሰቦቼና ከጓደኞቼ ተነጥዬ ከቆየሁ በኋላ ናፍቆትና የአዲሱ ሕይወት ዘይቤ ትግል የተፈራረቁበትን አካሌን ለማሳረፍ በሚሊኒየሙ ዋዜማ ወደ ቤት ተመልሻለሁ፡፡ እጅግ ጣፋጭ ስሜት ነበር፡፡ ነገር ግን ደስታውን ማጣጣም የቻልኩት የቅርብ ጓደኛዬ አንድ የቪድዮ ሲዲ ይዞልኝ እስከመጣበት

ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር፡፡ ቪድዮው መስከረም 16 - 1999 ዓ.ም. በጅማ ዞን በሻሻ በተባለ ቦታ አክራሪ ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ የፈፀሙትን ዘግናኝ ጭፍጨፋ የሚያሳይ ነበር፡፡ አካላቸው የተቆራረጠ፣ በእሳት የተለበለቡ፣ ተሰይፈው በየቦታው የወዳደቁ… አስከሬኖች ይታያሉ፡፡ በስፍራው የነበሩና በሕይወት የተረፉ ሰዎች ስለደረሰባቸውና ስለተመለከቱት አስፈሪ ሁኔታ ሳግ በተናነቀው ድምፅ እማኝነታቸውን ሲሰጡ ይደመጣሉ፡፡ ስለ ጉዳዩ ቀደም ሲል የሰማሁ ብሆንም ሰቆቃውን በዓይኔ በማየቴ የተሰማኝን ኀዘንና ድንጋጤ ቃላት አይገልፁትም፡፡ ኋላ ላይ ያገኘኋቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በወቅቱ 18 ክርስቲያኖች ተገድለዋል፣ 38 ቆስለዋል፣ 488 በግድ ሰልመዋል፣ ከ2000 በላይ ተፈናቅለዋል፣ 3 አብያተ ክርስቲያናትና ከ850 በላይ የክርስቲያን ቤቶች ተቃጥለዋል፣ 4 አብያተ ክርስቲያናት ተዘርፈዋል፡፡[1] ያቺ ዕለት እስልምናና ሽብርተኝነት ያላቸውን ቁርኝት ለማወቅ ጥናት ማድረግ እንዳለብኝ የወሰንኩባት ዕለት ሆነች፡፡

ውድ ወዳጆቼ፣ ይህ መጽሐፍ የገዛ ጥያቄዎቼን ለመመለስ ላለፉት ጥቂት ዓመታት የሠራሁት ጥናት ውጤት ነው፡፡ ጥራዙን ለንባብ ለማብቃት ስወስን ሁለት ነገሮች በብርቱ ሞግተውኝ ነበር፡፡ የመጀመርያው አሳሳቢ የሆነብኝ ነገር ዛሬ በማሕበረሰባችን ውስጥ የተንሰራፋው የፖለቲካዊ ትክክለኝነት (Political Correctness) አስተሳሰብ ነው፡፡ ብዙ የተማሩ ሰዎች እውነትን ከመናገር ይልቅ የሽንገላ ቃላትን በመናገር በማሕበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን ችግሮች መቅረፍ እንደሚችሉ ያስባሉ፡፡ የመገናኛ አውታሮቻችንን የተቆጣጠሩት ወገኖች ልባቸውና ቃላቸውን ያስማሙ አይመስሉም፡፡ በተለይም የሽብርተኝነትና የአክራሪ እስልምና

[1] አባ ሳሙኤል፡፡ *በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን፣* 2000፣ ገፅ 28-31
ኤፍሬም እሸቴ ፡፡ *አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ፣* 2000፣ ገፅ 172-175 ነው፡፡

ጉዳይ ሲነሳ በፍርሃት የሚርዱና የችግሩን ምንጭ ከመጥቀስ ይልቅ ዙርያ ጥምጥም የሚሄዱ ወገኖች ይበዛሉ፡፡ የችግሩ ምንጮች ሙስሊም ወገኖቻችን እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አክብረው የያዟቸው ጽሑፎች መሆናቸውንና ሽብርተኝነት ከአክራሪ እስልምና ታሪክ ጋር የተጋመደ መሆኑን በገሃድ መናገር በብዙ ችግሮች የተውተበተበውን ማሕበረሰባችንን ከመጥቀም ይልቅ ለጉዳት እንደሚዳርግ የሚያስቡ ወገኖች ብዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ዘላቂ መፍትሄ ይቅርና ጊዜያዊ መፍትሄ እንኳ ሲያመጣ አልታየም፡፡ በዝምታው ዳፋ ብዙ ዜጎቻችንን ለሽብር ገብረናል፡፡ “ጅቡ እግሬን እየበላው ነውና እንዳይሰማን ዝም በል” እንዳለው የዋህ መሆን እንደማያዋጣ ተገንዝበን የፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ሰካላ በመበጠስ እውነት እውነቱን ለመነጋገር ጊዜው እንደሆነ አምናለሁ፡፡

እኔ ለአገር ለወገኑ አሳቢ እንደሆነ ግለሰው፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የእውነትን የከበረ ዋጋ እንደተገነዘበ ክርስቲያን እውነትን መናገር እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡ አዎን እውነት አንዳንዴ መራራ ናት፤ ነገር ግን ታላቁ መምህር ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ነፃነትን ታቀዳጃለች (ዮሐንስ 8፡ 32)፡፡ አገርጋሪ ሆኖ ዝንተ ዓለም በሽብር እየተናጡ ከመኖር እውነትን ተናግሮ ዘላቂ መፍትሄ መፈለግ ይበጃል በሚል ምክንዮ ይህንን ሙግት በመርታት በአቋሜ ፀንቻለሁ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ሃቅን ላለማመቻመች ጥረት በማደርግበት ወቅት ሰላማውያን የሆኑትን የብዙኀኑን ሙስሊም ወገኖቼን ስሜት እጎዳ ይሆን? የሚል ጥያቄ ነበር፡፡ ለዚህም እውነትን ይዣለሁ በሚል ቅይድ ዕይታ በመነዳት የሙስሊም ወዳጆቼን ስሜት ላለመጉዳት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ አቀራረቤን ከዘለፋ አርቄ ለውይይት

የሚጋብዝ ለማድረግ እንጥፍጣፊ አቅሜን ተጠቅሜያለሁ፡፡ በሙስሊሙ ማሕበረሰብ ዘንድ ከበሬታ የተቸራቸውን ስብዕናዎች ስጠቅስ ተገቢውን አክብሮት ሳላጓድል ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ላነሳኋቸው አንኳር ነጥቦች ምሑራዊ ደንቦችን በጠበቀ መልኩ ምንጮችን በመጥቀስ ለአንባቢያን ያለኝን አክብሮት እንዳሳየሁ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ አንብቦ ከሰላማዊ ውይይት ይልቅ ለቁጣ የሚጋበዝ አስተዋይ ሙስሊም ይኖራል የሚል ግምት የለኝም፡፡ ምናልባት ይህንን መጽሐፍ ካነበበ በኋላ ትዕግስቱ የሚፈተን ሙስሊም ካለ ክርስትናን በተመለከተ የተጻፉ ጉልቁ መሣፍርት የሌላቸው እስላማዊ መጻሕፍት መኖራቸውን ያስታውስ፤ ስለ ሌላው እምነት የመናገር መብት ያላቸው ሙስሊም ወገኖች ብቻ አለመሆናቸውን ይወቅ የሚል ምላሽ እሰጣለሁ፡፡ ይህንን ስል ግን የዚህ ጥራዝ ዓላማ ክርስትናን በማብጠልጠል ለተጻፉት እስላማዊ መጻሕፍት አፀፋዊ ምላሽ መስጠት ነው እያልኩ አይደለም፡፡ ብዙ ሙስሊም ጸሐፊያን በጭፍን ጥላቻ ተነሳስተው በክርስትና ላይ ሲፈፅሙት በሚስተዋለው መንገድ የማንንም እምነት የመንቀፍና የማብጠልጠል ዓላማ እንደሌለው አንባቢያን ይገነዘቡታል ብዬ አምናለሁ፡፡

የክርስቶስን ፈለግ ለመከተል እንደሚተጋ ክርስቲያን ለሙስሊም ባለንጀሮቼ ጥልቅ ፍቅርና አክብሮት አለኝ፡፡ ይህ እንኳ ባይሆን አብሯቸው ኖሮ፣ በነርሱ እንክብካቤ አድጎ ደግነታቸውን በተግባር እንደተመለከተ ሰው እነርሱን ለመውደድና ለማክበር በቂ ምክንያቶች አሉኝ፡፡ ታሪክንና እስላማዊ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ የችግሩን መነሻ ምንጭ ለማግኘት ጥረት አድርጌ ለሁሉም የሚበጀውን የሰላም፣ የፍቅርና የመከባበር ጎዳና በመጠቆም ሕዝበ ክርስቲያኑን ብቻ ሳይሆን ከማንም ይልቅ የአክራሪ እስልምና ሰለባ የሆኑትን ሙስሊም ወገኖቼንም ጭምር የሚጠቅም

ሰናይ ምግባር እንደፈፀምኩ ይሰማኛል፡፡ ግና እርማትና ማሻሻያ የማያሻውን ፍፁም እንከን የለሽ *ሥራ* እንደሠራሁ በመቁጠር አልገደርም፡፡ በመሆኑም መልካም ጎኑን በማበረታታትና ለቀጣይ ዕትም ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ሕጸጻት በመጠቆም አስተያየቶቻችሁን እንደምታደርሱኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ኑረዲን ኢብን አል-መሲህ

# ክፍል 1

## መሐመድ የእስልምና ጀማሪ

❶

# የመሐመድ ታሪክ ምንጮች

ሙስሊሞች ለነቢዩ መሐመድ ጥልቅ ፍቅርና አክብሮት አላቸው፡፡ ነቢዩን የሚተች ማንኛውንም ነገር ሲሰሙ “የአላህ ነቢይ ሆይ አባቴም እናቴም ፊዳዕ (መስዋዕት) ይሁኑልዎት” በማለት ፍቅራቸውንና አክብሮታቸውን እንዲሁም የነቢዩን ስብዕና ከጥቃት ለመከላከል ያላቸውን ቁርጠኝነት ይገልፃሉ፡፡ መሐመድ በእስልምና ውስጥ ያላቸው ቦታ ምን ያህል የላቀ እንደሆነ ለመረዳት የመካከለኛው ዘመን ሱኒ ሊቅ የነበረው ኢብን ተይሚያ የጻፈውን እንደ ምሳሌ መጥቀስ በቂ ነው፡-

> “የአላህ መብቶችና የመልእክተኛው መብቶች እኩል ናቸው፡፡ አላህንና መሐመድን የምንታዘዛቸው በአንድ መንገድ ነው፡፡ መልእክተኛውን የሚሳደብ ሰው አላህን ይሳደባል፣ መልእክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ደግሞ አላህን ታዞታል፣ ምክንያቱም የእስላማዊ ኡማ አባላት በመልእክተኛው በኩል ካልሆነ በስተቀር ከፈጣሪያቸው ጋር ምንም ግንኙነት ሊኖራቸው አይችልምና፡፡ በመልእክተኛው በኩል ካልሆነ በስተቀር ማንም ወደ አላህ የመቅረቢያ መንገድ የለውም፡፡ አላህ ማንኛውንም ነገር ለማዘዝ፣ ለመከልከልም ሆነ ለማብራራት በሁሉም ረገድ [መሐመድን] በራሱ ምትክ አስቀምጧቸዋል፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ ጉዳዮች በማናቸውም በአላህና በመልእክተኛው መካከል መለየት የተፈቀደ አይደለም፡፡” [2]

---

[2] ሳም ሰለሞንና ኢ. አልመቅዲሲ፡፡ *አል-ሂጅራ፣ እስላማዊ የስደት አስተምህሮ፤ ነፃነትን መቀበል ወይንስ እስልምናን በኃይል መጫን?* ፤ 2008፣ ገፅ 6

# የመሐመድን ግለ ታሪክ ማወቅ ለምን አስፈለገ?

መሐመድ የዛሬ 1400 ዓመታት ገደማ የኖሩ ሰው ቢሆኑም ውርሶቻቸው በዙርያችን በሚገኙት ማሕበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የጎላ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ የቴሌቪዥኖቻችንን መስኮቶች በከፈትን ቁጥር የትምህርቶቻቸው ውጤቶች የሆኑ ዘገባዎችን አዘውትረን መመልከታችን ስለ መሐመድ ማወቅ ምርጫችን ከመሆን አልፎ ግዴታችን እየሆነ የመጣበት ዘመን ላይ መድረሳችንን ያመለክታል፡፡ ብዙ ጎረቤቶቻችንም በሁሉም ረገድ እርሳቸውን ለመምሰል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በአንድ ሙስሊም ጸሐፊ አባባል "መሐመድ በሕይወት የሉም፡፡ ነገር ግን መሞታቸው ያስከተለው ውጤት ኢምንት ነው፡፡ ምክንያቱም ባስተላለፏቸው እሳቤዎች በኩል ህልውናቸው ቀጥሏልና፡፡"[3]


ብዙዎቻችን ስለመሐመድ ግለታሪክ ያለን መረጃ በቂ ካለመሆኑ የተነሳ ስለ እስልምና ያለን መረዳት ውሱን ሆኗል፡፡ የእምነቱ ድርና ማግ የመሐመድ ማንነት፣ ታሪክና ትምህርት በመሆኑ እስልምናን ከመሐመድ ነጥሎ መረዳት የማይታሰብ ነው፡፡ ቁርአንን እንኳ ለመረዳት የርሳቸውን ታሪክ ማወቅ ግድ ነው፡፡ ምክንያቱም የቁርአን አውድ የመሐመድ ታሪክ ነውና፡፡ የነቢዩ መሐመድ ስብዕናና ታሪክ ከእስልምና ቢፋታ ሃይማኖቱ ብቻ ሳይሆን የሙስሊም ማሕበረሰብ መለያና መታወቅያ የሆነ ማንኛውም ነገር ሕልውናው ሊቀጥል አይችልም፡፡ ስለ እስልምና ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረንና የሙስሊም ማሕበረሰቦችን እንቅስቃሴ መረዳት ከተፈለገ የእምነቱን ጀማሪ ማንነትና ታሪክ ማጥናት በእጅጉ አስፈላጊና መተኪያ የሌለው አማራጭ ነው፡፡

---

[3] Shabbir Akhtar. *Be Careful With Muhammad;* 1992, p. 28

# አበይት ድርሳናት

የእስልምና ጀማሪ ስለሆኑት ስለ መሐመድ ለማወቅ መዛግብትን ማገላበጥ ከመጀመራችን በፊት ከግንዛቤ ውስጥ ሊገባ የሚገባው እውነታ ቢኖር ስለ እርሳቸው የምናውቀው አብዛኛው ነገር የተጻፈው ከህልፈታቸው በኋላ ከ150-300 ዓመታት ያህል በመዘግየት መሆኑ ነው:: በእስልምና የመጀመርያዎቹ ዘመናት አረቦች በዙርያቸው የሚገኙትን ሕዝቦች በመውረር ተጠምደው ስለነበር እስላማዊ ታሪኮችንና ትምህርቶችን በጽሑፍ ለማስፈር ጊዜ የነበራቸው አይመስልም:: በነዚያ ዘመናት በጽሑፍ እንደሰፈሩ የሚነገርላቸው እስላማዊ ድርሳናት ቢጠቀሱም መኖራቸውን የተረዳነው ብዙ ዓመታትን በመዘግየት ከተጻፉት አሁን በእጃችን ከሚገኙት ጽሑፎች ነው:: በእስልምና የመጀመርያው ክፍለ ዘመን እንደተጻፈ ለመናገር የሚያስደፍር እስላማዊ መጽሐፍ ቁርአን ሲሆን (ይህንን የሚጠራጠሩ ጥቂት የማይባሉ ሊቃውንት አሉ) የመሐመድ ስም በውስጡ ተጠቅሶ የምናገኘው አራት ጊዜ ብቻ ነው:: ቁርአንን በማንበብ ስለ መሐመድ የተወሰኑ ነገሮችን ማወቅ ብንችልም ሙሉ የሆነውን ምስላቸውን አናገኝም:: ሙሉ የሆነውን ምስላቸውን ለማግኘት ሌሎች ምንጮች የግድ ያስፈልጉናል::



የኢብን ኢስሐቅ መጽሐፍ አልፍረድ ጉላም በተሰኙ ምሑር ወደ እንግሊዘኛ ተመልሷል::

የመሐመድ ቀዳሚው ግለ ታሪክ ኢብን ኢስሐቅ በተባሉ የኢራቅ ሰው "ሲራት ረሱል- አላህ" (የአላህ መልእክተኛ ግለ-ታሪክ) በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ነው:: ይህ ግለ ታሪክ በ765 ዓ.ም. እንደተጻፈ የሚነገር ሲሆን በሁለት የእርማት ሥራዎች

ውስጥ አልፏል፡፡ የመጀመርያውን እርማት ያደረጉት አል-ባካኢ የተሰኙ ደቀ መዝሙራቸው ነበሩ፡፡ በማስከተል ደግሞ ኢብን ሒሻም የተሰኙ ሰው በ833 ዓ.ም. በማረም አሁን ያለውን መልክ ሰጥተውታል፡፡ ጉዳዩን ያጠኑ ሊቃውንት የኢብን ኢስሐቅ ሥራ ከሞላ ጎደል በኢብን ሒሻምና በአል-ጦበሪ ጽሑፎች ውስጥ እንደሚገኝ የሚናገሩ ሲሆን ነገር ግን ዋናው ጽሑፍ ጠፍቷል፡፡ ይህንን ግለ ታሪክ በማረም አሁን ያለውን መልክ ያስያዙት ኢብን ሒሻም በመቅድሙ ላይ የመሐመድን ታሪክ ሆነ ብለው መቀየራቸውን እንደሚከተለው ይናዘዛሉ፡- "ለመነጋገር አሳፋሪ የሆኑ ነገሮች፣ አንዳንድ ሰዎችን ሊያስጨንቁ የሚችሉ ጉዳዮችና በአል-ባካኢ [የኢብን ሒሻም መምህር] ተዓማኒ ተደርገው እንደማይቆጠሩ የተነገሩኝ ጉዳዮች እንዲወገዱ አድርጌያለሁ፡፡"[4]

ከኢብን ኢስሐቅ በተጨማሪ በአል ወቂዲና በጸሐፊያቸው በኢብን ሰዓድ የተዘጋጁ ሌሎች ሁለት ሲራዎችም ስለ መሐመድ ግለ ታሪክ መረጃዎችን በመስጠት ረገድ ጠቃሚ ምንጮች ናቸው፡፡[5]

ስለ እስልምናው ነቢይ የሚናገሩት ሌሎች ጥንታዊ ምንጮች ሐዲሳት በመባል የሚታወቁት መጻሕፍት ናቸው፡፡ ሐዲሳት (ትውፊቶች) የመሐመድ ንግግሮችና ድርጊቶች ስብስቦች ናቸው፡፡ ሙስሊሞች ከሕንድ ክፍለ አህጉር እስከ እስፔን የሚገኙትን ሰፊ ግዛቶች ከተቆጣጠሩ በኋላ ቁርአንን ብቻ በማንበብ ግልፅ የማይሆኑ ብዙ ሃይማኖታዊና ማሕበራዊ ጉዳዮችን አስተዋሉ፡፡ ቁርአንም ቢሆን የንባብ አውዱ ጠባብ በመሆኑ ትክክለኛ መልእክቱን ማግኘት አዳጋች ሆነ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ነቢዩ ያደረጓቸውንና የተናገሯቸውን ነገሮች እንዲሁም የቁርአን አናቅፅ በየትኞቹ የነቢዩ የታሪክ አውድ "እንደወረዱ"

---

[4] Alfred Guillaume. *The Life of Muhammad, A Translation of Ibn Ishaq's Sirat Rasul Allah;* 1955, p. 691
[5] Bennet Clinton. *In Search of Muhammad;* 1998, pp. 28-30

ለመረዳት ከሁለት ክፍለ ዘመናት በላይ ወደ ኋላ በመመለስ ማጥናት ግድ ሆነ፡፡ ስለዚህ ከአረብያ ውጪ የሆኑና አዳዲስ ከሰለሙት አካባቢዎች የተውጣጡ ሙስሊም ሊቃውንት ተበታትነው የሚገኙትን በአፈ ታሪክ የሚነገሩትን የመሐመድን ድርጊቶችና ንግግሮ ማሰባሰብ ተያያዙ፡፡ ቡኻራ ከተሰኘችው የኡዝቤኪስታን ከተማ የመጡት ኢማም አል-ቡኻሪ ዋነኛ የሐዲስ ሰብሳቢ ነበሩ፤ 600,000 ሐዲሳትን ሰብስበው የነበረ ሲሆን ከነዚህ መካከል ተአማኒ ናቸው ያሏቸውን 7,275 የሚሆኑትን ብቻ በመምረጥ የተቀሩትን አስወግደዋል፡፡

ሐዲሳት ቁርጥራጭ ታሪኮችና ንግግሮች ሲሆኑ ከጥቂት አረፍተ ነገሮች እስከ ተወሰኑ ገፆች የሚረዝሙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ታሪኮችና ንግግሮች ትልልቅ መጠን ባላቸው ጥራዞች በቅፅ ተከፋፍለው ታትመው እናገኛቸዋለን፡፡ በሱኒ ሙስሊሞች ዘንድ የቀኖናዊነት ደረጃ የተሰጣቸው አበይት ስብስቦች ስድስት ናቸው፡፡[6] በአረብኛ *ሳሂህ ሲታ* በመባል የሚታወቁት እነዚህ ስብስቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ሳሂህ አል-ቡኻሪ (870 ዓ.ም.፣ 256 ዓ.ስ.)[7] - በኢማም መሐመድ ቢን ኢስማዒል አል-ቡኻሪ የተሰበሰበ ሲሆን 7,275 ሐዲሳት ተካተውበታል፡፡
- ሳሂህ ሙስሊም (875 ዓ.ም.፣ 261 ዓ.ስ.) - ሙስሊም ቢን ሐጃጅ አል-ነይሻቡሪ በተሰኙ ሰው የተሰበሰበ ሲሆን 9,200 ሐዲሳትን ይዟል፡፡
- ሱናን አቡ ዳውድ (888 ዓ.ም.፣ 275 ዓ.ስ.) - በአቡ ዳውድ ሸዓሥ አል-ሲጂስታኒ የተሰበሰበ ሲሆን 4,800 ሐዲሳትን አካቷል፡፡
- ጃሚ አት-ቲርሚዚ (892 ዓ.ም.፣ 279 ዓ.ስ.) - በመሐመድ ቢን ዒሳ አል-ቲርሚዚ የተሰበሰበ ነው፡፡

---

[6] Ibid., p. 31-32

[7] ዓ.ስ. - ዓመተ ስደት ሲሆን በአረብኛ ሒጅራ የሚለውን ይወክላል፡፡ የተወሰደውም ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት በ2004 ካዘጋጀው ቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም መቅድም ላይ ነው (ገፅ 11 ይመልከቱ)፡፡

- ሱናን አን-ነሳዒ (915 ዓ.ም.፣ 303 ዓ.ስ.) – በአቡ አብዱልረህማን አን-ነሳዒ የተሰበሰበ ነው፡፡
- ሱናን ኢብን ማጃህ (887 ዓ.ም.፣ 273 ዓ.ስ.) - ኢብን ማጃህ አል-ቀዝዊኒ በተባሉ ሰው የተሰበሰበ ነው፡፡

አንድ ሐዲስ ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ የመጀመርያው *ኢሰናድ* (የዘገባ ሰንሰለት) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ *መትን* (ሐተታ) ነው፡፡ ኢስናድ ወይም የዘገባ ሰንሰለት ሐዲሱን ያስተላለፉ ሰዎች ስም ዝርዝር ነው፡፡ መትን ደግሞ ዋናው የዘገባ ምንባብ ነው፡፡ ሙስሊም ሊቃውንት ሐዲሳትን ሳሂህ (አስተማማኝ)፣ ሐሰን (ጥሩ)፣ ደዒፍ (ደካማ) እና መውዱዕ (የማይታመን) በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ ደረጃ ለማውጣት ጥቅም ላይ በሚውሉት መስፈርቶች ላይ ወጥ የሆነ አቋም የለም፡፡ ሐዲሳትን በዚህ መልኩ መከፋፈል ብዙ ሙስሊሞች ስለ መሐመድ የተነገሩትን መልካም ነገሮች እየመረጡ እንዲቀበሉና ያልተስማማቸውን ደግሞ እንዲጥሉ ክፍተት ፈጥሮላቸዋል፡፡

2

# የመሐመድ ግለ ታሪክ

የመሐመድን ሕይወት በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመርያው ከልደታቸው አንስቶ የመጀመርያውን "መገለጥ" እስከተቀበሉበት ጊዜ ድረስ የሚገኘው ነው፡፡ በእስላማዊ ምንጮች መሠረት መሐመድ የተወለዱት በአረቦች ታሪክ "የዝሆን ዓመት" በመባል በሚታወቀው 570 ዓ.ም. ነበር፡፡ ይህ ዓመት "የዝሆን ዓመት" የሚል ስያሜ ያገኘበት ምክንያት በወቅቱ የመንን ይገዛ የነበረ አብረሃ[8] የተሰኘ ክርስቲያን መሪ ቢያንስ በአንድ ዝሆን የታገዘ ሠራዊት በመምራት መካ ላይ በመዝመቱ ነበር፡፡ አብረሃ ካዕባን ለማፍረስ ያደረገው ጥረት ሳይሳካለት ተመልሷል፡፡ ሁለተኛው የታሪክ ክፍል የመጀመርያውን "መገለጥ" ከተቀበሉበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሒጅራ ወይም ወደ መዲና እስከተሰደዱበት ጊዜ ድረስ የሚገኘው ነው፡፡ በሒራ ዋሻ ውስጥ የመጀመርያውን "መገለጥ" እንደተቀበሉ የተናገሩት በ610 ዓ.ም. ሲሆን የእስልምና ጅማሬ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ሦስተኛው የሕይወታቸው ክፍል ደግሞ ከ622 ጀምሮ እስከ 632 ድረስ የሚገኘው ነው፤ ይህም ከሒጅራ አንስቶ እስከ ህልፈተ ሕይወታቸው ድረስ ያለውን ዘመን ይሸፍናል፡፡ የመጀመርያው የታሪክ ክፍል መሐመድ ብዙም የማይታወቁበት ነበር፡፡ ሁለተኛው "በነቢይነት" አገልግሎታቸው የታወቁበትና ተከታዮችንም ያፈሩበት

[8] የመን በወቅቱ የአክሱም ግዛት የነበረች ስትሆን አብረሃ የተባለው ወታደር የንጉሡን እንደራሴ በመግደል ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል በአክሱም ቁጥጥር ስር የነበረውን የየመን ግዛት ከሞላ ጎደል በራሱ ቁጥጥር ስር አድርጎ ነበር (The Cambridge History of Islam; 2008, p. 14)

ነበር፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ወታደራዊ ክንዳቸው ፈርጥሞ ከሞላ ጎደል መላውን አረብያ በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉበት ነበር፡፡[9]

ቀደም ሲል በተጠቀሱት እስላማዊ ምንጮች ውስጥ የሚገኙት ትርክቶች እርስ በርሳቸው የሚጣረሱና የትኛው ትክክል እንደሆነና እንዳልሆነ ለመለየት የሚያስቸግሩ እንዲሁም ተአማኒነት በጎደላቸው አፈ-ታሪኮች የታጀቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ፓትሪሺያ ክሮን የተሰኙ የታሪክ ሊቅ መሐመድ በልጅነታቸው ያነጋገሩትን አንድ ባህታዊ በተመለከተ ወደ 15 የሚሆኑ እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ዘገባዎችን ከእስላማዊ ምንጮች ውስጥ በማውጣት በመጽሐፋቸው ውስጥ አስፍረዋል፡፡[10] እነዚህ እስላማዊ ምንጮች በዘመን ከመሐመድ ጋር የማይገናኙና በዝርዝር ሁኔታዎች ላይ ብዙ መለያየቶችን የሚያሳዩ ቢሆኑም ስለ ሕይወታቸው የሚከተሉትን አጠቃላይ መረጃዎች ይሰጡናል፡፡

## የልጅነት ሕይወት

የመሐመድ የልጅነት ሕይወት በፈተና የተሞላ ነበር፡፡ ፈተናው የሚጀምረም ከመወለዳቸው በፊት ነው፡፡ አያታቸው አብዱል ሙጠሊብ (ሽይባህ ኢብን ሐሺም) አንድ ልጅ ብቻ ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ተጨማሪ ልጆችን መውለድ የሚችሉ ከሆነ ከመካከላቸው አንዱን መስዋዕት አድርገው እንደሚያቀርቡ ለሚያመልኩት ሁባል ለተባለ ጣዖት ቃል ገቡ፡፡ ስዕለቱም ስለሰመረላቸው የተናገሩትን ለመፈፀም በልጆቻቸው ላይ እጣ እንዲጣል አደረጉ፡፡ እጣውም በመሐመድ ወላጅ አባት በአብደላህ ላይ ወደቀ፡፡ ነገር ግን አብደላህ

[9] Bennet C. *In Search of Muhammad;* P. 17

[10] Patricia Crone. *Meccan Trade and the Rise of Islam;* 1987, P. 220

ለመስዋዕትነት ከመቅረባቸው በፊት ሰዎች ጣልቃ ስለገቡ በፋንታቸው መቶ ግመሎች ተሰውተው ከሞት ተረፉ፡፡[11]

መሐመድ በተፀነሱ በስድስተኛው ወር ነበር ወላጅ አባታቸው አብደላህ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት፡፡ እናታቸው አሚና ቢንት ወሒብ በወቅቱ በነበረው የአረቦች ልማድ መሠረት ህፃኑ መሐመድን ጡት እንድታጠባ ሐሊማ ለተባለች ሴት በመስጠታቸው ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ተለይተዋቸው ኖሩ፡፡ ከዚህ በኋላ በመመለስ አብረው ጥቂት እንደኖሩ ገና የስድስት ዓመት ጨቅላ ሳሉ ወላጅ እናታቸውን በሞት ተነጠቁ፡፡ በዚህም ሳቢያ በአያታቸው በአብዱል ሙጠሊብ ዘንድ ለመኖር ተገደዱ፡፡



ካዕባ

በቁረይሽ ጎሣ ዘንድ የተከበሩት አያታቸው መሐመድን በጣም ይወዷቸውና ይንከባከቧቸው እንደ ነበር በሙስሊሞች የተጻፉት እነዚህ ድርሳናት ይዘክራሉ፡፡ በህፃንነታቸውም ከአያታቸው ጋር አምልኮተ ጣዖት ወደሚፈፀምበት ወደ ካዕባ ይሄዱ ነበር፡፡ ነገር ግን ገና የስምንት ዓመት ህፃን ሳሉ አያታቸው አብዱል ሙጠሊብ ሕይወታቸው በማለፉ ሳብያ ከእርሳቸው ጋር ከሁለት ዓመት በላይ ለመቆየት አልታደሉም፡፡ ቤተሰባዊ እንክብካቤ ሊያደርጉላቸው የሚችሉትን ሰዎች አንድ በአንድ በሞት የተነጠቁት መሐመድ እስከ አሥራ ሁለት ዓመታቸው ድረስ ግመልና ፍየል በመጠበቅ አጎታቸው አቡጧሊብን እያገዙ አብረዋቸው ይኖሩ

[11] Guillaume. *the Life of Muhammad;* pp. 66-68

ነበር፡፡ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳሉ ከአጎታቸው ጋር ለንግድ ወደ ሦሪያ እንደተጓዙ ከታሪካቸው እንረዳለን፡፡[12]

እነዚህ ሁሉ የችግር ዘመናት በመሐመድ ስብዕና ላይ የጎላ ተፅዕኖ ነበራቸው፡፡ በመከራ ውስጥ ማለፋቸው ጠንካራና ፅናት ያላቸው እንዲሁም ብልጠትን የተሞሉ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ሲሆን በሥጋ ዘመዶቻቸው መገፋታቸውና ተቀባይነትን ማጣታቸው ደግሞ የሰዎችን ሕይወት በኃይል ተቆጣጥሮ የመግዛት እንዲሁም ከሐሳባቸው ጋር የማይስማሙትን ሰዎች እንደ ጠላት የመቁጠር ሥነ-ልቦና እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

## ጋብቻ ከከዲጃ ጋር


የመሐመድ ሕይወት መቃናት የጀመረው ከቁረይሽ ጎሣ ለሆኑት ከዲጃ ለተባሉት ኃብታም መበለት በውክልና የንግድ እንቅስቃሴ መምራት በጀመሩበት ወቅት ነበር፡፡ በሙስሊሞች የተጻፉት ግለ ታሪኮቻቸው እንደሚናገሩት በታማኝነታቸው የተማረኩት የ40 ዓመቷ ከዲጃ በወቅቱ ዕድሜያቸው 25 ለነበረው ለመሐመድ የጋብቻ ጥያቄ በማቅረባቸው ሳብያ በመካከላቸው የነበረው የ15 ዓመታት ልዩነት ሳያግዳቸው በትዳር ተጣምረው የከዲጃ ሕይወት እስካለፈበት ጊዜ ድረስ ለ25 ዓመታት ያህል አብረው ኖረዋል፡፡ በወቅቱ በነበረው የአረቦች ባሕል መሠረት አባት ዕውቅና ሳይሰጥ መጋባት ስለማይቻልና ከመሐመድ ጋር ትዳር መመሥረታቸው በአባታቸው ዘንድ ስላልተወደደ ከዲጃ አባታቸውን አስካሪ መጠጥ በማጠጣት ጋብቻውን ሕጋዊ ማድረግ ችለው ነበር፡፡ ከዚህ ያለአቻ

12 Juan E. Campo. *Encyclopedia of Islam;* 2009, pp. 491-492

ጋብቻ መሐመድ ስድስት ልጆችን ያፈሩ ሲሆን ሦስቱን በእንቆቅላነታቸው በሞት ተነጥቀዋል፡፡[13]

መሐመድ ከአጎታቸው ጋርም ሆነ የከዲጃን የንግድ እንቅስቃሴ እየመሩ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወራቸው የክርስትና፣ የአይሁድና የዞራስትሪያኒዝም እምነት ተከታዮች ከሆኑ ሰዎች ጋር እንዲገናኙና ስለ እምነታቸው እንዲሰሙ ሰፊ ዕድልን እንደሰጣቸው መገንዘብ እንችላለን፡፡ የእነዚህ እምነቶች ተፅዕኖም በቁርአን ውስጥ በእጅጉ ተንፀባርቆ እንመለከታለን፡፡

## የመጀመርያው መገለጥ



ሒራ ዋሻ

ከከዲጃ ጋር ትዳር ከመሠረቱ በኋላ ለንግድ ረጃጅም ጉዞዎችን ማድረግ አላስፈለጋቸውም ነበር፤ ይህም ሁኔታ የተረጋጋ ሕይወት መምራት ስላስቻላቸው መንፈሳዊ ጉዳዮችን በማሰላሰል ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር፡፡ ለዚህ ደግሞ ተስማሚ ሆኖ ያገኙት ሒራ የተባለ እዚያው መካ አካባቢ የሚገኘውን ዋሻ ነበር፡፡ ለስድስት ወራት ያህል ወደ ዋሻው በመመላለስ በፆም፣ በጸሎትና በተመስጦ በማሰላሰል ካሳለፉ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን መልአኩ “ጂብሪል (ገብርኤል)” ወደ እርሳቸው በመምጣት በሱራ 96፡1-5 ላይ የተጻፈውን ቃል “ገለጠላቸው”፡፡

መሐመድ በመጀመርያዎቹ መገለጦቻቸው የመካ ነዋሪዎችን የጣዖት አምልኮ መንቀፍ ጀመሩ፡፡ ይህ ደግሞ ለቁረይሾች ገቢና ነባር ልማድ ሥጋት ስለነበር

13 Alfred Guillaume. *The Life of Muhammad;* 1955, p. 83

ውክቢያን አስነሱባቸው፡፡ ለተነሳባቸው ለዚህ ውክቢያና ተቀባይነት ማጣት በሁለት መንገዶች ነበር ምላሽ የሰጡት፡፡ የመጀመርያው ሽሽት ወይም ስደት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሰይጣናዊ ጥቅሶች (Satanic Verses) በመባል የሚታወቁትን መገለጦች መፍጠር ነበር፡፡

## የሶሃቦች ስደት ወደ ምድረ ሐበሻ

የመካ ነዋሪዎች በመሐመድ ላይ የሚያደርሱት ስደት እየጨመረ መጣ፡፡ ከስደቱ ማምለጫ ለራሳቸውና ለተከታዮቻቸው (ለሶሃቦች) ከተለያዩ አካባቢዎች ድጋፎችን ለማግኘት ጥረት ቢያደርጉም ስላልተሳካላቸው የነበራቸው አማራጭ ተከታዮቻቸውን ደህንነታቸው ሊጠበቅ ወደሚችልበት ራቅ ወዳለ ቦታ እንዲሄዱ ማድረግ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በ613 ዓ.ም. ከተከታዮቻቸው መካከል አሥራ አምስቱን በወቅቱ ጠንካራ መንግሥታዊ አስተዳደር ወደነበራት ወደ አክሱም ሰደዱ፡፡ ክርስቲያን የነበረውም የአክሱም ንጉሥ ጥገኝነት በመስጠት በመልካም ሁኔታ አስተናግዷቸው ነበር፡፡ ይህ በእስላማዊ ምንጮች ውስጥ “የመጀመርያው ሒጅራ (ስደት)” ተብሎ ተጠርቷል፡፡ እነዚህ የመጀመርያዎቹ ስደተኞች ገና አክሱም ከመድረሳቸው የመካ ጣዖታውያን እስልምናን መቀበላቸውን በመስማታቸው ምክንያት ብዙም ሳይቆዩ ተመልሰው ሄደዋል፡፡ ነገር ግን መካ ከደረሱ በኋላ ጉዳዩ ሌላ ሆኖ ስላገኙትና ስደቱም ከፊት ይልቅ ስለበረታ በ615 ዓ.ም. በመሐመድ የአጎት ልጅ በጃዕፋር የሚመራ ቁጥሩ ወደ አንድ መቶ የሚሆን የሙስሊሞች ቡድን ወደ አክሱም ተንቀሳቅሷል፡፡[14] እነዚህ የስደተኛ ቡድኖች ኋላ ላይ ኸሊፋ በመሆን የሙስሊሙን ዓለም ያስተዳደሩትን ኡሥማን ኢብኑ አፋንና

[14] Rafiq Zakaria. *Muhammad and the Quran;* 1991, pp. 403-404; Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp. 146-155

የመሐመድ ልጅ የነበሩትን የትዳር አጋራቸውን ሩቂያ ቢንት መሐመድን ጨምሮ በእስልምና ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና የነበራቸውን ዕውቅ ሰዎች ያካተቱ ነበሩ፡፡[15]

## ሰይጣናዊ ጥቅሶች

ተመሳሳይ ርዕስ ካለው በሰልማን ሩሽዲ ከተጻፈውና ዓለም አቀፋዊ የሙስሊሞች ቁጣና ተቃውሞን ካስነሳው የልበወለድ መጽሐፍ የተነሳ በዓለም ዙርያ የሚገኙ ብዙ ሕዝቦች ከዚህ ታሪክ ጋር ተዋውቀዋል፡፡ ይህ ታሪክ ቀዳሚያን በሆኑት እስላማዊ ምንጮች ውስጥ በስፋት የተዘገበ ሲሆን[16] የመሐመድን እውነተኛ ነቢይነት ጥርጣሬ ላይ ስለሚጥል ብዙ ሙስሊሞች ሊቀበሉት አይወዱም፡፡ ታሪኩ በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ወቅቱ መሐመድ ስደትና መገለል ስለበረታባቸው የመካ ነዋሪዎችን ለማስደሰት መልዕክታቸውን ማመቻመች የጀመሩበት ጊዜ ነበር፡፡ አንድ ቀን ካዕባ በተባለው የመካ አምልኮተ ጣዖታት ቦታ  ሳሉ የተለያዩ የአረብ ጎሣ መሪዎችን አንድ ላይ ተሰብስበው ተመለከቱ፡፡ የእነዚህን ሰዎች ልብ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉና ከራሳቸው ወገን ማሰለፍ እንደሚችሉ ካወጡና ካወረዱ በኋላ አንድ ሐሳብ ተከሰተላቸው፡፡ በአረብያ ይመለኩ ከነበሩት ጣዖታት መካከል ታዋቂ የሆኑት ሦስቱ ጣዖታት፤ ማለትም  *አል-ላት፣ መናትና ኡዛ* ከፍተኛ ክብር እንዳላቸውና ከአላህ የማማለድ ሥልጣን እንዳላቸው ተናገሩ፡፡ ይህ ደግሞ ቁረይሾችን አስፈነደቀ፡፡ እርሳቸው ሲሰግዱ ሁሉም አብረዋቸው ሰገዱ፡፡ የመካ ነዋሪዎች እስልምናን መቀበላቸውን በተመለከተ እስከ አክሱም ድረስ የተወራው ወሬ ከዚህ ጋር የተያያዘ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ሱራ 53፡19-20 ላይ የሚገኘው “አል-ላትንና

---

15 Ibid.

16 Al-Tabari, *The History of al-Tabari (Ta'rikh al-rusul wa'l-muluk),* Vol. VI: *Muhammad at Mecca;* Translated by W. M. Watt and M.V. McDonald, pp. 107-112. Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp. 165-167

አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (አያችሁን? የምትግገዟቸው ኃይል አላቸውን?)”[17] የሚለው ጥቅስ መጀመርያ እንዲህ አልነበረም፡፡ “እነዚህ ከፍ ያሉ በራሪዎች ናቸው፡፡ ምልጃቸውም ተስፋ ይደረጋል” የሚል ተጨማሪ ንባብ ነበረው፡፡

ቀደም ሲል ሲነቅፏቸው የነበሩትን ጣዖታት ማሞጋገሣቸውና የተቃወሙትን አምልኮተ ጣዖት የሚያጸድቅ “መገለጥ” መናገራቸው ተከታዮቻቸውን ማስቆጣቱና ጥርጣሬ ላይ መጣሉ አልቀረም፡፡ በዚህ ጊዜ መሐመድ ተከታዮቻቸውን ላለማጣትና ከገቡበት አጣብቂኝ ለመውጣት ሌላ መላ ዘየዱ፡፡ ይህም “መገለጡ” ከሰይጣን መሆኑን መናገር ነበር፡፡ ይህ ውኾንብር ከተከታዮቻቸው መካከል የተወሰኑትን ጥርጣሬ ላይ የጣለና የቁረይሾች ስደት እንዲበረታባቸው ያደረገ ቢሆንም ቅሉ በአጎታቸው በአቡጧሊብና በባለቤታቸው በከዲጃ ድጋፍ አስቸጋሪውን ጊዜ ለማለፍ ችለዋል፡፡ ስህተቱም ያልተለመደና በሌሎች ነቢያት ላይ ያልደረሰ አለመሆኑን ለማስረዳት ሌሎች “መገለጦችን” ሲያመጡ እንመለከታለን፡-

> “ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም ባነበበ (እና ዝም ባለ) ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጅ፡፡ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፡፡ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡ ሰይጣን የሚጥለውን ነገር ለእነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ላለባቸው ልቦቻቸውም ደረቆች ለሆኑት ፈተና ሊያደርግ (ይጥላል)፡፡ በዳዮችም ከእውነት በራቀ ጭቅጭቅ ውስጥ ናቸው፡፡” (የሐጅ ምዕራፍ 22፡52-53)

---

17 በአማርኛ የቁርአን ትርጉም በቅንፍ የተቀመጡት በአረብኛው አይገኙም፡፡

የጉዳዩን ታሪካዊነት በተመለከተ ሻቢር አኽታር የተሰኙ ሙስሊም ጸሐፊ የሚከተለውን ብለዋል፡- "ይህ በጣም ሐቀኛ በሆነ እስላማዊ ትውፊት የተዘገበው አውዳሚ የሆነ ክስተት ሰይጣን በነቢዩ የመገለጥ ንባብ አቀባበል ጣልቃ ሊገባ እንደሚችል አሳይቷል ... ሩሽዲ በሱራ 53 ላይ የሚገኘውን ሙሉ ተቀባይነት ያለውንና ሳይከለስ የተጠበቀውን ተያያዥ አንቀፅ ጠቅሶ በማጣመም በመጀመርያው መገለጥ ውስጥ የነበረውን ሰይጣን ያስገባውን ተክቷል፡፡"[18]

"ሰይጣናዊ ጥቅሶች" የሚለውን ሐሳብ ያመነጨው ሰልማን ሩሽዲ ወይም ሌላ ሰው አይደለም፡፡ ታሪኩ በእስላማዊ ምንጮች ውስጥ የተዘገበና ለክፍለ ዘመናት የኖረ ነው፡፡ ይህ "የሰይጣናዊ ጥቅሶች" ክስተት መሐመድ መገለጥን በመገለጥ የመሻር አስተምህሮን እንዲያስተዋውቁ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡[19]

## ስደት ወደ ያሥሪብ

የትዳር አጋራቸው ከዲጃና አጎታቸው አቡጧሊብ ተከታትለው በመሞታቸው ምክንያት 619 ዓ.ም. ለመሐመድ ጥሩ ዓመት አልነበረም፡፡ ሁለቱ ሰዎች ተሰሚነት ስለነበራቸውና አደጋ እንዳይደርስባቸው ከለላ ያደርጉላቸው ስለነበር ሁለቱንም በተከታታይ ማጣት ትልቅ ጉዳት ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ተጋላጭ እንዲሆኑና ስደት እንዲበረታባቸው ስላደረገ ሊመጣባቸው ካለው አደጋ ለማምለጥ በፈጣን አእምሯቸው መላ መምታት ነበረባቸው፡፡ ስለዚህም በጣም በተጠና ሁኔታ በሚስጥር በወቅቱ ያሥሪብ ተብላ በምትታወቀው (ኋላ ላይ መዲና በተሰኘችው) ከተማ ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት የአረብ ጎሣ መሪዎች ጋር መረጃዎችን መለዋወጥ ጀመሩ፡፡

---

18 Shabbir Akhtar. *Be Careful With Muhammad;* 1992, p. 114

19 ሳም ሰለሞንና ኢ-አልመቅዲሲ፡፡ *አል-ሂጅራ፣* ገፅ 60

ያሥሪብ ከሞላ ጎደል የአይሁድ ከተማ ነበረች፡፡ ነገር ግን አውስና ኸዝራጅ የተሰኙ እሳትና ጭድ የሆኑ የአረብ ጎሣዎችም ይኖሩባት ነበር፡፡ እነዚህ ጎሣዎች በአይሁድ የበላይነትና ስኬት ይቀኑ ነበር፡፡ መሐመድ ሁለቱን ጎሣዎች የበላይ እንደሚያደርጉና አይሁድን እንደሚያዋርዱ ቃል በመግባት አስማምተዋቸው “የአቃባ ቃል ኪዳን” በመባል የሚታወቀውን ስምምነት ከተወካዮቻቸው ጋር ተፈራረሙ፡፡



ቁባ መስጊድ - ነቢዩ መሐመድ በመዲና በሰሩት የመጀመርያው መስጊድ ቦታ ላይ ይገኛል

ኸዝራጅ በእናታቸው በአሚና በኩል የመሐመድ የአክስት ልጆች ከሆኑትና በአያታቸው በአብዱል ሙጠሊብ በኩል ከሚዛመዷቸው ከበኒ አል ነጃር ጋር ዝምድና ነበራቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ መሐመድ ከአይሁድ ከተማ ከያሥሪብ ጋር ጠንከር ያለ ቤተሰባዊ ትስስር ነበራቸው፡፡ በእርግጥ አይሁድ ያሥሪብን ስለቆረቆሯት የአይሁድ ከተማ እንደሆነች ነበር የሚያስቡት፡፡ ነገር ግን የአረብ ጎሣዎች የሆኑት አውስና ኸዝራጅ ከተማይቱን የራሳቸው ብቻ የማድረግ ፅኑ መሻት ነበራቸው፡፡ መሐመድን በጣም እንደሳባቸው የሚታሰብ አንድ ነገር ቢኖር የያሥሪብ ሰዎች በቁረይሾች ላይ የነበራቸው ቁርሾ ነበር፡፡ ያሥሪብ የአረብያ ዋነኛ የንግድ ከተማ የነበረች ብትሆንም ነገር ግን የዘምዘም ውኃ በተገኘ ጊዜና ውኃ ችግር መሆኑ ከቀረ በኋላ መካ እንደ ማረፍያና ትንፋሽ መሰብሰብያ ጣብያ ዋነኛ የሲራራ ነጋዴዎች መተላለፍያ ሆና ነበር፡፡ አውስ እና ኸዝራጅ በያሥሪብ ውስጥ የነበረውን

የአይሁድን የበላይነትና ቁረይሾች በርቀት ሆነው የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ የመስበር ብርቱ መሻት ነበራቸው፡፡[20]

ወደ ያሥሪብ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ከተማይቱን ማዘጋጀት ስለነበረባቸው ለሁለቱ የአረብ ጎሣዎች ጠላት የነበሩትን የመካ ቁረይሾች የሚያብጠለጥሉና አይሁድን የሚያሞጋግሱ "መገለጦችን" መናገር ጀመሩ፡፡ ይህም ልባቸው በቁረይሾች ጥላቻ የተሞላው ሁለቱ የአረብ ጎሣዎች በአዲሱ ነቢይ መሪነት ድል የሚነሱበትን ቀን እንዲናፍቁና አይሁድ ደግሞ መሐመድን እንደ ወዳጅ እንዲቆጥሯቸው አደረገ፡፡ አይሁድ በነዚህ መገለጦች ስለተዘናጉ ወዳጅ መስሎ በመቅረብ እነርሱን ለማጥፋት የተጠነሰሰውን ሤራ አላወቁም ነበር፡፡[21]

መሐመድ አስፈላጊ የሆኑትን ዝግጅቶች ካጠናቀቁ በኋላ በ622 ዓ.ም. በሌሊት ከተወሰኑ ተከታዮቻቸው ጋር ወደ ያሥሪብ አቀኑ፡፡ ይህም ጉዞ "ሒጅራ" በመባል የሚታውቅ ሲሆን እስልምና ከአንዱ ምዕራፍ ወደሌላው የተሸጋገረበት ታሪካዊ ክስተት ነበር፡፡ ሒጅራ በእስልምና ውስጥ ካለው ጉልህ ሚና የተነሳ 622 የእስልምና ዘመን መቁጠርያ መጀመርያ ለመሆን በቅቷል፡፡ ከሒጅራ በኋላ የእስልምናው ነቢይ መሐመድ "ከሰላማዊ" ሰባኪነት ወደ ጦር አበጋዝነት ተለወጡ፡፡ በመዲና ኃይላቸውን ካጠናከሩ በኋላ አይሁድን የሚያሞጋግሱ "መገለጦቻቸው" እነርሱን በሚያንቋሽሹ መገለጦች ተተኩ፡፡ ባገኟቸው አጋጣሚዎች ሁሉ እነርሱን ማጥቃትና ማዳከም ተያያዙ፡፡ በመካ ነዋሪዎችም ላይ ጥቃቶችን ማድረስ ጀመሩ፡፡ ከዚህ በኋላ ጂሃድ የሕይወታቸው መዳፍና ፈለግ ሆነ፡፡

---

[20] ሳም ሶሎሞንና ኢ.አል መቅዲሲ፡፡ *አል-ሒጅራ፣* ገፅ 47

[21] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 49

## ሰይፍ የታጠቀው ነቢይ



አል-በታል የሚል ስያሜ ያለው የነቢዩ መሐመድ እንደሆነ የተነገረለት ሰይፍ፤ በኢስታንቡል ከተማ ቶፕካፒ ቤተ መዘክር ውስጥ ይገኛል፡፡[22]

መሐመድ “የነቢይነት” አግልግሎታቸውን ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ የመካ ከተማን በኃይል እስከተቆጣጠሩበት ጊዜ ድረስ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ የተጠናና በሦስት ደረጃዎች የተከፋፈለ መሆኑን እናስተውላለን፡፡ በመካ ከተማ በነበሩ ጊዜ ተቃዋሚዎቻቸውን ገሃነም እንደሚገቡ ከማስፈራራት የዘለለ አካላዊ ጥቃት ሲያደርሱ አንመለከትም፡፡ ወደ መዲና በገቡ በመጀመርያዎቹ ዓመታት ደግሞ ለአዲሱ ሃይማኖታቸው እንቅፋት እንደሚሆኑ የገመቷቸውን ተቃዋሚዎቻቸውን ሸማቂዎችን በመላክ አስገድለዋል፡፡ በመካ ነጋድያን ላይ ድንገተኛ ጥቃቶችን በመፈፀምም ያዘርፉ ነበር፡፡ ወታደራዊ ኃይላቸውን እስኪያደራጁ ድረስ ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ በጀርባ በኩል እነርሱን የሚያዳክሙ ሥራዎችን እየሠሩ በድርድርና የተለያዩ የሰላም ስምምነቶችን በመፈራረም ምቹ ጊዜ እስኪመጣላቸው ድረስ ይጠባበቁ ነበር፡፡ ትልቅ አቅም የሚጠይቁ ከባባድ ጦርነቶችን ከማድረግ ይልቅ በግለሰቦችና በአናሳ ቡድኖች ላይ በማነጣጠር እዚያም እዚህም ፈጣን ጥቃቶችን በመፈፀም ጠላቶቻቸውን ያሸብሩ ነበር፡፡ ከጠላቶቻቸው አቅም ጋር የሚመጣጠን በቂ

---

22 በተከታዩ ድረ-ገፅ ላይ 9 የሚሆኑ የነቢዩ ንብረት እንደነበሩ የሚነገርላቸው ሰይፎች ከነምስላቸው ይገኛሉ፡-
http://www.usna.edu/users/humss/bwheeler/swords/index_of_swords.html

ወታደራዊ ኃይል እንዳደራጁ ካረጋገጡ በኋላ ግን ቀደም ሲል የተፈራረሟቸውን የሰላም ስምምነቶች በማፍረስ ትልልቅ የውጊያ ግንባሮችን መክፈት ጀመሩ፡፡ ዋና ጠላቶቻቸው የነበሩትን ቁረይሾችንም በመግጠም ድል ነሷቸው፡፡ የመካ ከተማንም ተቆጣጠሩ፡፡ በማስከተልም መላውን የአረብ ባህረ ገብ ምድር በኃይል አሰለሙ፡፡[23]

አክራሪ ሙስሊሞች የመጀመርያዎቹን የመሐመድ ዓመታት **"ዘመነ ብዕር"** በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ በመዲና የነበሩትን የመጀመርያዎቹን ዓመታት ደግሞ **"ዘመነ ሚዛን"** ይሏቸዋል፡፡ ይህም ማለት እንደየሁኔታው ብዕርንና ሰይፍን እያፈራረቁ መጠቀም፤ ማለትም ምቹ ሁኔታ ሲፈጠር ጠላትን ማጥቃት፤ ነገሮች ካልተመቻቹ ደግሞ ውጊያውን የሐሳብ ማድረግ ማለት ነው፡፡ መሐመድ በወታደራዊ አቅም ከተደራጁ በኋላ የሚገኙትን ዓመታት ደግሞ **"ዘመነ ሰይፍ"** በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ ይህ ጊዜ ሰዎች በግድም ሆነ በውድ የሚሰልሙበት አለዚያ ደግሞ ተዋርደው ለእስልምና ግብርን እየከፈሉ የሚኖሩበት ዘመን ነበር፡፡

መሐመድ በመዲና በኖሩባቸው 10 ዓመታት ውስጥ 27 ውጊያዎች ላይ በአካል መሳተፋቸውን ኢብን ኢስሐቅና አል-ጦበሪ ዘግበዋል፡፡[24] እነዚህም የውጊያ ግንባሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

---

[23] Mark A. Gabriel. *Islam and Terrorism: What the Qur'an Really Teaches about Christianity, Violence and the Goals of the Islamic Jihad;* Charisma House Publishers, 2002, p. 88
[24] Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp. 659-660

- አል አብዋእ
- ቡወጥ
- አል ዑሻይራህ
- የመጀመርያው የበድር ጦርነት
- ታላቁ የበድር ጦርነት
- በኒ ሱለይመን
- አል ሰዊቅ
- ገተፈን
- በኒ ሊህየን፡፡
- ዙ ቀደር፡፡
- በኒ አል-ሙስጠሊቅ
- ሁደይቢያ
- ኸይበር
- የመካ መያዝ
- ሁነይን
- አል ጣኢፍ
- ተቡክ
- ባህረን
- በኒ ቀይኑቃዕ
- ኡሁድ
- ሐመር ዑል-አሰድ
- በኒ ናዲር
- የነኽል ዘቱልሪቃ
- የበድር የመጨረሻው ጦርነት
- ዱመት ዑል-ጀንደል
- አል-ኸንደቅ
- በኒ ቁረይዛ

መሐመድ እራሳቸው በዘጠኝ ጦርነቶች ውስጥ በአካል በመግባት ሰይፍ መዘዋ፡- በድር፣ ኡሁድ፣[25] አል-ኸንደቅ፣ ቁረይዛ፣ አል-ሙስጠሊቅ፣ ኸይበር፣ [መካን] መያዝ፣ ሁነይን እና አል ጣኢፍ፡፡ በተጨማሪም ኢብን ኢስሐቅ በመሐመድ ትዕዛዝ ተከታዮቻቸው የፈፀሟቸውን 35 ጥቃቶች ዘርዝረዋል፡፡[26]

---

[25] የኡሁድ ጦርነት ነቢዩ የተሸነፉበት ጦርነት ነበር፡፡ በዚህ ጦርነት ላይ አጎታቸው ሐምዛ የሞቱ ሲሆን መሐመድ እራሳቸው ከንፈራቸው ተሰንጥቆ የፊት ጥርሶቻቸው ረግፈዋል፡፡ የመሐመድ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሁለት ጥርሶች ዛሬ በኢስታንቡል ሙዚየም ውስጥ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ (Paul Fregosi. *Jihad in the West, Muslim Conquest from 7th to 21st Centuries;* 1998, p. 53)

[26] Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp. 659-660

3

# የመሐመድ ውርሶች

መሐመድ ብዙ ውርሶችን (Legacies) ትተው አልፈዋል፡፡ አንዳንዶቹ አዎንታዊ ሲሆኑ ብዙዎቹ ደግሞ አሉታዊ ናቸው፡፡ ከሥነ ምግባር ያፈነገጡ አስደንጋጭ ተግባራትንም ፈፅመዋል፡፡ እነዚህ የመሐመድ ውርሶች ከሁለት ምንጮች የሚመነዘሩ ናቸው፤ እነርሱም ቁርአንና ሱና ይሰኛሉ፡፡

## ቁርአን

በሙስሊሞች እምነት መሠረት ቁርአን ፍፁም የሰው እጅ ያልገባበት ከአላህ ዘንድ በቀጥታ የወረደ መገለጥ ነው፡፡ ይህንንም መገለጥ 'ናዚል' ወይም 'ተንዚል' በማለት ይጠሩታል፡፡ በ23 ዓመታት ውስጥ ለመሐመድ በጅብሪል አማካይነት የወረዱላቸው የአላህ ቀጥተኛ ንግግሮች ስብስብ እንደሆነም ያምናሉ፡፡ "ኡም አል-ኪታብ" (የመጽሐፉ እናት) በመባል የሚታወቅ ያልተፈጠረ ነገር ግን አላህ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ከርሱ ጋር የነበረ ጽሑፍ እንዳለና ቁርአንም የዚያ ግልባጭ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ (ሱራ 13፡39)

ነቢዩ በሕይወት በነበሩበት ዘመን ቁርአን በአንድ ጥራዝ አልተሰበሰበም ነበር፡፡ ቁርአንን በአንድ ጥራዝ እንዲሰበሰብ ያደረጉት የመጀመርያው ሰው ኸሊፋ አቡበከር ሲዲቅ ሲሆኑ በእርሳቸው ትዕዛዝ በዘይድ ጣቢት የተሰበሰበው የመጀመርያው ጥራዝ "ስሑፍ" በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ ስያሜውም ከኢትዮጵያ እንደተወሰደ ይነገራል፡፡ ይህ የቁርአን ስብስብ ያለ አናባቢ የተጻፈ ስለነበረ አንድ

ወጥ የሆነ አነባበብ አልነበረውም፡፡[27] በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በስደት ኖረው የነበሩት ኸሊፋ ኡሥማን ታርሞ አንድ መልክ ያለው ቁርአን እንዲዘጋጅ ካደረጉ በኋላ የመጀመርያዎቹን ጽሑፎች አቃጥለዋቸዋል፡፡[28]

ብዙ ሙስሊሞች አሁን በእጃቸው የሚገኘው የአረብኛ ቁርአን በ1924 ዓ.ም. ይህንን መልክ እንደያዘና ከዚያ ቀደም ከሚገኙት የእጅ ጽሑፎች በብዙ መልኩ የሚለይ መሆኑን አያውቁም፡፡ "ሮያል ካይሮ ኤዲሽን" በመባል የሚታወቀው የአሁኑ ቁርአን ብዙ ጥንታዊ የቁርአን የእጅ ጽሑፎችን ያላገናዘበ ነው፡፡ በተለይም *የሰነዓ የእጅ ጽሑፎች* በመባል የሚታወቁት የቁርአን ኮፒዎች ከተገኙ ወዲህ ይህ መጽሐፍ ሙስሊሞች ለዘመናት ሲናገሩለት እንደኖሩት ያልተለዋወጠ ሰነድ አለመሆኑ ስለተደረሰበት ብዙ መልስ ያላገኙ ጥያቄዎች ከምሑራን ዘንድ እየተነሱ ይገኛሉ፡፡[29] በመጀመርያዎቹ ሙስሊሞች ዘመን እንኳ አንድ ዓይነት ቁርአን እንዳልነበረና በተለያዩ ሰዎች እጅ የሚገኙት የቁርአን ጽሑፎች ብዙ ልዩነቶች የሚታዩባቸው እንደነበሩ ከእስላማዊ ምንጮች መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ቁርአንን የማስተማር ብቃቱ በመሐመድ እንደተመሰከረለት በሐዲሳት ውስጥ የተዘገበው አብዱላህ ኢብን መስዑድ በራሱ የቁርአን ቅጂ ውስጥ አልፋቲሃ የሚለውን ምዕራፍ አላካተተም ነበር፡፡ የእርሱ ቅጂ ሱራ 113 እና 114 አልነበረውም፣ ሱራ 3፡19፣ 39 ላይ የተለየ ንባብ ይከተላል፣ ሱራ 9 ላይ ቢስሚላህ የሚለው የለውም፡፡[30] የዘይድንም ቁርአን አይቀበልም ነበር፡፡[31]

---

27 የአማርኛ ቁርአን መቅድም፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ ገፅ 11

28 ዝኒ ከማሁ፣ Sahih Al Bukhari 6:61:510

29 Keith Small. *Holy Books Have History: Textual History of the New Testament and the Qur'an;* 2010, pp.116-117

30 Abu Bakr `Abdullah b. abi Da'ud. *Kitab al Masahif;* ed. A. Jeffery, Cairo, 1936/1355, p. *17*

31 Ibn Sa'ad. *Kitab al tabaqat al kabir;* vol. 2, p. 444

ሳሂህ ሙስሊም ውስጥ እንደተዘገበው በመሐመድ ዘመን ሙስሊሞች 129 አንቀፆች ካሉት ሱራ በረዓት (አል-ተውባ) ጋር እኩል የሆነ ሱራ ያነበንቡ ነበር፡፡ ነገር ግን ከአንድ አንቀፅ በስተቀር ሙሉ በሙሉ ተረስቷል፡፡ አንዱም አንቀፅ ቢሆን በሐዲስ ውስጥ ከመጠቀሱ ውጪ በቁርአን ውስጥ አልተካተተም፡፡[32]

ኢብን አቢ ዳውድ የሚከተለውን አስተላልፈዋል፡ “ብዙ የወረዱ የቁርአን ጥቅሶች በየማማ ጦርነት ላይ በሞቱት ብዙ ሰዎች ይታወቁ ነበር .... ከጦርነቱ በተረፉት ሰዎች ግን አይታወቁም ነበር እንዲሁም በጽሑፍ አልሰፈሩም ነበር፡፡ ቁርአን ሲሰበሰብ አቡ በከር፣ ዑመርም ሆነ ኡሥማን አያውቋቸውም ነበር፡፡ ከእነርሱ በኋላ በነበረ አንድም ሰው ጋ ማግኘት አልተቻለም፡፡”[33] ኢብን አቢ ዳውድ ከዚህ በተጨማሪም አንዳንድ የቁርአን አንቀፆች ሆነ ተብለው እንዳይካተቱ መደረጋቸውን ዘግበዋል፡፡[34]

አስ ሱዩጢ፣ ኢትቃን በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ የሚከተለውን ማስጠንቀቅያ አስቀምጠዋል፡- “ከእናንተ መካከል ማንም ሰው ሙሉውን ቁርአን አግኝቼዋለሁ ብሎ መናገር የለበትም፡፡ የቁርአን አብዛኛው ክፍል የጠፋ ሆኖ ሳለ ሁሉን አውቃለሁ ብሎ መናገር እንዴት ይቻላል? ከዚህ ይልቅ የተረፈውን አግኝቼዋለሁ ብሎ ይናገር፡፡”[35]

የሚከተለው ዘገባ ከአይሻ የተላለፈ ነው፡- “በድንጋይ ስለመውገርና ጎልማሳ ወንዶችን አሥር ጊዜ ጡት ስለማጥባት የሚናገሩት የቁርአን ጥቅሶች ወርደው ነበር፡፡ የተጻፈበትም ወረቀት ከእኔ ጋ በእኔ ትራስ ስር ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛ

---

[32] Sahih Muslim 5:2286; Jalal al Din `Abdul Rahman b. abi Bakr al Suyuti. *Al-Itqan fi `ulum al Qur'an;* Halabi, Cairo, 1935/1354, part 2, p. 25
[33] Ibn abi Da'ud. *Kitab al Masahif;* p. 23
[34] Ibid., p.11
[35] Al Suyuti. *Al- Itqan fi `ulum al Qur'an;* part 2, p. *25*

በሞቱ ጊዜ በእረፍታቸው ተዋክበን ሳለን  ፍየል ገብታ በላችው፡፡”[36] በሌላ ዘገባ ደግሞ አይሻ እንዲህ የሚል መረጃ አስተላልፋ ነበር፡- “ኀልማሶችን አሥር ጊዜ ጡት ማጥባት ጋብቻን ያፈርሳል የሚል ሕግ ለአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ወርዶላቸው ነበር፡፡ ሕጉም በቁርአን ውስጥ ነበር፡፡ አምስት ጊዜ በሚል ሌላ ሕግ ተሻረ፡፡ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በቁርአን ውስጥ ነበር፤ ሙስሊሞችም ይደግሙት ነበር፡፡”[37] እነዚህ ሕግጋት ዛሬ በሙስሊሞች እየተተገበሩ የሚገኙ ቢሆኑም በቁርአን ውስጥ ግን አይገኙም፡፡

አል ቡኻሪ የሚከተለውን ዘግቧል “አነስ ኢብን ማሊክ እንዳስተላለፈው ‹‹በቢር ማዑና የሞቱትን ሰዎች በተመለከተ እንዲህ የሚል አያት እንቀራ ነበር፡- ‹ለሕዝባችን ጌታችንን እንዳገኘነውና በኛ ደስ መሰኘቱን እኛንም ማስደሰቱን ንገሩልን፡፡› ነገር ግን ይህ አያ ከቁርአን ውስጥ እንዲወጣ ተደርጓል››፡፡”[38]

ራፊዲ የተሰኙ አክራሪ ሺአዎች አሊ የነቢዩ ትክክለኛ ተተኪ መሆኑን የሚያሳዩትን ጨምሮ ወደ 500 የሚሆኑ ጥቅሶችን ኡሥማንና ተባባሪዎቹ ‹ሙሳሂፍ› ከተሰኘው ከመጀመርያው የቁርአን ስብስብ ውስጥ ሆነ ብለው ማስወገዳቸውን ይናገራሉ፡፡[39] አብዱላህ ዩሱፍ አሊ የተሰኙት የቁርአን ተርጓሚ ሱራ 33፡6 ላይ የኡበይ ቢን ካእብ ቁርአን ቅጂ “...እንዲሁም እርሱ አባታቸው ነው” የሚል ሐረግ እንዳለው በግርጌ ማስታወሻ ላይ አስቀምጠዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ሐረግ በዛሬዎቹ ቁርአኖች ውስጥ አይገኝም፡፡[40]

---

[36] Sunan Ibn Majah, 1944
[37] Sahih Muslim, book 8, no. 3421
[38] Sahih Bukhari, vol. 5, p. 288
[39] Ibn abi Da'ud. *Kitab al Masahif;* p. 36
[40] Abdullah Yusuf Ali. *The Holy Quran;* 1975, note 3674

## የሁከት መጽሐፍ

ከላይ የጠቀስናቸው ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ቁርአን በብዙ የእርማት ሥራዎች ውስጥ አልፎ አሁን ያለውን መልክ ቢይዝም ነገር ግን በሙስሊሞች ዘንድ እንከን አልባ የአላህ ቃል ተብሎ ታምኖበታል፡፡ ስለዚህ አንድ እውነተኛ ሙስሊም በውስጡ የሚገኙትን ትዕዛዛትና መመሪያዎች ለመፈፀም የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ብዙ ትዕዛዛትና ትምህርቶች ፍቅርን፣ መቻቻልንና ሰላምን ከመስበክ ይልቅ ጥላቻን፣ አለመቻቻልንና ነውጠኝነትን ስለሚያስተምሩ ቁርአንን አጥብቀው የሚይዙ ብዙ ሙስሊሞች ከሌሎች ጋር በሰላም ለመኖር ከመቸገር አልፈው ጥቃቶችን እስከመፈፀም ይደርሳሉ፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሲነፃፀር ቁርአን ትልቅ ሊባል የሚችል መጽሐፍ አይደለም ነገር ግን በውስጡ የሚገኙት “የሰይፍ ጥቅሶች” እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ በጦር ዘረፋ (አል-አንፋል)፣ በመሐመድ የጦርነት ውሎ (ሱረት አል-አሕዛብ)፣ ሰዎችን ከአገር በማባረር (አል-ሐሽር)፣ በጦርነት ሰልፍ (አስ-ሶፍ) እና በመሳሰሉት የተሰየሙ ምዕራፎች በውስጡ ይገኛሉ፡፡ ብዙ ጥቅሶቹ የሌሎች እምነቶችን አስተምህሮዎች፣ በተለይም ደግሞ ክርስትናንና ይሁዲን የሚያወግዙና የሚያንቋሽሹ እንደመሆናቸው መጠን አንድ ሙስሊም የሌሎችን እምነት ሳይነካና ሳይነቅፍ የራሱን ብቻ መከተል አስቸጋሪ ይሆንበታል፡፡

የቁርአን መክፈቻ በሆነው “አልፋቲሃ” ተብሎ በሚጠራው ምዕራፍ ሰባተኛው ቁጥር ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናነባለን፡- “የነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን በሉ)፡፡” በመሐመድ ትውፊቶች  መሠረት አላህ የተቆጣባቸው ሰዎች

አይሁድ ሲሆኑ የተሳሳቱት ደግሞ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡[41] ሙስሊሞች ይህንን ጸሎት በቀን አሥራ ሰባት ጊዜ ይደግሙታል፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ አይሁድ በአምላክ ቁጣ ሥር ያሉና ክርስቲያኖች ደግሞ የተሳሳቱ መሆናቸውን ያውጃሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ አንድ ሙስሊም ዕድሜ ልኩን ሳያቋርጥ ስለ ሌሎች እምነቶች ተከታዮች እያሰበና እምነታቸውን እየነቀፈ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጥቅሶች እስካሉ ድረስ ሙስሊሞች የሌሎችን እምነት ሳይነኩ መኖር አይቻላቸውም፡፡

## ሱና

በአንድ ወቅት መሐመድ ከቁርአን ጋር የተካከለ ነገር ከአላህ መቀበላቸውን ተናግረው እንደነበር በእስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ ተዘግቦ እናገኛለን፡- “ቁርአንና ከእርሱ ጋር እኩል የሆነ ሌላ ነገር (ሱና) ተሰጥተውኛል፡፡”[42]

*ሱና* የሚለው የአረብኛ ቃል ልማድ፣ ትውፊት ምሳሌነት የሚሉ ትርጉሞች አሉት፡፡[43] የሱና ፅንሰ ሐሳብ ሙስሊሞች ሁሉ ሊከተሉት የተገባውን የመሐመድን ምሳሌነት ያመለክታል፡፡ የሱናን አመጣጥ በተመለከተ ዶ/ር ሳም ሶሎሞንና ኤልያስ አል መቅዲሲ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> ሱና በገሃድ የተመሠረተው በመዲና ነበር፡፡ እንጭጭ የነበረው የሙስሊም ማሕበረሰብ አል ሙሐጂሩን ማለትም “ስደተኞች” በመባል የሚታወቁ የአረብ ጎሣዎችና አውስ እንዲሁም ኻዝራጅ ወይም አል-አንሳር በመባል የሚታወቁ የመዲና ጎሣዎች እንዲሁም የሌሎችም ቅይጥ

[41] Dr. Muhammad Taqi-ud-Din al-Hilali and Dr. Muhammad Muhsin Khan, *Interpretation of the Meanings of the Noble Qur'an in the English Language;* 1996, p. 30

[42] *Sunan Abu Dawud*, Book 40, Number 4587

[43] Campo. *Encyclopedia of Islam;* 2009, P. 644

ነበር፡፡ እያንዳንዱ ጎሣ ከሌላው የተለየ የየራሱ የሆነ እድሜ ጠገብ ትውፊት ስለነበረው እስልምናን እንደ ሃይማኖትና መሐመድን እንደ ነቢያቸው ቢቀበሉም ከመሐመድ ሂጅራ ጥቂት ጊዜ በኋላ ግጭት መፈጠሩ አልቀረም፡፡ መሐመድ ትልቅ የሆነ ቀውስ ሊፈጥር የሚችለውን ነገር ወዲያውኑ ደረሱበት፡፡ ስለዚህም ሁሉንም ጎሣዎች የአባቶቻቸውን ልማዶች እንዲሁም ከእስልምና በፊት የነበሩትን ልማዶቻቸውን በሙሉ በመተው የአዲሱን እስላማዊ ማሕበረሰብ መንፈስ እንዲቀበሉ ጠየቋቸው፡፡ ለዚህ ድጋፍ የሚሰጡ የተለያዩ የቁርአን አናቅፅንም ሲያመጡ እንመለከታለን፡፡[44]

አላህ በቁርአን ውስጥ መሐመድ “በጥሩ ሥነ ምግባር” ላይ መሆናቸውን ይመሰክርላቸዋል (68፡4)፡፡ ሙስሊሞችም ሁሉ የእርሳቸውን “መልካም ፈለግ” እንዲከተሉ አዟቸዋል (33፡21)፡፡ ነቢዩን መታዘዝ እርሱን መታዘዝ መሆኑንም ያስገነዝባቸዋል (4፡80)፡፡ ከዚህም አልፎ በሁሉም ረገድ ፍርድን በመስጠት ከራሱ ጋር በእኩል ደረጃ ላይ እንዳስቀመጣቸው ይገልፃል (33፡36)፡፡ በመጨረሻም አንድ ሰው ወደ ገነት ለመግባት መሐመድን መከተል የግድ እንደሆነ ይናገራል (3፡132፣ 33፡21፣ 24፡56)፡፡ ስለዚህ በእስልምና አስተምህሮ መሠረት የመሐመድን ሱና መከተል ጀነት የመግባት ያለመግባት ጉዳይ በመሆኑ ምክንያት ሙስሊሞች እጅግ ጥቃቅን በሆኑት ጉዳዮች እንኳ ሳይቀር ፈለጋቸውን ለመከተል ይሞክራሉ፡፡ እስልምናም የበላይነትን እንዲቆናጠጥ መርሆቻቸውን መከተል ወሳኝ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

---

[44] ሳም ሶሎሞንና ኢ.አል መቅዲሲ፡፡ *አል-ሒጅራ*፤ ገፅ 3

ለጂሃድ መፋፋም ምክንያት የሆኑት ኢብን ተይሚያ፣ አብዱል ወሃብና ሰይድ ቁጥብን የመሳሰሉት ሙስሊም አብዮተኞች በሙስሊሙ ማሕበረሰብ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማምጣት የቻሉት፤ ትምህርቶቻቸው ስሜትን የሚኮረኩሩና ፈቃድን የሚረቱ ውስብስብ ፍልስፍናዎች በመሆናቸው ሳይሆን መሐመድ ያስተማሯቸውንና የኖሯቸውን የሕይወት



ከአንድ ወይም ሁለት ስንዝር ቁመት ቀጭን እንጨት የሚሰራ የጥርስ መፋቅያ (ሚስዋክ) የነቢዩ ሱና ነው፡፡

አካሄዶች ግልፅና ቀለል ባለ ሁኔታ በማቅረባቸው ምክንያት ነው፡፡ የእነዚህን ግለሰቦች ትምህርቶች ያጠና ሰው ይህንን እውነታ በቀላሉ መታዘብ ይችላል፡፡

ቀደም ሲል እንደተባለው የሙስሊም ማህበረሰቦችን እንቅስቃሴዎች ሁሉ ለማወቅ መሐመድን ማወቅ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ እስልምና ዓላማው፣ ስልቶቹና ግቡ ምንድን ናቸው? በዘርያችን የሚገኙት እስላማዊ እንቅስቃሴዎች ምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ? ከዚህ በኋላስ ቀጣዩ ምዕራፍ ምን ይሆን? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘትና መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሐሳቦችን ለመለየት መሐመድን በጥልቀት ማወቅ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

# ክፍል 2

## ጥንታዊው ጂሃድና የዘመኑ የሽብር ስጋት

❶

# የጂሃድ ምንነትና ታሪክ

ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ባዘጋጀው የእስልምና ኢንሳይክሊፒድያ ውስጥ ጂሃድ እንደሚከተለው ተተርጉሟል፡-

> “ጂሃድ የሚለው የአረብኛ ቃል ጥሬ ትርጉም (በአምላክ መንገድ) መታገል ማለት ነው፡፡ በሃይማኖት የተደነገገ ጦርነትን ያመለክታል፡፡ ቁርአን የአምላክን አገዛዝ ለማስፋፋት ጂሃድን ያዛል (ሱራ 2፡192፣ 8፡ 39)፣ በጦርነት ውስጥ የሚገደሉትም በመጪው ሕይወት ሽልማት እንደሚጠብቃቸው ቃል ይገባል (ሱራ 9፡81-82፣ 48፡16)፡፡”[45]

የኢራኑን እስላማዊ አብዮት ያፋፋሙት የሺአው መሪ አያቶላህ ኾሜይኒ ጂሃድን በሚከተለው መልኩ ይተረጉሙታል፡-

> “ጂሃድ ማለት ሙስሊም ያልሆኑትን አካባቢዎች መውረር ማለት ነው፡፡ የዚህ የወረራ ጦርነት የመጨረሻ ግብ የቁርአን ሕግ የበላይነት ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ መንሰራፋት ነው፡፡”[46]

ሰይድ አቡል አላ ማውዱዲ የተሰኙ ስመጥር ሙስሊም ሊቅ ሚያዝያ 13/ 1939 ዓ.ም. ባደረጉት ዝነኛ ንግግር የጂሃድን ትርጉምና ዓላማ በሚከተለው መልኩ አስቀምጠዋል፡-

> “እስልምና እንደ ማንኛውም ዛፍ ቢሆንና ሙስሊሞችም ደግሞ እንደማንኛውም ሕዝብ ቢሆኑ ኖሮ  እስላማዊ ጂሃድ የአምልኮ ሁሉ

---

[45] Campo. *Encyclopedia of Islam;* p. 398

[46] Fregosi. *Jihad;* 1998, p. 20

ቁንጮና የዘውድ እንቁ ያደረጋትን ቀዳሚ ቦታዋን ማጣቷ ወንጀል ባልሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን እስልምና እንደማንኛውም ተራ ዛፍ አይደለም፡፡ ሙስሊሞችም ደግሞ እንደሌሎች ሕዝቦች አይደሉም፡፡ እውነታው እስልምና አብዮተኛ የሆነ አይዲዮሎጂ መሆኑ ነው፡፡ የመላውን ዓለም ማሕበራዊ ሥርኣት በማፍረስ በራሱ መሠረታዊ ሐሳቦችና አመለካከቶች መልሶ የሚገነባ አብዮታዊ አጀንዳ ነው፡፡ 'ሙስሊም' የሚለው ቃል አብዮታዊ መርሃ-ግብሩን ከግብ እንዲያደርስ በእስልምና የተደራጀ የዓለም አቀፋዊ ፓርቲ መጠርያ ነው፡፡ ጂሃድ ደግሞ እስላማዊ ፓርቲ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት የሚጠቀምበት አብዮታዊ ትግል ነው፡፡ እስልምና አይዲዮሎጂውንና ዓላማውን የሚቃወሙ በየትም ቦታ የሚገኙትን መንግሥታት በሙሉ ለማጥፋት ይፈልጋል፡፡ የእስልምና ግብ በራሱ እሳቤና ዓላማ ላይ የተመሠረተን መንግሥት ማቋቋም ነው፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ የትኛውም አገር ይህንን ሚና ቢጫወት ወይም በዚህ ሂደት ውስጥስ የትኛውም አገር ቢጨፈለቅ አሳሳቢ አይደለም፡፡ .... እስልምና ሃይማኖት ብቻ አይደለም ወይም የተወሰኑ የአምልኮ ሥርኣቶች መጠርያ አይደለም፤ ነገር ግን በዓለም ላይ የሚገኙትን እኩይ ሥርኣቶች በሙሉ በማጥፋት ለሰው ልጆች ደህንነት አስፈላጊ የሆነውን የራሱን የተሓድሶ መርሃ ግብር የሚተገብር ሁሉን አቀፍ ሥርኣት ነው፡፡ ከዚህ ማብራርያ ግልፅ ሊሆንላችሁ የሚገባው ነገር ቢኖር የእስላማዊ ጂሃድ ዓላማ እስላማዊ ያልሆነውን ሥርኣት በማስወገድ በዚያ ፋንታ የእስላማዊ መንግሥት አገዛዝን መመሥረት መሆኑ ነው፡፡ እስልምና ይህንን አብዮት በአንድ አገር ወይም በጥቂት አገራት ውስጥ መወሰን አይፈልግም፡፡ የእስልምና ዓላማ ዓለም አቀፋዊ የሆነን አብዮት ማምጣት ነው፡፡"[47]

[47] Belteshazzar& Abednego. *The Mosque and Its Role In the Society;* 2006, p. 22

ከእነዚህ ትርጉሞች እንደምንረዳው በእስልምና ውስጥ ጂሃድ በአመዛኙ የትጥቅ ትግልን የሚያመለክት መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን “ሰላማዊ” የጂሃድ ዓይነቶች ተብለው የሚጠቀሱም አሉ፡፡ የሸሪኣ ሕግ የሚከተሉትን የጂሃድ ዓይነቶች ይዘረዝራል፡- [48]

| |
|---|
| **ጂሃድ ቢል አል-ሊሳን ፡** - በምላስ/ ስብከት/ እወጃ/ ክርክር/ ውይይት ወዘተ. የሚደረግ ጂሃድ |
| **ዐ’ጂሃድ ቢል አል-ቀለም ፡** - በብዕር/ ጽሑፍ/ ሕትመት/ የመገናኛ ብዙኃን ወዘተ. የሚደረግ ጂሃድ |
| **ዐ’ጂሃድ ቢል ሒጅራ ፡** - በስደት የሚደረግ ጂሃድ፤ ወደ ውጪ አገራት ወይንም ከከተማ ወደ ከተማ የሚደረግ ሊሆን ይችላል |
| **ዐ’ጂሃድ ቢ አል-መል ፡** - በገንዘብ የሚደረግ ጂሃድ |
| **ዐ’ጂሃድ ቢ አል ነፍስ ፡** - በአንድ ሰው ማንነት (ነፍስ) ውስጥ ክፉን ለማሸነፍ በግል የሚደረግ ትግል |
| **ዐ’ጂሃድ ቢ ዐ’ ነፌስ፡** - በአንድ ሰው አካል የሚደረግ ጂሃድ፣ ራስን መሰዋት |

ከላይ የተዘረዘሩት የጂሃድ ዓይነቶች ተመጋጋቢዎች ሲሆኑ አምስቱ ጂሃዶች ለአካላዊ ጂሃድ (ቅዱስ ጦርነት ወይም ተጋድሎ) ቅድመ ዝግጅቶች ናቸው፡፡ ሌሎቹን ለጊዜው እንለፋቸውና በቀጥታ አካላዊውን ጂሃድ እንመልከት፡፡ ልዩ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ ከዚህ በኋላ “ጂሃድ” ስንል አካላዊውን የጂሃድ ዓይነት ለማመልከት ነው፡፡

[48] Ibid.

# ጂሃድ በኸሊፋዎች ዘመን

የሱኒ ሙስሊሞች “በትክክል የተመሩ” የሚሏቸውና የመሐመድን የጂሃድ ውርስ ያስቀጠሉ አራት ኸሊፋዎች ነበሩ፡፡

## አቡበክር ሲዲቅ (632-634)

የእስልምና መስረች የሆኑት መሐመድ በ632 ባልተጠበቀ ሁኔታ የህልፈታቸው ዜና እንደተሰማ[49] ከመጀመርያዎቹ ሙስሊሞች መካከል አንዱ የሆኑት አማቻቸው አቡ በከር የሙስሊሙን ኡማ የማረጋጋት ኃላፊነት በትከሻቸው ላይ ወደቀ፡፡ አቡ በከር ከመካ የስደት ዘመን ጀምሮ በታማኝነት መሐመድን የተከተሉ የልብ ወዳጃቸው ነበሩ፡፡ የመሐመድ ጨቅላ ሚስት የአይሻ አባትም ነበሩ፡፡ የመሐመድ ሞት ድንገተኛ ስለነበረና የእሳቸውን ቦታ ሊረከብ የሚችል ሰው ስላልተዘጋጀ በሕዝበ ሙስሊሙ ዘንድ ካላቸው ተሰሚነት የተነሳ አዛውንቱ አቡበከር የመጀመርያውን የኸሊፋነት ሥልጣን ተረከቡ፡፡

በሥልጣን ዘመናቸው የሚከተሉትን ጂሃዳዊ ተልዕኮዎች ፈፅመዋል፡-

- በመሐመድ የጂሃድ ሠራዊት ተገደው የሰለሙ ብዙ ሕዝቦች ከህልፈታቸው በኋላ እስልምናን በመተው ወደ ኋላ ተመልሰው ነበር፡፡ ሌሎች ደግሞ ያለፍቃዳቸው እንዲከፍሉ የተጫነባቸውን ዘካት አቋርጠው ነበር፡፡ አቡበከር እስልምናን የተውትን እነዚህን ሕዝቦች ጂሃድን በማወጅ ወደ እስልምና እንዲመለሱ አድርገዋል፡፡ ዘካትንም እንዲከፍሉ አስገድደዋቸዋል፡፡
- የእስላም ጦር ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ውጪ አገራት በመዝመት ጂሃዳዊ ወረራዎችን የፈፀመውም በአቡ በከር ዘመን ነበር፡፡ በውጤቱም ከሞላ ጎደል የክርስቲያን ግዛቶች የነበሩት ኢራቅና ሦርያ ሰልመዋል፡፡[50]

---

49 መሐመድ ሕይወታቸው ያለፈው በኸይበር ጦርነት ወቅት አንዲት አይሁዳዊት ሴት ባበላቻቸው መርዝ ምክንያት መሆኑን እስላማዊ ትውፊቶች ይጠቁማሉ፡፡ (Tabari: Volume 8, page 124)

50 Encyclopedia Britannica: www.britannica.com/biography/Abu-Bakr

## ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (634-644)

ዑመር የመሐመድ አማካሪና የቅርብ ወዳጅ የነበሩ ሲሆን የመሐመድ ሚስት የሐፍሳ አባትም ነበሩ፡፡ በአገዛዝ ዘመናቸው የሚከተሉትን ጂሃዳዊ ተግባራት ፈፅመዋል፡-

- ሠራዊት በማደራጀት በአቡበከር የተጀመረውን የጂሃድ ወረራ አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ በዚህም መሠረት ኢራቅ፣ ኢራን፣ ሦርያና ፍልስጥኤም ጠንካራ የእስላም ይዞታዎች እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡
- በእስልምና አስተዳደር ስር የወደቁትን አገራት እስልምና ብሔራዊ ኃይማኖት እንዲሆንና በሸሪአ እንዲተዳደሩ አድርገዋል፡፡
- ደቡባዊ ሕንድን በመዝለቅ እንዲሁም በምዕራብ በኩል ኑብያን (ሱዳንን) በእስልምና ቁጥጥር ስር አድርገዋል፡፡
- ሰሜን አፍሪቃን ሙሉ በሙሉ በእስልምና ቁጥጥር ስር አድርገዋል፡፡ በየአገራቱ የሸሪአ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ዳኞችን ሾመዋል፡፡
- የፖሊስ ኃይልና ወህኒ ቤቶችን አቋቁመዋል፤ ባልሰለሙት ሕዝቦች ላይ (በክርስቲያኖችና በአይሁድ ላይ) ከፍተኛ ግብር ጥለዋል፡፡
- ክርስቲያኖችና አይሁዶች ከአረብያ እንዲባረሩ አድርገዋል፡፡
- እስላማዊ የመንግሥት አስተዳደርን በየአገራቱ በመዘርጋት ከአስር ሺህ በላይ መስጊዶችንና እስላማዊ ትምህርት ቤቶችን አቋቁመዋል፡፡
- በኢየሩሳሌም መስጊድ አስገንብተዋል፡፡
- በመጨረሻም በአንድ ባርያ ተገድለዋል፡፡ ቀጣዩን ኸሊፋ እንዲመርጡ ኮሚቴ አቋቁመው የነበረ በመሆኑ በኮሚቴው ምርጫ መሠረት በኡሥማን ተተኩ፡፡[51]

---

[51] New World Encyclopedia: www.newworldencyclopedia.org/Umar_ibn_al-khattab

## ኡሥማን ኢብኑ አፋን (644-656)

ኡሥማን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ሙስሊም ስደተኞች መካከል አንዱ የነበሩ ሲሆን የመሐመድን ልጅ ሩቂያን አግብተው ነበር፡፡ ቁርአንንም መልክ ለማስያዝ ባደረጉት ጥረት ይታወቃሉ፡፡ የኡሥማን ሥልጣን ላይ መውጣት የመሐመድ አማችና የአጎታቸው ልጅ በነበሩት በአሊ ደጋፊዎች ዘንድ ቁጣን ቀስቅሶ ነበር፡፡ በዚህም ሳብያ የሥልጣን ዘመናቸውን ያሳለፉት በተቃውሞ ቢሆንም የተለያዩ ጂሃዳዊ ተግባራትን ፈፅመዋል፡-

- ባህር ኃይል በማቋቋም ብዙ አገራትን ተዋግቷል (ኢራን፣ ትንሹ ኢስያ፣ አፍጋኒስታን፣ የሶቭዬት ህብረትን የተወሰነ ክፍል፣ ሩቅ ምስራቅ አገራትን፣ እስፔንን በከፊል፣ ሰሜን አፍሪቃን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር አውለዋል)፡፡
- ቢዛንታይኖች የተነጠቋቸውን ግዛቶች ለማስመለስ ያደረጉትንም ጥረት አምክነዋል፡፡
- በመጨረሻም ኡሥማን በቤታቸው ሳሉ በተቃዋሚዎቻቸው ተገድለዋል፡፡[52]

## አሊ ኢብኑ አቡጧሊብ (656-661)

አሊ የመሐመድ የአጎት ልጅና የልጃቸው የፋጢማ ባል ነበሩ፡፡ “በትክክል የተመሩ” ከሚባሉት የሱኒ ኸሊፋዎች መካከል የመጨረሻው ሲሆኑ በሺአ ሙስሊሞች ዘንድ ደግሞ የመጀመርያው ኸሊፋ ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ የአሊ ዘመነ ሥልጣን በእርስ በርስ ጦርነትና በአመፅ የሚታወቅ ቢሆንም ሊጠቀሱ የሚችሉ ጂሃዳዊ እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡

- አሊ ከተቡክ ጦርነት በስተቀር በመሐመድ ሕይወት ዘመን በተደረጉት ጂሃዶች ሁሉ ላይ ተሳትፈዋል፡፡
- የባሕር ኃይላቸውን በመጠቀም ሕንድ ድረስ በመዝለቅ ተዋግቷል፡፡
- የተወሰኑ የአፍጋኒስታን ክልሎችንም አስልመዋል፡፡[53]

---

[52] Islamic Encyclopedia: www.islamicencyclopedia.org/public/index/topicDetail/id/1050

## ኸል-ኸዋሪጅ፤ የመጀመርያው እስላማዊ የሽብር አንጃ

የአሊ ሥልጣን መያዝ የሦርያ አስተዳዳሪ በነበሩት በሙአዊያ ዘንድ ተቃውሞን አስነስቶ ነበር፡፡ መቃቃሩ እጅግ ስለከፋ እስላማዊውን ግዛተ-መንግሥት ከጥፋት ለመታደግ ሁለቱንም መሪዎች ከሥልጣን በማስወገድ ሙስሊሞችን ሁሉ ሊያስማማ የሚችል መሪ መምረጥ እንደሚያስፈልግ በአሊ ተወካዮችና በሙአዊያ ተወካዮች ከስምምነት ላይ ስለተደረሰ ሁለቱንም መሪዎች ከሥልጣን ለማስወገድ ተስማሙ፡፡ የአሊ ተወካዮች ቃላቸውን በመጠበቅ አሊን ከሥልጣን አወረዱቻው፡፡ የሙአዊያ ተወካዮች ግን ቃላቸውን አጠፉ፡፡ ከዚህ የተነሳ የሙስሊሙ ማሕበረሰብ ለሁለት ተከፈለ፡፡ የአሊ ተከታዮች ሺኣዎች ተብለው ሲጠሩ የሙአዊያ ደግሞ ሱኒዎች ተባሉ፡፡ በዚህ መሀል የሙስሊሙን ማህበረሰብ መለያየት ያልወደደና እስልምና በነቢዩ ዘመን ከነበረው ይዘቱ መለወጡን ያመነ ኸል-ኸዋሪጅ የተሰኘ አንጃ በ657 ከሺኣ ተገንጥሎ ተቋቋመ፡፡ ይህ ቡድን ሙስሊሙን ኡማ መልሶ አንድ ለማድረግ ሁለቱንም ባላንጣ መሪዎች መግደል አስፈላጊ እንደሆነ ስላመነ አሊን ገደላቸው፡፡ ኸል-ኸዋሪጅ ዛሬ ለሚገኙት ብዙ የሽብር ቡድኖች ሞዴል ሲሆን የመጀመርያው እስላማዊ የሽብር አንጃ እንደሆነ መናገር ይቻላል፡፡[54]

## የኸል-ኸዋሪጅ እምነቶች

ኸል-ኸዋሪጅ የአረብኛ ቃል ሲሆን "የሚወጣ" እንደማለት ነው፡፡ እነዚህ ቡድኖች በሸሪኣ ሕግና በነቢዩ ሱና ከማይተዳደሩ መንግሥታት አገዛዝ ስር እንደወጡ የሚናገሩ ሲሆን ለነዚህም መንግሥታት መታዘዝ እንደማያስፈልግም ያምናሉ፡፡

---

[53] Islamic Encyclopedia: www.islamicencyclopedia.org/public/index/topicDetail/id/116

[54] Mark Gabriel. *Islama and Terrorism;* p. 83

ከሌሎች ለየት የሚያደርጓቸው አበይት አስተምህሮዎቻቸው የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከአላህ ሕግ (ከሸሪአ) ውጪ ሌላ ሕግ መኖር እደሌለበትና እንደማያስፈልግ ፅኑ እምነት አላቸው፡፡ የተወሰኑ የመሐመድ ሰሃቦችን ጨምሮ ብዙ ኢማሞችንና ሙስሊም ሊቃውንትን በከሃዲነት ይፈርጃሉ፡፡
- ሙስሊሞች ሁሉ ከቁርአን ጋር በማይስማሙ መሪዎች ላይ (ሙስሊሞች ቢሆኑም ባይሆኑም) ለሚታወጅ የጂሃድ ጥሪ ምላሽ መስጠት አለባቸው ይላሉ፡፡ በጂሃድ ውስጥ የማይሳተፍ ማንኛውም ሰው በከሃዲነት ይፈረጃል፡፡
- አዛሪቅ የተሰኙት የኸዋሪጅ ንዑስ ቡድን አባላት የከሃዲያን ሴቶችና ህፃናት መገደል እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡
- ሙስሊሞች የከሃዲያንን ሴቶች፣ ህፃናትና ንብረት ሁሉ የራሳቸው የማድረግ መብት አላቸው በማለት ያምናሉ፡፡
- እስልምናን የበላይ ለማድረግ በሚደረግ ተጋድሎ ነፍሰ ገዳይነትን፣ ክህደትን፣ አለመተማመንን እና ታማኝነት ማጉደልን የእስልምና ጠንካራ ክፍል አድርገው ይቆጥራሉ፡፡

በዚህ ስም ራሳቸውን የሚጠሩ ቡድኖች በዓለም ዙርያ እንደሚገኙ የሚታወቅ ሲሆን በአገራችንም ውስጥ በጅማ ዞን አካባቢ ለደረሱት ጥቃቶች መንግሥት እነዚህን ቡድኖች ተጠያቂ ማድረጉ የሚታወስ ነው፡፡[55]

[55] Patrick Despalta & Terje Østebø. *Muslim Ethiopia: The Christian Legacy, Identity Politics and Islamic Reformis;* 2013, p. 1

# በክርስቲያኖችና በአይሁድ ላይ የተመዘዘ ሰይፈ ጂሃድ

እስልምና ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በመጽሐፉ ሰዎች[56] ላይ የደረሰውን ሰቆቃ በነዚህ ጥቂት ገፆች ዘርዝሮ መጨረስ የማይታሰብ ነው፡፡ ታሪክን መለስ ብለን የቃኘን እንደሆነ የእስልምና ሰይፍ በክርስቲያኖችና በአይሁድ ደም የሰከረ መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡ ዛሬም ድረስ ትኩስ ደም ከሰይፉ ላይ ይንጠባጠባል፡፡

## መሐመድ በአይሁድ ላይ የፈፀሙት ግፍ

ከእስልምና በፊት ብዙ የአይሁድ ማሕበረሰቦች በአረብያ ውስጥ ለብዙ ክፍለ ዘመናት ኖረዋል፡፡ ጥንካሬያቸው ሲታሰብ በወታደራዊ ኃይል ሳይደራጁ እነዚህን ማሕበረሰቦች መጋፈጥ ጥፋትን መጋበዝ በመሆኑ መሐመድ ምቹ ጊዜ እስኪመጣ ድረስ በተቻለ መጠን እነርሱን አሳምኖ ከጀርባቸው ማሰለፍን ቀዳሚ ምርጫ አድርገው ነበር፡፡ “በመገለጦቻቸው” አሞጋግሶ ኩራት እንዲሰማቸው በማድረግ ለእስልምና ልባቸውን ማስከፈት የመጀመርያው ዘዴ ሲሆን ስለ አይሁድ ደግ ደጉን የሚናገሩት የቁርአን ክፍሎች “ወረዱ” የተባሉት በዚያን ጊዜ እንደነበር ይነገራል፡፡

> “የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬንና እኔም በዓለማት ላይ ያበለጥኳችሁ (አባቶቻችሁን በጊዜያቸው ከነበሩት ዓለማት ያበለጥኩዋቸው)[57] መኾኔን አስታውሱ፡፡” (የላም ምዕራፍ 2፡ 47)

አብርሃምን የመሳሰሉትን በአይሁድ ዘንድ ከበሬታ ያላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ስብዕናዎች ማሞጋገስ የአይሁድን ልብ ለማማለል ጥቅም ላይ የዋለ ሌላው ዘዴ ነበር (2፡124፣ 117)፡፡ በተጨማሪም የስግደት አቅጣጫ (ቂብላ) ወደ ኢየሩሳሌም

[56] የመጽሐፉ ሰዎች የሚለው ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን የሚያመለክት ቁርአናዊ አገላለፅ ነው፡፡
[57] በቅንፍ የተጨመረው በአረብኛው ንባብ ውስጥ አይገኝም

እንዲሆን ተደረገ፡፡ መሐመድም ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በሌሊት በተዓምር መሄዳቸውን የሚገልፅ ታሪክ ተወራ (17፡1)፡፡ ነገር ግን በጣት ከሚቆጠሩት በስተቀር አይሁድ መሐመድን እንደ ነቢይ ባለመቀበላቸው ምክንያት እነዚህ ሁሉ ጥረቶች መና ሆነው ቀሩ፡፡ ስለዚህ የሙገሳ መገለጡ ወደ እርግማንና ወደ ዘለፋ ተቀየረ፡-

> ከነዚያ አይሁዳውያን ከኾኑት ሰዎች ንግግሮችን ከስፍራዎቹ የሚያጣምሙ አልሉ፡፡ «ሰማንም አመጽንም የማትሰማም ስትኾን ስማ» ይላሉ፡፡ በምላሶቻቸውም ለማጣመምና ሃይማኖትንም ለመዝለፍ ራዒና ይላሉ፡፡ እነሱም «ሰማን ታዘዝንም ስማን ተመልከተንም» ባሉ ኖሮ ለነሱ መልካምና ትክክለኛ በኾነ ነበር፡፡ ግን በክህደታቸው አላህ ረገማቸው፡፡ ጥቂትንም እንጅ አያምኑም፡፡ (የሴቶች ምዕራፍ 4፡46)

ወደ ኢየሩሳሌም የነበረውም ቂብላ ወደ መካ ተመለሰ፡፡

> “ከሰዎቹ ቂሎቹ «ከዚያች በርሷ ላይ ከነበሩባት ቂብላቸው ምን አዞራቸው?» ይላሉ፤ «ምሥራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው፤ የሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል» በላቸው .... ያችንም በርሷ ላይ የነበርክባትን አቅጣጫ መልክተኛውን የሚከተለውን ሰው ወደ ክህደት ከሚመለሰው ሰው ልናውቅ (ልንገልጽ) እንጅ ቂብላ አላደረግናትም .... የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን፡፡ ወደምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን፡፡ ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር፡፡ የትም ስፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አግጣጫ አዙሩ፡፡” (የላም ምዕራፍ 2፡142-144)

ከአይሁድ ወገን የሆኑ ሰዎች በአላህ ተረግመው ወደ ዝንጀሮነትና ወደ አሳማነት[58] እንደተቀየሩ የሚናገሩ የቁርአን ጥቅሶች “ወረዱ”ተባለ (7፡166፣ 2፡65፣ 5፡60)፡፡ አይሁድንና ክርስቲያኖችን ተዋርደው ግብርን (ጂዝያ) እስኪከፍሉ ድረስ መዋጋት እንደሚያስፈልግም ተነገረ (9፡29)፡፡

[58] ፅንፈኛ ሙስሊሞች አይሁዶችን ብዙ ጊዜ “አሳማ” (ኸንዚር) በማለት ሲጠሩ መስማት የተለመደ ነው፡፡

በመሐመድ ዘመን ብዙ ጠንካራ የአይሁድ ጎሣዎች በአረብያ ይኖሩ ነበር፤ ነገር ግን በመሐመድ የተደራጀው የጂሃድ ጦር በቃላት ሊገለፅ የማይችል ግፍ ፈጽሞባቸዋል፤ ለአስከፊ ሰቆቃም ዳርጓቸዋል፡-

**በኒ ቀይኑቃዕ** - መሐመድ በበድር ጦርነት ላይ ድልን በመቀዳጀታቸው ምክንያት በሠራዊታቸው ዘንድ የነበረው ወኔ ከፍ ብሎ ነበር፡፡ በኒ ቀይኑቃዕ በመዲና ከተማ ጠረፍ ላይ የሚኖሩ የአይሁድ ጎሣ ነበሩ፡፡ ወርቅ በማንጠር ሥራ ስለሚተዳደሩ ባለጠጎች መሆናቸው አልቀረም፡፡ መሐመድ በቅርቡ በበድር ጦርነት ካሸነፏቸው ቁረይሾች ጋር አብረዋል በሚል ሰበብ ነገር ይፈልጓቸው ጀመር፡፡ በአንዲት ሙስሊም ሴትና በአንድ አይሁዳዊ ወንድ መካከል በተፈጠረ ግጭት ሌላ ሙስሊም ወንድ አይሁዳዊውን በመግደሉና አይሁድም ሙስሊሙን ሰው በመግደላቸው ምክንያት መሐመድ ሠራዊት በማዝመት አስከበቧቸው፡፡ ቀይኑቃዎች አብደላህ ቢን ኦበይ ከተሰኘ የኸዝራጅ ጎሣ መሪ ጋር ወዳጅነት ስለነበራቸው ሊታደጋቸው ሊመጣ እንደሚችል በመገመት ከበባውን ተቋቁመው ቆዩ፡፡ ነገር ግን አብደላህ በጊዜ ሊደርስላቸው ስላልቻለ ኃይላቸው ተሟጦ ተረቱ፡፡ መሐመድም እጆቻቸው ወደ ኋላ ታስረው ከምሽጋቸው እንዲወጡ አዘዙ፡፡ ለመገደልም “በእዝነቱ ነቢይ” ፊት ቀረቡ፡፡ ነገር ግን አብደላህ በአሥራ አንደኛው ሰዓት በመምጣት መሐመድን በብርቱ ስለለመናቸው ከተደገሰላቸው ጭፍጨፋ አመለጡ፡፡ ጭንቅላቶቻቸውን ከመቆረጥ ቢተርፉም ንብረታቸውን ተዘርፈው ከአገር ከመባረር ግን ሊተርፉ አልቻሉም፡፡[59]

**በኒ ናዲር** - መሐመድ ከዚህ የአይሁድ ጎሣ ጋር በሰላም ለመኖር የሰላም ውል ገብተው ነበር፡፡ ወታደራዊ ክንዳቸው ከፈረጠመ በኋላ ግን ቃል ኪዳን አፍርሰው ከመካውያን ጋር አብረዋል እንዲሁም ነቢዩን ለመግደል ከመዲና አስመሳዮች ጋር

[59] Guillaume. *The Life of Muhammad*; p. 363

አሟረዋል የሚል ምክንያት በመፍጠር ሰኔ 4 - 625 ዓ.ም. ጦራቸውን አዘመቱባቸው፡፡ ሙስሊም ጂሃዳውያንም የአይሁድን ንብረት ማጥፋትና የፍራፍሬ ተክሎቻቸውን መቁረጥ ተያያዙ፡፡ በንብረታቸው ላይ የደረሰው ውድመት ወኔያቸውን ስለሰለበ አይሁድ እጅ ከመስጠት ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም፡፡ በእስላማዊ ትውፊቶች መሠረት ከሁለት ወይም ከሦስት ሳምንታት ከበባ በኋላ ነበር የተረቱት፡፡ መሐመድ ባስቀመጡት ቅድመ ሁኔታ መሠረት የጦር መሣርያዎቻቸውን በማስረከብ ከአገር ለመሰደድ ተስማሙ፡፡ የሚወዷትን የመዲናን ከተማ በመልቀቅ ባዶ እጃቸውን እግር ወደመራቸው ሄዱ፡፡ ሙስሊም ጂሃዳውያንም ንብረታቸውን ዘረፉ፣ መሬታቸውንም ተከፋፈሉ፡፡[60]

**በኒ ቁረይዛ -** በኒ ናዲር ላይ ጥቃት በተፈፀመ ጊዜ በኒ ቁረይዛ “ከመሐመድ ጋር የሰላም ስምምነት አለን” በሚል አጉል ታማኝነት ሳይረዷቸው ቀሩ፡፡ እነሆ የእነርሱም እጣ ከሁለት ዓመታት በኋላ ደረሰ፡፡ መሐመድ 3,000 ወታደሮችና 36 ፈረሰኞችን በማስከተል ድንገት በማለዳ ተከሰቱ፡፡ ከሁለት ወይም ከሦስት ሳምንታት በኋላ በኒ ቁረይዛ እጅ ሰጡ፡፡ ሴቶችና ህፃናትን ጨምሮ ቁጥራቸው ወደ 2000 ይሆን ነበር፡፡ ወንዶቹ ከሴቶችና ከህፃናት ተለይተው እጃቻቸው ወደ ኋላ ታስሮ እንዲቀርቡ ተደረገ፡፡ “የእዝነቱ ነቢይም” ሰቆቃቸውን በመመልከት ሀሴት ያደርጉ ነበር፡፡ ከዝያም ፍርዳቸው ምን መሆን እንደሚገባው ይወስን ዘንድ ሰዓድ ኢብን ሙኣዝ የተሰኘ ሰው ዳኛ አድርገው ሾሙ፡፡ ኢብን ሙኣዝ በወቅቱ በአንድ አይሁዳዊ በተወረወረ ቀስት ቆስሎ ስለነበር ልቡ በበቀል ተሞልቶ ነበር፡፡ ይህንንም አጋጣሚ በብዙዎች ላይ የሞት ፍርድ ለመፍረድ ተጠቀመበት፡፡ ከሰባት መቶ እስከ ስምንት መቶ የሚገመቱ አይሁድ ወንዶች እጃቻቸው ታስረው ወደ መዲና የገበያ ቦታ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ ሙስሊሞች ሌሊቱን ጉድጓድ ሲቆፍሩ

---

[60] Ibid., p. 437

እነዚህ አይሁድ በጭንቀት ውስጥ ሆነው ምህረትን ይለምኑ ነበር፡፡ በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ነቢዩ ከአጃቢዎቻቸው ጋር በመምጣት ተቀመጡ፡፡ የሞት ፍርድ የተፈረደባው አይሁድም ስድስት ስድስት ሆነው ወደ ጉድጓዱ እንዲቀርቡ ተደረገ፡፡ አንገታቸውን በጉድጓዱ አፋፍ ላይ አድርገው እንዲተኙ ከተደረጉ በኋላ ሁላቸውም በሰይፍ ታረዱ፡፡[61]

**የኸይበር ወረራ** - ኸይበር በአረብ በረሃ ውስጥ የሚገኝ አካባቢ ቢሆንም በልምላሜው ይታወቅ ነበር፡፡ የብዙ ምንጮች መገኛ በመሆኑ ምክንያት ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችም በብዛት ይገኙበት ነበር፡፡ በመስከረም ወር 628 ዓ.ም. መሐመድ 1,600 የጂሃድ ሠራዊት አስከትለው ድንገት ከተፍ አሉ፡፡ አይሁድ ለየዕለት ሥራዎቻቸው ማለዳ ሲነሱ "በእዝነቱ ነቢይ" የሚመራው የጂሃድ ሠራዊት እንደ ደራሽ ውኀ ፈሰሰባቸው፡፡ ወንዶች የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ሕይወት ከዚህ ምህረት የለሽ የሰባተኛው ክፍለ ዘመን የሽብር ሠራዊት መቅሠፍት ለመታደግ  በብርቱ ቢጋደሉም ተመጣጣኝ አቅም ስላልነበራቸው ተረቱ ፡፡ መሪያቸው የነበረው ወጣቱ ኪናናም ተያዘ፡፡ መሐመድ ኪናና ባለጠጋ መሆኑን ያውቁ ነበር፡፡ በሠርጉ እለት ብዙ የወርቅ ስጦታ እንደተቀበለና ለመካ ነዋሪዎችም እንደሚያበድር መረጃ ነበራቸው፡፡ ነገር ግን የወርቁን ማስቀመጫ የት እንደደበቀ ስላላወቁ ለማውጣጣት ዙበይር የተሰኘ አጃቢያቸው እርሱንና የአጎቱን ልጅ እንዲያሰቃያቸው ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ዙበይርም በዝርግ ብረት እሳት ደረታቸው ላይ በማስቀመጥ ክፉኛ አሰቃያቸው፡፡ በመጨረሻም ንብረቱ የት እንደተደበቀ ከተናገሩ በኋላ "የእዝነቱ ነቢይ" እንዲታረዱ አዘዙ፡፡ ሁለቱም የእስላም ካራ ሰለባዎች ሆኑ፡፡ ኪናና ሳፊያ የተሰኘች መልከ መልካም ሚስት ነበረችው፡፡

[61] Ibid., p. 461

መሐመድም የ17 ዓመቷን ወጣት ሚስታቸው ትሆን ዘንድ ወሰዷት፡፡ ከሞት የተረፉትም አይሁድ የዚማ ቃል ኪዳን በመግባት ባርያዎች ተደረጉ፡፡[62]

## የዚማ ቃል ኪዳን

የኸይበር ጦርነት ሙስሊሞች እስከ ዛሬ ድረስ ከአይሁድና ከክርስቲያኖች ጋር ላላቸው ግንኙነት መሠረት የጣለ የታሪክ ክስተት ነበር፡፡ መሐመድ በኸይበር ወረራ ወቅት በሕይወት የተረፉትን አይሁድ ሃይማኖታቸውን ይዘው እንዲቆዩ የፈቀዱላቸው ቢሆንም ያንን ማድረግ ይችሉ ዘንድ አንድ ቃል ኪዳን አስገብተዋቸው ነበር፡፡ ይህ ቃል ኪዳን "የዚማ ቃልኪዳን" ወይም "የመገዛት ቃልኪዳን" በመባል ይታወቃል፡፡ "ዚማ" የሚለው ቃል "ዘማ" ከሚል የአረብኛ ግሥ የተገኘ ሲሆን "(ክፉ ጠባይን በተመለከተ) መውቀስ፣ ምስጋና መንፈግ፣ ስህተትን ፈልጎ ማግኘት፣ መገምገም፣ ማሔስ" የሚሉ ትርጉሞች አሉት፡፡ የማመስገን ተቃራኒ ነው፡፡ ዚማ ጥፋት ወይም ስህተትን ከመፈፀም የተነሳ የሚመጣ ተጠያቂነትን የሚያመለክት ሲሆን ቢፈርስ ወይም ቢጣስ ቃል ኪዳን አፍራሹን ወገን ተጠያቂ ሊያደርግ የሚችል ስምምነትን ወይም ቃል ኪዳንን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡[63] ስምምነቱን የሚፈርሙ ሰዎች ደግሞ "ዚሚ" በመባል የሚታወቁ ሲሆን የገቡትን ቃል ኪዳን እስካላፈረሱ ድረስ ሕይወታቸው በሕግ ይጠበቃል፡፡ ዚሚዎች የመጀመርያ የሚገቡት ውል ለሙስሊሞች እንደ ደም ካሳ የሚቆጠር "ጂዝያ" በመባል የሚታወቅ ግብር መክፈል ነው፡፡ ይህ ግብር የሚከፈለው ሕይወትን ለማቆየት ነው፡፡ ሙስሊሞች ግብሩን የሚቀበሉት እንደ ተጎጂ አካል በመሆን ነው፡፡ ማለትም አንድ ጂሃዳዊ ክርስቲያኑን ሲገድል የገደለውን ሰው ንብረት፣ ሚስትና ልጅ የራሱ የማድረግ

---

[62] Ibid., p. 510

[63] Mark Durie. *The Third Choice: Islam, Dhimmitude and Freedom;* 2010, pp. 122-123

ዕድል ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ካልገደለው ይህንን ጥቅም በማጣት “ተጎጂ” ስለሚሆን የጉዳት ካሳ ሊከፈለው ይገባል ማለት ነው፡፡ በሌላ አባባል ጂዝያ የሚከፈለው ሙስሊሞች ከገዛ ራሳቸው ዚሚውን እንዲጠብቁት ነው፡፡[64] የሚከተለው የቁርአን ጥቅስ ስለ ጂዝያ ክፍያ የሚናገር ነው፡-

> “ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች [አይሁድና ክርስቲያኖችን ለማመልከት ነው] እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ **የተዋረዱ ኾነው** ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው፡፡” (የንስሐ ምዕራፍ 9፡29)

መሐመድ ዚሚዎች እንዳይገደሉ አጥብቀው ከልክለዋል፡፡ ምክንያቱን ሲናገሩ ደግሞ የሙስሊሞች የገቢ ምንጭ ስለሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡[65]

በሸሪአ ሕግ መሠረት ሴቶች፣ ድኾች፣ ህሙማንና አቅመ ደካሞች ጂዝያን እንደማይከፍሉ ቢነገርም ነገር ግን ከአርመንያ፣ ከሦርያ፣ ከሰርብያና ከአይሁድ የተገኙ ምንጮች እንደሚመሰክሩት ህፃናት፣ መበለቶች፣ ወላጅ አልባዎችና ሙታን እንኳ ሳይቀሩ ጂዝያ መክፈል ይጠበቅባቸው ነበር፡፡[66] የዚሚ ማሕበረሰቦች ከጂዝያ በተጨማሪ የሚከፍሏቸው ብዙ የግብር ዓይነቶች ነበሩ፡፡ ሙስሊሞች ለንግድ ወይም ለመጓጓዣ የሚከፍሏቸው ሌሎች ቀረጦች በሙሉ ዚሚዎች በእጥፍ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ በጦርነት ምክንያት የሚወጡትን ወጪዎች ለማካካስ ሙስሊም ገዢዎች የዚሚ ማሕበረሰቦች የሚበዘብዙባቸውን

---

64 Ibid., pp. 122-125

65 Sahih al-Bukhari. The Book of *al-Jizya* the Stoppage of War. Vol. 4, Book 58, No. 3166

66 Bat Ye’or. *Islam and Dhimmitude: Where Civilization Collide*; 2002, p. 69

ስልቶች ይነድፉ ነበር፡፡ ሙስሊም ሽፍቶችና አማፅያን ደግሞ ግለሰቦችን አፍኖ በመውሰድ ወጆ (የማስለቀቂያ ክፍያ) እንዲከፈል ያስገድዱ ነበር፡፡ ብዝበዛውን መቋቋም ካለመቻላቸው የተነሳ ብዙ ክርስቲያኖች ልጆቻቸውን ለባርነት እስከመሸጥ ደርሰዋል፡፡[67]

የዚማ ቃል ኪዳን እጅግ አዋራጅና ዘግናኝ ገፅታዎች አሉት፡-

## የጂዝያ አከፋፈል ሥርዓት

- ግብር በሚከፈልበት ቀን በቆሻሻ በተሞላ ዝቅተኛ ቦታ እንዲቆሙ ይደረጋል፡፡
- ዚሚው የመጓጓዣ እንስሳትን በመጠቀም ሳይሆን በእግሩ እየሄደ ወደ ቦታው መምጣት አለበት - አንዳንድ ምንጮች በእጁና በጉልበቱ እየዳኸ መምጣት እንዳለበት ይናገራሉ፡፡
- ተቀባዩ በመቀመጥ እርሱ ግን በመቆም ክፍያውን መፈፀም ይኖርበታል፤ - ተቀባዩ ከእርሱ በላይ ከፍ ብሎ ይቀመጣል፡፡
- ዚሚው ወዲያና ወዲህ ክፉኛ ይገፈታተራል፤ እንዲፈራና እንዲርበተበትም ይደረጋል፤ ይዋረዳል፡፡
- ግብር ተቀባዩ በእጁ ላይ ጅራፍ ይይዛል፡፡
- ዚሚው ለምን እዛ እንደተገኘ የሚያውቅ ቢሆንም እንዲከፍል ቀጭን ትዕዛዝ ይሰጠዋል፡፡
- ድብደባ ይፈፀምበታል፡፡
- ሊገደል እየተወሰደ እንዳለ ምርኮኛ ልብሱን በመያዝ ወይም አንገቱ ላይ ገመድ ታስሮ በመጎተት ጎሮሮው ታንቆ ወደ ፊት እንዲደፋ ይደረጋል፡፡
- ልክ እንደሚሰየፍ ሰው ወይም እንደሚታረድ ሰው ማጅራቱ ላይ ወይም ደግሞ ጎሮሮው ላይ ይመታል (በሰይፍ የእርድ ምልክት ይደረጋል)፡፡

---

67 Ibid., p. 71

- ፀጉሩን ከግንባሩ አካባቢ እንዲቆርጥ ይታዘዛል፡፡ ይህም የሚደረገው አንገቱን ከመቆረጥ መትረፉን እንዲያስታውስ ነው፡፡
- ሌላው አንገትን የመቆረጥ ምልክት የብረት ማነቆ በአንገት ላይ ማጥለቅ ነው፡፡
- እንደሚሰየፍ ሰው ጢሙ ተይዞ ይጎተታል፡፡
- ራሱ ላይ ቆሻሻ ይጣልበታል፡፡
- ሙስሊሙ ሰው የዚሚው አንገት ላይ ይቆማል፡፡
- ከፍያውን ከፈፀመ በኋላ ከሰይፍ ማምለጡን ለማመልከት ወደ ጎን ተገፍትሮ እንዲያልፍ ይደረጋል፡፡
- የከፈሉበትን ደረሰኝ ይዘው የማይንቀሳቀሱ ወይም የጣሉ ዚሚዎች ሕይወታቸውን ለከፍተኛ አደጋ ያጋልጣሉ፡፡

## የዚሚ ግዴታዎች

- በእስልምና ስር ባለ ግዛት ውስጥ ወደ ክርስትና ወይም ወደ ይሁዲ የሚቀየር ሙስሊም ይገደላል፡፡ ሰዎች እምነታቸውን ይዘው እንዲቆዩ ተፈቅዷል ነገር ግን ወደ እስልምና ካልሆነ በስተቀር ወደ ሌላ እምነት መቀየር ክልክል ነው፡፡
- አንድን ሙስሊም እምነቱን እንዲቀይር ለማድረግ መሞከር በሞት ሊያስቀጣ የሚችልና የተከለከለ ተግባር ነው፡፡
- አንድ ዚሚ እስልምናን እንዳይቀበል እንቅፋት መሆን የተከለከለ ነው፡፡
- አንድ ሙስሊም ወንድ ክርስቲያን ወይም አይሁዳዊት ሴት ማግባት ይችላል ነገር ግን ልጆቻቸው በሸሪአ ሕግ መሠረት ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ያ ቤተሰብ የሙስሊም ቤተሰብ ነው፡፡ ዚሚ ከሙስሊም ሴት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ይህንን ተግባር መፈፀም እስከ ሞት የሚደርስ ቅጣት ያስከትላል፡፡

- ወደ እስልምና የሚቀየር ማንኛውም ሰው በቤተሰቡ ውስጥ ልዩ የውርስ መብት ይኖረዋል - የሚሰልም ወይም የምትሰልም የትዳር አጋር በፍቺ ወቅት ልጆችን የማሳደግ ልዩ መብት ታገኛለች ወይም ያገኛል፡፡
- ከወረራ በኋላ አዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መገንባት የተከለከለ ነው፡፡ ያረጁትንም ማደስ የተከለከለ ነው፡፡
- ቅዱሳት መጻሕፍቶቻቸውን በማባዛት ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡
- የዚሚ ቤቶች ከሙስሊም ቤቶች ያነሱና ዝቅ ያሉ መሆን አለባቸው፡፡ ሲወጡና ሲገቡ እንዲያጎነብሱ የቤታቸው በር ጠባብና አጭር መሆን አለበት፡፡ በጥንቷ እስፔን ውስጥ የሚገኙ አይሁድ ይኖሩባቸው የነበሩ አጫጭር ቤቶች እስከ ዛሬ ድረስ ይታያሉ፡፡
- ዚሚዎች በተለየ ሁኔታ መልበስና ከሙስሊሞች ያነሱ አልባሳትን መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ [68]
- እስላማዊ ስሞችን መጠቀም ክልክል ነው፡፡ ይህም በቀላሉ ተጋላጭ እንዲሆኑ የታለመ ነው፡፡
- ዚሚ የሚቀመጥበትን ቦታና የሚሄድበትን መንገድ ለሙስሊም ሰው የመልቀቅ ግዴታ አለበት፡፡
- ዚሚ የትህትና አቋቋም ሊኖረው ይገባል፡፡
- ዚሚ በሙስሊም ሰው ላይ እጁን ማንሳት (መምታት) በሞት ወይንም አካልን በመቆረጥ የሚያስቀጣ በጥብቅ የተከለከለ ድርጊት ነው፡፡ በምንም ምክንያት አንድን ሙስሊም መምታት የተከለከለ ነው፡፡
- ሙስሊሞችን መስደብ የተከለከለና በሞት የሚያስቀጣ ነው፡፡

---

[68] ቃዲ አሕመድ ቢን ጣሊብ (ዘጠነኛው ዓ.ም.) በአንደሉሽያ (እስፔን) አይሁዶች በትከሻው ላይ የዝንጀሮ ምልክት ያለበትና ክርስቲያኖች ደግሞ የአሳማ ምልክት ያለበትን ነጭ ልብስ እንዲለብሱ፤ እንዲሁም በበራቸው ላይ የዝንጀሮ ምልክት ያለውን ሰሌዳ እንዲለጥፉ የሚያስገድድ ትዕዛዝ ወጥቶ እንደነበር ጽፏል፡፡ Bat Ye'or. *The decline of Eastern Christianity Under Islam: from Jihad to Dhimmitude;* p. 340

- ዚሚ መሳርያ ሊኖረው ወይንም ሊይዝ አይችልም፡፡ ክርስቲያኖችና አይሁድ ራሳቸውን የሚከላከሉበት ምንም መንገድ መኖር የለበትም ማለት ነው፡፡ (ዛሬ እንኳ በአንዳንድ የሙስሊም አገራት የሚኖሩ ክርስቲያኖች መሳርያ መያዝ ስለማይፈቀድላቸው የቤተ ክርስቲያን ዘበኞች ሙስሊሞች ናቸው፡፡)
- የሙስሊም ሰው ደም ከዚሚ ሰው ደም ጋር እኩል አይደለም፡፡[69] ለምሳሌ ያህል አንድን ሙስሊም መግደል በሞት የሚያስቀጣ ቢሆንም የሸሪኣ ሕግ እንደሚናገረው ሙስሊም ያልሆነን ሰው በመግደሉ ምክንያት ማንም ሙስሊም በሞት መቀጣት የለበትም፡፡
- ዚሚ ሌላውን ዚሚ ከገደለ በኋላ ቢሰልም ከቅጣት ሊያመልጥ ይችላል፤ ወደ እስልምና የሚቀየር ማንኛውም ሰው ከሚጠብቀው የሞት ቅጣት ያመልጣል፡፡
- ክርስቲያኖችና አይሁድ ሕዝባዊ ሥልጣን ሊኖራቸው አይችልም፤ ወይንም በሥልጣን ከሙስሊሞች በላይ እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም፡፡
- ሙስሊም ባርያ ሊኖራቸው አይችልም ወይም ከሙስሊም ባርያን መግዛት አይችሉም፡፡
- በእስላማዊ ሸሪኣ ፍርድ ቤት ዚሚ በሙስሊም ላይ የሚሰጠው ምስክርነት ተቀባይነት የለውም፡፡
- አንድ ሙስሊም ከፍተኛ ቅጣት በሚያስከትል ክስ አንድን ክርስቲያን ቢከስ የክርስቲያኑ ምስክርነት ራሱን ለመከላከል የሚበቃና ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አንድ ሙስሊም ወንድ ክርስቲያን ሴት ቢደፍር ቃሏ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
- ዚሚዎች ሙስሊም ወታደሮችን የማስጠለልና የመመገብ ግዴታ አለባቸው፡፡ በስምምነቱ መሠረት ጂሃድን ሊደግፉ ይገባል፡፡

---

[69] ሳዑዲ አረብያ የሁሉንም ዓይነት ሰው ዘር ደም ዋጋ የሚያሳይ ዝርዝር አላት፤ ሙስሊም ወንድ ከሁሉ የላቀ ዋጋ አለው፣ ከዚያ ሙስሊም ሴት፣ ክርስቲያን ወንድ፣ ክርስቲያን ሴት፣ አይሁድ ወንድ፣ አይሁድ ሴት፣ ሒንዱ ወንድ፣ ሒንዱ ሴት እያለ የደረጃ ምድብ ዝርዝሩ ይቀጥላል፡፡ https://en.wikipedia.org/wiki/Diyya

- ዚሚዎች ከሙስሊም ጠላቶች ጋር መወዳጀት፣ እነርሱን መርዳትም ሆነ ከእነርሱ እርዳታን መቀበል የተከለከለ ነው፡፡
- ዚሚዎች በእስልምና ቁጥጥር ስር ካለ አካባቢ ለቆ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡
- ዚሚዎች በአደባባይ እምነታቸውን በምንም ዓይነት መንገድ እንዲያንፀባርቁ አይፈቀድም፡፡ መስቀል ማሳየት አይችሉም፡፡ በሃይማኖታቸው መሠረት የቀብር ስርአት መፈፀም አይችሉም፡፡ ደወል ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው መዘመርም ሆነ ማስተማር አይችሉም፡፡[70]
- ዚሚዎች ልጆቻቸውን ስለ እስልምና ከማስተማር ተከልክለዋል፡፡ በሥርአቱ ስር ተጨቁኖ መሠቃየት እንጂ የሥርአቱን ምንነት ማወቅ የተከለከለ ነው፡፡
- እስልምናን፣ መሐመድንና የዚማን ሥርአት መተቸት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡
- ዚሚዎች ፈረስ እንዳይቀመጡ ተከልክለዋል ምክንያቱም በደረጃ ከሙስሊሞች በላይ ከፍ ያደርጋቸዋልና፡፡
- አህያ እንዲቀመጡ የሚፈቀድላቸው ሲሆን እግራቸውን በማንፈራጠጥ እንስሳው ላይ መቀመጥ አይችሉም፡፡ ሁለቱም እግሮቻቸው ወደ አንድ አቅጣጫ ዞረው በጎን መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- በብዙ ቦታዎች ዚሚዎች ከሌላው እንዲለዩ በልብሳቸው ላይ የተለየ የቀለም ምልክት እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸው ነበር፡፡
- በብዙ ቦታዎች አንድ ዓይነት ጫማ እንዲጫሙ አይፈቀድላቸውም ነበር፡፡
- በሕዝባዊ መታጠብያ ቦታዎች ከሙስሊም ተለይተው እንዲታወቁ የአንገት ማነቆዎችን ወይም ቃጭሎችን እንዲያጠልቁ ይገደዱ ነበር፡፡

---

[70] ለዚህ ነው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ተነሱትን የኢየሩሳሌምን ፎቶግራፎች ስንመለከት በአንድም ቤተ ክርስቲያን ላይ የመስቀል ምልክት ማግኘት የማይቻለው፡፡

- በተለያዩ አካባቢዎች የዚሚን ማሕበረሰቦች የሚያዋርዱ የተለያዩ ተግባራት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል የሞሮኮ አይሁድ የቆሻሻ መጣያዎችን እንዲያፀዱ፣ የሞቱ እንስሳትን እንዲያነሱና የሞት ፍርድ በተፈፀመባቸው ወንጀለኞች ጭንቅላት ላይ ጨው እንዲነሰንሱ ይገደዱ ነበር፡፡
- ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ርኩሶች እንደሆኑ ከሚናገረው የቁርአን ቃል በመነሳት (9፡28) በ19ኛው ክፍለ ዘመን በሐመዳን (ኢራን አገር) ይኖሩ የነበሩ አይሁድ በበረዶና በዝናባማ ቀን ከቤት እንዳይወጡ ይከለከሉ ነበር፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ሰውነታቸውን የነካ እርጥበት ኋላ ላይ የሙስሊሞችን እግር በመንካት እንዳያረክሳቸው በሚል ነበር፡፡

በዚህ ኢ-ሰብዓዊ ሕግ መሠረት ከዚሚ ማህበረሰብ መካከል አንድ ሰው የገባውን ቃል ኪዳን በማፍረስ አንዱን ሕግ እንኳ ተላልፎ ቢገኝ ሙስሊሞች መላውን የዚሚ ማሕበረሰብ የመቅጣትና የመግደል መብት አላቸው፡፡ በእስላማዊ አነጋገር ደማቸው ሐላል (የተፈቀደ) ይሆናል ማለት ነው፡፡ ግብሩ እጅግ አስጨናቂ ከመሆኑ የተነሳ አእምሯቸውን የሳቱ፣ መድረሻቸውን ሳያውቁ ጠፍተው በመንከራተት የሞቱ ብዙ ክርስቲያኖችና አይሁድ መኖራቸውን ታሪክ ዘግቧል፡፡[71]

የ18ኛው ክፍለ ዘመን ሞሮኮዋዊ ሐታች የነበረው ኢብን አጂባህ ሱራ 9፡29 ላይ አስተያየት ሲሰጥ እንዲህ አለ፡-

> “ዚሚው ነፍሱን፣ መሻቱንና መልካም ዕድሎቹን ሁሉ በገዛ ፈቃዱ እንዲገድል ይታዘዛል፡፡ ከሁሉም በላይ ለሕይወት፣ ለሥልጣንና ለክብር ያለውን ፍቅር መግደል ይኖርበታል፡፡ ዚሚው የነፍሱን ጥማት መለወጥ አለበት፤ ሙሉ በሙሉ እስኪገዛ ድረስ ነፍሱን መሸከም ከምትችለው በላይ ማስጨነቅ አለበት፡፡ ከዚያ በኋላ መሸከም የማይችለው ነገር

---

71 እነዚህ መረጃዎች የተወሰዱት፡- Mark Durie. *The Third Choice: Islam, Dhimmitude and Freedom;* pp. 131-153 እንዲሁም Bat Ye'or. *Islam and Dhimmitue: Where Civilization Collide;* 2002, pp. 50-110 ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም በባት ዬኦር የተመሠረተውን www.dhimmitude.org በመጎብኘት መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡

አይኖርም፡፡ ለጭቆናና ለኃይል ጥቃት ግዴለሽ ይሆናል፡፡ ድህነት እና ኃብት ለእርሱ አንድ ይሆናሉ፤ ሙገሳና ንቀት አንድ ይሆኑበታል፤ መከልከልና መስጠት አንድ ይሆኑበታል፤ ማግኘትና ማጣት አንድ ይሆኑበታል፡፡ ስለዚህ ሁሉም ነገር አንድ ሲሆንበት ፍፁም በሆነ መገዛት ከእርሱ የሚፈለገውን ነገር ማቅረብ ይችላል፡፡"[72]

ኢብን ከሢር በመጽሐፉ ውስጥ እንዲህ በማለት አስፍሯል፡-

"አላህ በቁርአኑ ‹የተዋረዱ ሆነው ጂዝያን እስኪከፍሉ ድረስ ተጋደሏቸው› ብሏል፡፡ ሙስሊሞች የዚማን ሕዝቦች ማክበር ወይንም ከሙስሊሞች በላይ ከፍ ማድረግ አልተፈቀደላቸውም፤ ምክንያቱም እነርሱ ዕድለ ቢሶች፣ ቆሌያቸው የተገፈፈና ወራዶች ናቸውና፡፡ ሙስሊም የተሰኘው ዘጋቢ ከአቡ ሁራይራ ሰምቶ እንዳስተላለፈው ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- ‹አይሁድን ወይንም ክርስቲያኖችን ሰላም አትበሏቸው፤ ማናቸውንም በመንገድ ላይ ብታገኙ ወደ ጠባቡ የመንገዱ ጠርዝ ግፏቸው፡፡› ለዚህ ነው የታማኞች መሪ የነበረው ኡመር አል ከታብ (አላህ ይውደደውና) ሁላችንም የምናውቃቸውን ቅድመ ሁኔታዎቹን ክርስቲያኖች እንዲቀበሉ የጠየቀው፡፡ እነዚህም ቅድመ ሁኔታዎች ውርደታቸው፣ ቅለታቸውና እፍረታቸው ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ ለማድረግ የታለሙ ናቸው፡፡" [73]

ይህ አስጨናቂ ሕግ አውሮፓውያን የሙስሊም አገራትን በቅኝ ገዢነት እስከያዙበት ዘመን ድረስ ቀጥሎ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በብዙ ሙስሊም አገራት ውስጥ በተወሰነ መልኩ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ሦርያ፣ ግብፅ ኢራንና ኢራቅን በመሳሰሉት የአረብ አገራት ውስጥ እየኖሩ የሚገኙት ክርስቲያኖችና አይሁድ እነዚህን ኢ-ሰብዓዊ ሕግጋት ተቋቁመው ያለፉ ናቸው፡፡

---

[72] Durie. *The Third Choic;* p. 140-141

[73] Tafsir Ibn Kathir, vol. 4:406-7; Quoted in:- Durie. *The Third Choic;* p. 142

# ጥንታዊ የክርስቲያን ማዕከላትን መውረር

በመሐመድ ዘመን በአረብያ የነበሩት ክርስቲያን ማህበረሰቦች ቁጥራቸው አናሳ ስለነበረ እንደ አይሁድ ለአዲሱ እስላማዊ ማሕበረሰብ "ስጋት" ሊፈጥሩ የሚችሉ አልነበሩም፡፡ ነገር ግን መሐመድ ዙርያው በክርስቲያን ማሕበረሰቦች እንደተከበበ ያውቁ ነበር፡፡ እነዚህ አገራት እንዲሰልሙ ወደየመሪዎቻቸው ደብዳቤዎችንም ይጽፉ ነበር፡፡ የመሐመድን ደብዳቤዎች ከተቀበሉት ክርስቲያን ነገሥታት መካከል የአክሱም ንጉሥ ይገኝበታል፡፡ በሙስሊሞች የተጻፉት ታሪኮች እንደሚናገሩት "አል-ነጃሺ" የተሰኘ የአክሱም ንጉሥ እንደ ሙስሊም የተቆጠረ ሲሆን ከእርሱ ቀጥሎ የነገሠው ንጉሥ እንዲሁ ወደ እስልምና እንዲመጣ ግብዣ የሚያቀርብ በማስፈራርያ የሚደመደም ደብዳቤ ከመሐመድ ደርሶታል፡፡[74]

ከመሐመድ ሞት በኋላ ወዲያውኑ ነበር የጂሃድ ሠራዊት የክርስቲያን አካባቢዎችን መውረር የጀመረው፡፡ በዘመኑ ዋና ዋና የሚባሉትን የክርስቲያን ማዕከላትንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በመቆጣጠር በሰይፍ ስለት አሰለመ፡፡ ደማስቆ በ635 በጂሃድ ሠራዊት እጅ ወደቀች፡፡ አንፆኪያ በ636 ተያዘች፡፡ ኢየሩሳሌም በተያዘች በሁለት ዓመታት ውስጥ ደግሞ ቂሣርያ ከረጅም ጊዜ ከበባ በኋላ በሙአዊያና በወንድሙ ለሚመራው የጂሃድ ጦር እጅ ሰጠች፡፡ በ640 በሦርያ የነበሩት ክርስቲያኖች በአረብ ሙስሊሞች ምድራቸውን ተነጠቁ፡፡ በ641 ፋርስና ግብፅ ለጂሃድ ሠራዊት እጅ ሰጡ፡፡ ከ649-668 ቆጵሮስ፣ ሮዴስና ቀርጤስን የመሳሰሉት የክርስቲያኖች መኖርያ የነበሩት ደሴቶች በእስላም ጦር ተያዙ፡፡ መሐመድ በሞቱ በዘጠኝ ዓመታት ውስጥ በዘመኑ የሚታወቁት የክርስቲያን ማዕከላት የጂሃዳውያን ሰለባ ሆኑ፡፡ ሙስሊም ጂሃዳውያን በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪቃ የነበሩትን የክርስቲያን አገራት ከተቆጣጠሩ በኋላ

---

[74] ሙሐመድ ጦይብ፡፡ *ኢትዮጵያና ኢስላም፣* በኢድሪስ ሙሐመድ የተተረጎመ፤ 1999፣ ገፅ 102-103

በቀጥታ ወደ ቁስጥንጢንያ ነበር የዘመቱት፡፡ በ668 ዓ.ም.[75] ከሦርያ የተንቀሳቀሰው የጂሃድ ጦር ከተማይቱን ለስድስት ዓመታት የከበባት ሲሆን ሳይሳካለት ተመልሷል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቢዛንታውያን ይጠቀሙት የነበረ የፈላ ፈሳሽ እንደነበር ይነገራል፡፡[76] በመጨረሻም በ1453 በኦቶማን ቱርኮች እጅ ወድቃለች፡፡ ስሟም ተቀይሮ ኢስታንቡል ተብሏል፡፡ ውብ የሆነውም የሶፍያ ቤተ ክርስቲያን መስጊድ የተደረገ ሲሆን በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመርያ ላይ ወደ ሙዚየምነት ተቀይሯል፡፡



በቱርክ ጂሃዳውያን ወደ መስጊድነት የተቀየረው በኢስታንቡል የሚገኘው የሶፍያ ቤተ ክርስቲያን፡፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በዚህ መልኩ ወደ መስጊድነት ተቀይረዋል፡፡ ይህ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት ሙዚየም ሆኗል፡፡

---

75 ትክክለኛውን ዓመት በተመለከተ የተለያዩ ጸሐፊያን የተለያዩ ዓመታትን ያስቀምጣሉ፡፡

76 Fregosi. *Jihad;* pp. 71-86

# የመስቀል ጦርነቶች (ክሩሴዶች)



ሰማዕቱ ፐርፌክቶስ ስለ ኢየሱስና ስለመሐመድ ማንነት በተጠየቀ ጊዜ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እና አዳኛችን መሆኑን ነገር ግን መሐመድ እውነተኛ ነቢይ አለመሆኑን በመናገሩ ምክንያት ሚያዝያ 18/ 850 ዓ.ም. በዚህ መልኩ ተገደለ፡፡

የመስቀል ጦርነቶችን ትክክለኛ መነሻና አውድ ለማወቅ ከጦርነቶቹ በፊት የተፈፀሙትን ታሪኮች ወደ ኋላ መለስ ብሎ መቃኘት ያስፈልጋል፡፡

ጂሃዳውያን በምስራቅ የሚገኙትን የክርስቲያን አገራት ከወረሩ በኋላ መላውን አውሮፓ በማስለም ክርስትናን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት በቀጥታ ወደ ምዕራብ ነበር የዘመቱት፡፡ በዚህም መነሻ በ711 ዓ.ም. ጣሪቅ ኢብን ዚያድ የተሰኘ ጂሃዳዊ 7,000 የሚሆን ሠራዊት በማስከተል ከሰሜን አፍሪቃ ወደ እስፔን ተሻገረ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይህ ቁጥር ወደ 12,000 በማደግ ተጠናከረ፡፡ ሮዴሪክ የተሰኘ የወቅቱ የእስፔን መሪ 25,000 ሠራዊት አስከትሎ ሊገጥመው የወጣ ቢሆንም ይህ መሪ ዊቲዛ በተባለ ንጉሥ ላይ መፈንቅለ መንግሥት በመፈፀም ወደ ሥልጣን የመጣ ስለነበረ በሕዝቡ ዘንድ የሚወደድ አልነበረም፤ ከዚህም የተነሳ የወታደሮቹ የመዋጋት ፍቃደኝነት ያን ያህል ነበር፡፡ የዊቲዛ ወንድም የነበሩት ጳጳሱ ኦፓስ ለጂሃዳውያኑ በመወገናቸው ምክንያትና ሌላውም ነገር ተደማምሮ የጂሃድ ጦር ድል ነሳ፡፡ የክርስቲያን ምድር የሆነችው እስፔንም በእስላማዊ አገዛዝ ስር ወደቀች፡፡[77]

[77] Anwar Shaikh. *Islam and Terrorism;* 2004, pp. 167-173

እስልምና እስፔንን በገዛባቸው ክፍለ ዘመናት ብዙ ግፎች በክርስቲያኖች ላይ ተፈፅመዋል፡፡ በተለይ አል-ኀኪም የተሰኘ የኡመያድ ሥረወ መንግሥት ኤሚር (796-822) እጅግ ጨካኝ ሰው ነበር፡፡ ቶሌዶ በተባለ ቦታ ወደ እስልምና ተቀይረው የነበሩ ክርስቲያኖች እንኳ ከጭፍጨፋ ሊተርፉ አልቻሉም ነበር፡፡ በአንድ ቀን ወደ 5,000 የሚሆኑ ሰዎች አንገታቸውን መቀላታቸው ተዘግቧል፡፡ ይህም በእስፔን ታሪክ "የጉድጓድ ቀን" በመባል ይታወቃል፡፡ በኮርዶባ ሙስሊም ጂሃዳውያን የምግብ ዋጋ በማስወደዳቸው ምክንያት ሰላማዊ ሰልፍ የጠሩ መሪዎች እንዲሰቀሉ ተደርጓል፡፡ በበነጋው ስቅላቱን ለመቃወም የወጡ 300 ሰዎች ተሰቅለዋል፡፡ በዚያን ዘመን በመስቀል ላይ የበሰበሱ አስከሬኖችን በየመንገዱ ማየት የተለመደ ነበር፡፡ ከሮማውያን የስደት ዘመን ቀጥሎ በአውሮፓ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሰማዕታት የበዙበት እንደዚያ ያለ ዘመን አልነበረም፡፡ ፍሎራና ማርያም የተሰኙ ሁለት ሴቶች በታሪክ ሲታወሱ ከሚኖሩት የእስፔን ሰማዕታት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ ካህናቱ ፐርፌክቶስና ኢሎጊዎስ እንዲሁም አሥራ አንዱ የኮርዶባ ሰማዕታትም ከብዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡[78]

የጂሃድ ጦር ወደ ኢጣሊያ በመሻገር ከ827-902 በሲሲሊ ላይ የማያቋርጥ ጥቃት ፈፅሟል፡፡ በነዚያ ዘመናት ጂሃዳውያን ለመስማት የሚዘገንን ብዙ ግፍ በክርስቲያኖች ላይ ፈፅመዋል፡፡ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን ያረክሱ ነበር፡፡ ሕዝበ ክርስቲያኑን ይጨፈጭፉ፣ ያዋርዱና ንብረቱን ይዘርፉ ነበር፡፡ ኤድዋርድ ጊቦን የተባለ ጸሐፊ ታሪክ እንደዘገበው በሴሌርኖ ከበባ ጊዜ የጂሃዱ መሪ የቅዱስ ቁርባን ማስቀመጫ በሆነው በመቅደሱ ውስጥ በሚገኘው መሰዊያ ላይ መደረቢያውን በማንጠፍ በምንኩስና ይኖሩ የነበሩትን የገዳሙን ደናግላን አንድ

[78] Fregosi. *Jihad;* pp. 1126-129

በአንድ እያመጣ ድንግልናቸውን ይገስስ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የመቅደሱ ጣርያ ድንገት ተደርምሶ ጭንቅላቱ ላይ በመውደቅ ዘማዊውን ጂሃዳዊ ገድሎታል፡፡[79]

ጂሃዳውያኑ የክርስቲያን ማዕከላት የነበሩትን ሮምንና ቁስጥንጢንያን ለመቆጣጠር ወደፊት ገሠገሡ፡፡ በ846 ሮም ከተማ በመግባት የቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስን አብያተ ክርስቲያናት ዘረፉ፡፡ ጳጳሱም በዓመት 25,000 የብር ሳንቲሞችን ለመክፈል ቃል ስለገቡ ወራሪዎቹ ተመለሱ፡፡ ጳጳሱ ሊዮን አራተኛ የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያን ከጥቃት ለመከላከል "የሊዮን ግንብ" በመባል የሚታወቀውን ቅጥር አስገነቡ፡፡ ነገር ግን የሚሸነፍ የማይመስለው የጂሃድ ሠራዊት መላውን አውሮፓ ለመቆጣጠር ያደረገው ጥረት ቱርስ በተባለ ቦታ ላይ ተገታ፡፡ አረቦች በፈረንሳዮች እጅ የሽንፈት ፅዋቸውን ተጎነጩ፡፡ አውሮፓም ለእስልምና ከመንበርከክ ተረፈች፡፡[80]

ክሩሴዶች ወይም የመስቀል ጦርነቶች ተብለው የሚታወቁት ጦርነቶች በዚህ ሁኔታ መላውን የክርስቲያን ዓለም ለማጥፋት የተነሳውን ጂሃድ ለመቋቋም በ 1095-1291 ዓ.ም. መካከል የተደረጉ ነበሩ፡፡ በነዚያ 200 ዓመታት ውስጥ ባጠቃላይ ወደ 10 ክሩሴዱች ተደርገዋል፡፡ ጦርነቶቹን ያወጁት የፈረንሳይ ጳጳስ የነበሩት ዳግማዊ አርባን ነበሩ፡፡ አውሮፓውያን ክርስቲያኖች በመጀመርያው ክሩሴድ እስከ መካከለኛው ምስራቅ በመዝለቅ ኢየሩሳሌምን ከሙስሊሞች እጅ የነጠቁ ሲሆን ሦርያና ፍልስጥኤምን በግዛቶች በመከፋፈል ማስተዳደር ጀምረው ነበር፡፡ ነገር ግን ኋላ ላይ ተሸንፈው ለቀው ወጥተዋል፡፡[81]

---

[79] Edward Gibbon. *Decline and Fall of Roman Empire;* Vol. 5, chap. 46, quoted in Paul Fregosi. *Jihad in the West;* 1998, p. 133
[80]. Ibid. 116-121
[81] Campo. *Encyclopedia of Islam;* p. 175

የክሩሴድ ጦርነቶች የአውሮፓ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ከሠራቻቸው ትልልቅ ስህተቶች መካከል በግንባር ቀደምትነት ቢጠቀሱም ለጦርነቶቹ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑት የሙስሊም ወራሪ ኃይላት እንጂ ክርስቲያኖች አለመሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ዛሬ እስልምና ተጎናዝሎ የተቀመጠባቸው የመካከለኛው ምስራቅና የሰሜን አፍሪቃ አገራት የክርስቲያን አገራት የነበሩና በእስላም ወራሪ ኃይላት ተደምስሰው የክርስትና ታሪካቸው እንዲጠፋ የተደረጉ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዛሬም ድረስ የሚታዩት ጥንታውያን የአብያተ ክርስቲያናት ፍርስራሾችና ከብዙ የግፍ ሥራዎች በእግዚአብሔር ተዓምር ተርፈው ክርስትናቸውን ጠብቀው የሚገኙት ቅሬታዎች ምስክሮች ናቸው፡፡ ሙስሊሞች እነዚህን አገራት ያሰለሙት በሰይፋቸው እንጂ በመጽሐፋቸው ፈፅሞ አልነበረም፡፡ እስፔን ድረስ በመዝለቅ ጎሮሯቸው ላይ ሰይፉን ያስቀመጠውን ይህንን እስላማዊ የጂሃድ ወረራ ለመቋቋምና ልክ እንደ ዛሬዎቹ የአይኤስና የአልቃኢዳ አሸባሪዎች ጨካኞች በነበሩት ጂሃዳውያን እጅ ለወደቁት የመካከለኛው ምስራቅ ክርስቲያን ወንድሞቻቸው የድረሱልን ጥሪ ጩኸት ምላሽ ለመስጠት የነበራቸው አማራጭ ኃይልን መጠቀም እንደነበረ ስለተሰማቸው የአውሮፓ ክርስቲያኖች የጦርነት ዘመቻዎችን በማድረግ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን ክርስቲያኖች በዚያ የታሪክ አጋጣሚ የተፈጠረውን ስህተት ሲያስቡ ዛሬም ድረስ ይፀፀታሉ፡፡ የአውሮፓ ቤተ ክርስቲያንም በተደጋጋሚ ይቅርታ ጠይቃለች፡፡ ሙስሊም አገራት ግን አንድም ጊዜ ለይቅርታ ጥያቄው ዕውቅና ሰጥተው አያውቁም፡፡ የክርስቲያኖች የይቅርታ ጥያቄ የመነጨው ሰይፍን መጠቀም ከክርስቶስ ትምህርት ጋር የሚጣረስ መሆኑን ከማመን እንጂ እነርሱ የፈፀሙት ራስን የመከላከል የአልሞት ባይ ተጋዳይ ትንቅንቅ ጂሃዳውያን ከ7ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በክርስቲያኖች ላይ ከፈፀሙት በደልና ግፍ ጋር የሚነፃፀር ሆኖ አይደለም፡፡ ቢሆንም ግን ሰይፍን በሰይፍ መመለስ የክርስቶስ ትምህርትና ኑሮ ባለመሆኑ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

ካህናትና ተከታዩ ሕዝብ እንደዚያ ዓይነት ውድቀት ውስጥ መግባታቸው ስህተት ነበር፡፡

ክሩሴዶች እስከ ዛሬ ድረስ በምዕራብና በሙስሊም አገራት መካከል ላለው ግንኙነት ተምሳሌት ሆነው ቀጥለዋል፡፡ ሙስሊሞች በክሩሴድ ዘመን በገዛ አገሮቻቸው በሰላም ሲኖሩ እንደነበርና ያለ ምንም ምክንያት በክርስቲያኖች ወረራ እንደተፈፀመባቸው በማስመሰል ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ማለትም በክርስቲያኖችና በመሰብሰቢያ ቤቶቻቸው ላይ ለሚፈፅሟቸው ጥቃቶችም እንደ ማፅደቅያ ይጠቀሙታል፡፡

## የከሸፉ ጂሃዶች

ጂሃዳውያን የክርስቲያን ማዕከላትን በመውረር የተሳካላቸውን ያህል ክሽፈቶችንም አስተናግደዋል፡፡ በተለይም የቱርስና የቪዬና ጦርነቶች ወርቃማ ዕድሎችን እንዳጡ በማሰብ በእጅጉ የሚቆጩባቸው የታሪክ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡

### የቱርስ (የፖይቲርስ) ጦርነት

ቱርስ በፈረንሳይ ውስጥ የምትገኝ ታሪካዊ ቦታ ናት፡፡ ጦርነቱ የተደረገው ከእስፔን ወደ ምዕራብ አውሮፓ በተሻገሩ አረብ ወራሪዎችና በፈረንሳይ ክርስቲያኖች መካከል ነበር፡፡ የኡመያድ ካሊፌት ጦር አብዱልረህማን አል ጋፊቅ በተሰኘ የአል-አንደሉሺያ (እስፔን) ኤሚር የተመራ ሲሆን የፈረንሳይ ሠራዊት ደግሞ ቻርልስ ማርቴል[82] በተሰኘ መኮንን ነበር፡፡ ሁለቱ ሠራዊቶች ሰኔ 10/ 732 ዓ.ም. በመግጠም እልህ አስጨራሽ ፍልሚያ አድርገዋል፡፡ በዚህ ጦርነት አብዱልረህማን

82 ‹ማርቴል› ‹መዶሻ› ማለት ሲሆን በጂሃዳውያን ላይ በተቀዳጀው ድል ምክንያት የተሰጠው ቅፅል ስም ነው፡፡

የተገደለ ሲሆን በእርሱ የተመራው የአረብ ወራሪ ኃይል ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት በመሸነፍ አፈግፍጓል፡፡ ከዚያ በኋላ የእስላም ጦር መላውን አውሮፓ ለማስለም ያንን በሚያህል ግዙፍ ሠራዊት ወረራ ለመፈጸም 700 ዓመታት ያህል መጠበቅ ነበረበት፡፡[83]

## የቪዬና ከበባ

ከነበራት እስትራቴጂያዊ አቀማመጥ የተነሳ የኦስትሪያ ዋና ከተማ የሆነችውን ቪዬናን መያዝ የኦቶማን ቱርኮች የረጅም ጊዜ ህልም ነበር፡፡ ኦቶማኖች የሮማ ምስራቃዊ ግዛተ መንግሥት የነበረውን ቢዛንታይንን በመውረር ቁስጥንጢንያን ከያዙ በኋላ ግሪክ፣ ቡልጋርያ፣ ሩማንያና ሰርቢያን የመሳሰሉትን የምስራቅ አውሮፓ አገራት በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ ተሳክቶላቸዋል፡፡ መላውን አውሮፓ የማስለም ህልማቸውን እውን ለማድረግ በኦስትሪያ ላይ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን በመፈፀም በ1529 ቪዬናን የከበቡ ቢሆንም ሳይሳካላቸው በመቅረቱ እንደገና ተጠናክረው በመምጣት በ1683 ወረራ ፈፅመዋል፡፡ በዚህ ወረራ ወቅት በመንገዳቸው ላይ ብዙ ከተሞችንና መንደሮችን አጥፍተዋል፤ ብዙ ክርስቲያኖችንም ማርከዋል፡፡ የኦስትሪያ ንጉሥ የነበረው ሊኦፖልድ 11,000 ወታደሮችና 5,000 ፈቃደኛ ዜጎችን በማስተባበር ከተማይቱ እንዳትያዝ ቢፋለምም የእርሱ አቅም በቱርካዊው የጦር መኮንን ካራ ሙስጠፋ ፓሻ ከሚመራው 150,000 የእስላም ሠራዊት ጋር የሚመጣጠን አልነበረም፡፡ የፖላንድ ንጉሥ የነበረው ሣልሳዊ ጆን ሶቢዬስኪ 30,000 ወታደሮችን በማስከተል ባይደርስ ኖሮ የከተማይቱ መያዝ እርግጥ ነበር፡፡ ከፖላንዶች በተጨማሪ በዚህ ጦርነት ላይ 18,500 የኦስትሪያ ወታደሮች፣ 9,000 የሳክሰን ወታደሮችና 19,000 የፈረንሳይ፣ የሱዋቢያኖችና የባራቪያኖች ቅይጥ የሆኑ ወታደሮች ተሳትፈዋል፡፡

[83] Encyclopedia Britannica www.britannica.com/event/Battle-of-Tours

ሶቢዬስኪ ከፍተኛ ወታደራዊ ብቃቱን በመጠቀም እነዚህን ሠራዊቶች ካቀናጀ በኋላ መስከረም 12፣ 1683 በቱርኮች ላይ ጥቃት ከፈተ፡፡ 12 ሰዓታት ያህል በፈጀው በዚህ ወሳኝ ፍልሚያ የቱርኮች ኃይል ተሰበረ፡፡ ሽንፈቱን የተረዳው የእስላም ጦርም በእጁ በሚገኙት ምርኮኞች ላይ ጭፍጨፋ ከፈፀመ በኋላ ብዙ ንብረት በመጣል ሕይወቱን ለማትረፍ ሸሸ፡፡ በሽንፈታቸው ከፍተኛ ብስጭትና እፍረት ውስጥ የገቡት ቱርኮች ካራ ሙስጠፋ ፓሻን ተጠያቂ በማድረግ ጥቅምት 25፣ 1683 ቤልግሬድ ውስጥ በዘግናኝ ሁኔታ በሞት ቀጥተውታል፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ የጂሃድ ጦር በዚያ መልኩ ወረራ ለመፈፀም ዳግመኛ ወደ ምዕራብ አውሮፓ አልተመለሰም፡፡[84]

አረቦችና ቱርኮች እነዚያን ጦርነቶች ድል አድርገው ቢሆን ኖሮ መላውን የምዕራብ ዓለም የማስለም ዕድል ይኖራቸው ስለነበር አላህ በቁርአን ውስጥ እስልምናን ከሃይማኖቶች ሁሉ የበላይ ሊያደርግ የገባው ቃል እውን በሆነ ነበር (ሱራ 9፡33)፡፡ ነገር ግን ይህ ተስፋ አሁንም ድረስ ተስፋ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

[84] Ibid., www.britannica.com/event/Siege-of-Vienna-1683

2

# ጂሃድ በአዲስ መልክ

አሥራ ስምንተኛው ክፍለዘመን የመካከለኛው ምስራቅ ሥልጣኔ በመክሰም የምዕራባውያን ሥልጣኔ ከፍ ብሎ የታየበት ነበር፡፡ ናፖሊዮን ቦናፓርት በ1798 ሠላሳ አምስት ሺህ ወታደሮቹን ግብፅ ላይ ማሥፈሩ የኃይል ሚዛኑ መለወጡን በግልፅ ያመለከተ የታሪክ አጋጣሚ ነበር፡፡ በአሥራ ዘጠነኛውና በሃያኛው ክፍለ ዘመን የነበረው የአውሮፓውያን የመስፋፋት ፖሊሲ የዓለምን የኃይል ሚዛን ስለለወጠው የሙስሊሙ ዓለም ከገዢነት ወደ ተገዢነት ለማሽቆልቆል ተገደደ፡፡ በኦቶማን ቱርኮች በክርስቲያኖች ላይ ይደረጉ የነበሩት የማጥቃት ዘመቻዎችም ወደ ውጪ ከመሆን ይልቅ በግዛተ መንግሥቱ ውስጥ በነበሩት የክርስቲያን ማሕበረሰቦች ላይ ያነጣጠሩ ሆኑ፡፡ የኦቶማን ግዛተ መንግሥትም ከመፈራረሱ በፊት ማሳረጊያውን የብዙ ክርስቲያኖችን ደም በማፍሰስ አደረገ፡፡

## የነፃነት መዘዝ

ከአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ብሪቴንና ፈረንሳይን በመሳሰሉት አገራት በቱርኮች ላይ ይደረግ የነበረው ጫና እየበረታ በመምጣቱ ሳብያ የኦቶማን ቱርኮች ግዛተ መንግሥት ፈተና ውስጥ ገባ፡፡ ምዕራባውያንም በኦቶማን ግዛቶች ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖችና አይሁድ የሚከፍሉት የጂዝያ ግብር እንዲቀር ግፊት አደረጉ፡፡ የግብሩ መቅረት ያስቆጣቸው ሙስሊሞች በየቦታው ክርስቲያኖችን ማጥቃት ተያያዙ፡፡ በተለይ በደማስቆ ክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ጭፍጨፋ እጅግ ዘግናኝ ነበር፡፡ ጭፍጨፋው የተደረገው በ1860 ዓ.ም. ሲሆን በቁጣ የተሞሉ ሙስሊሞች ስለታማ መሳርያዎችን ይዘው በመውጣት ከ7,000 –

10,000 የሚገመቱ ክርስቲያኖችን ገድለዋል፡፡ ብዙዎችንም ለስደት ዳርገዋል፡፡ የቱርክ ወታደሮችም ጨፍጫፊዎቹን በመርዳት ክርስቲያኖችን አሳልፈው ይሰጡ ነበር፡፡ በሽሽት ላይ የነበሩትንም በመያዝ ከነሕይወታቸው የእሳት ነበልባል ውስጥ ይወረውሯቸው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ አብዱል ቃድር የተሰኙ ምግባረ ሰናይ ሙስሊም በሺህዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችን በቤታቸው በማስጠለል ማትረፋቸው በደግነታቸው ታሪክ ከሚያስታውሳቸው ሰዎች መካከል አንዱ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከፈረንሳይ መንግሥት የክብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት በሰብአዊነት የሚመሩ ለጥላቻ ትምህርቶች ልባቸውን ያልሰጡ ወገኖች ባይኖሩ ኖሮ ዓለማችን ምን ትሆን ነበር? ብዙ የአውሮፓ የሚስዮናውያን ድርጅቶችም ክርስቲያን ስደተኞችን በመታደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል፡፡ በወቅቱ የተደረገውን ጭፍጨፋ ዝነኛው የኒውዮርክ ታይምስ መጽሔት በኦገስት 13/ 1860 እትሙ ላይ በስፋት ዘግቦታል፡፡[85]

የኦቶማን ኢምፓየር መዳከም ሲጀምር ለዘመናት ሲጨቆኑ የኖሩት የተለያዩ የክርስቲያን ማህበረሰቦች ነፃነታቸውን መፈለግ ጀመሩ፡፡ ነገር ግን ይህንን ጥያቄ ማንሳታቸው እየተፈረካከሰ የነበረው የእስላም ግዛተ መንግሥት ምህረት የለሽ የጂሃድ ሰይፉን እንዲያሳርፍባቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ በተለይ በአርመናውያን ክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ሰቆቃ መቼም ቢሆን የሚረሳ አይደለም፡፡ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋው የተደረገው በ1915 ሲሆን ከአንድ ሚሊዮን እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚገመቱ ክርስቲያኖች በዘግናኝ ሁኔታ ተጨፍጭፈዋል፡፡ ወንዶቹ በጅማ የተጨፈጨፉ ሲሆን ሴቶችና ህፃናት ደግሞ በወታደሮች እየተነዱ ወደ ሦርያ በረሃ በመወሰድ እንዲበዘበዙ፣ እንዲደፈሩ፣ በረሃብ፣

[85] The New York Times: http://www.nytimes.com/1860/08/13news/syrian-outbreak-details-damascus-massacre-foreign-intervention-syria.html

በጥማትና በፀሐይ ሀሩር ተጠብሰው እንዲያልቁ ተደርጓል፡፡[86] ወታደሮቹ ክርስቲያን ሴቶችን ሲደፍሩ እንዲመለከቱ ባሎቻቸውን ያስገድዱ ከዚያም ይገድሏቸው እንደነበርና ብዙ ወጣት ሴቶችም በመስቀል ተቸንክረው መሰቀላቸውን የታሪክ ድርሳናት እማኝነታቸውን ይሰጣሉ፡፡[87]

## ሽብርተኝነት - የጥንቱ ጂሃድ አዲስ ገፅታ

የኦቶማን ግዛተ መንግሥት ከፈራረሰ ወዲህ ጂሃድ አዲስ መልክ እየያዘ መጣ፡፡ ከዚያ ቀደም ሙስሊም ባልሆኑት ሕዝቦች ላይ ይፈፀም የነበረው ጂሃድ በዋናነት በእስላም መንግሥታት አማካይነት ሲሆን አሁን ግን አፊሴላዊ በሆነ ሁኔታ በሕጋዊ መንግሥታት የሚደረጉ የጂሃድ እንቅስቃሴዎች የሚያስኬዱ አልሆኑም፡፡ ስለዚህ የእስላም መንግሥታት የሽብር ቡድኖችን በማደራጀትና በመደገፍ ከመድረክ ጀርባ ሆኖ መተወን አስፈልጓቸዋል፡፡ ዛሬ ለምዕራባውያን ሃያላን መንግሥታት እንኳ ፈተና የሆኑት በዓለም ላይ የሚገኙት የሽብር ቡድኖች ያላቸው አቅምና አደረጃጀት የግለሰቦች ስብስብ ብቻ አለመሆናቸውንና ከበስተጀርባቸው ሌላ ኃይል መኖሩን ይጠቁማል፡፡

በነቢዩ መሐመድና በተከታዮቻቸው የተጀመረው የጥንቱ ጂሃድ ስልቱን ቀይሮ "ሽብርተኝነት" የሚል ስም በማግኘት ብቅ ካለ ሰነባብቷል፡፡ በግብፅ የሚገኘው የአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲም ዋነኛ የፅንፈኛ ትምህርቶች መፍለቂያ መሆኑና ግብፅም የሽብርተኛ ቡድኖች የርቢ መስክ ሆና መቆየቷ ይታወቃል፡፡

---

86 Christopher J. Walker. *Armenia, the Survival of Nation; 1980,* pp. 200-203; Campo. *Encyclopedia of Islam;* pp. 62-63

87 Shahkeh Yaylaian Setian. *Humanity in the Midst of Inhumanity;* Xlibris publishers, 2011, p. 170

## ሊቃውንተ ሽብር

የእስላማዊ ሽብርተኝነትን አስተሳሰብ ከዋናዎቹ ምንጮች በመቅዳት ያስተማሩና የተገበሩ፣ ትምህርቱንም ስልታዊ ይዘት ባለው መልኩ ያዋቀሩ ሊቃውንተ ሽብር ይገኛሉ፡፡ በዋናነት የሚጠቀሱት አራት ሲሆኑ የመጀመርያው በመካከለኛው ዘመን የኖረ፣ ሁለተኛው በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን የኖረና የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ በሃያኛው ክፍለ ዘመን የኖሩ ናቸው፡፡

### ኢብን ተይሚያ - "የወሃቢዝም አያት"

ሐራን በተባለችው የቱርክ ከተማ በ1263 ዓ.ም. የተወለደው ኢብን ተይሚያ ሞንጎሊያኖች በሦርያ ላይ ጥቃት በፈፀሙበት ዘመን (1299-1303) ተዋግቶ ነበር፡፡ የሞንጎሊያ ሙስሊሞች እውነተኛ ሙስሊሞች እንዳልሆኑና ማንም ከእነርሱ ጋር እንዳይተባበር እንዲሁም ለእነርሱ እንዳይገዛ አስተምሮ ነበር፡፡ ለነርሱ የተገዛ፣ እነርሱን የረዳ ወይንም ደግሞ ከነርሱ ጋር የተደራደረ ሰው ልክ እንደነርሱ ከሃዲ እንደሆነም በማወጅ ሙስሊሞችን በጎራ ከፍሏል፡፡ ይህ አቋሙ ተከታዮቹ ሙስሊም ያልሆኑትን ብቻ ሳይሆን እውነተኛ ሙስሊሞች እንዳልሆኑ በሚያምኗቸው ሰዎች ሁሉ ላይ ጦርነትን እንዲያውጁ መንገድ ከፍቷል፡፡ ብዙ ሙስሊም ሊቃውንትን በመተቸት ጽሑፎችን የጻፈ ሲሆን ቁርአንና ሐዲሳት በቀጥታ መተርጎም አለባቸው የሚል አቋም ነበረው፡፡ ሙስሊሞች የነቢዩን አጋሮች (የሰሃባዎችን ወይም ሰለፎችን) መንገድ እንዲከተሉና "ቅዱሳን" የተባሉ ሰዎችን መቃብሮች ከመጎብኘት እንዲታቀቡ በብርቱ አስተምሯል፡፡ ኢብን ከሢርና ኢብን ቀይም የኢብን ተይሚያ አስተምህሮ ተፅዕኖ ካሳደረባቸው ሙስሊም ሊቃውንት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡[88] የዚህ ሰው ጽሑፎችና ትምህርቶች

[88] Mark Gabriel. *Islam and Terrorism;* p. 111

በአብደል ወሃብ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ለዛሬው የወሃቢዝም ፍልስፍና ዋና ምንጭ በመሆናቸው ምክንያት “የወሃቢዝም አያት” ብለነዋል፡፡

## ኢብን አብደል ወሃብ - “የወሃቢዝም አባት”

የሳዑዲ አረብያ ተወላጅ የነበረው አብደል ወሃብ (1703-1791) የወሃቢዝም (ሰለፊ) እንቅስቃሴ መስራችና ዋና ፈላስፋ ነበር፡፡ ቁልፍ አስተምህሮዎቹ “ኪታብ አል-ተውሂድ” (የአሃዳዊነት መጽሐፍ) በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ ሰፍረዋል፡፡ እንደ ኢብን ተይሚያ ሁሉ የቅዱሳን ሰዎችን መቃብሮች መጎብኘትን በጥብቅ የተቃወመ ሲሆን የቁርአንና የሐዲስ ጽሑፎች በቀጥታ መተርጎም እንዳለባቸው ያምናል፡፡ የሸሪኣ ሕግም በጥብቅ ተፈፃሚ መሆን እንዳለበት አስተምሯል፤ ተግባራዊም አድርጓል፡፡ አብደል ወሃብ ፍልስፍናው ፖለቲካዊ ድጋፍ ከሌለው በስተቀር ዘለቄታነት እንደማይኖረው ስለተረዳ በዘመኑ ከነበሩት የሳዑዲ ገዢዎች ጋር ስምምነት በመፍጠር ትምህርቱን አስፋፍቷል፡፡ አመለካከቱንም በንጉሣዊ ቤተሰቦች ዘንድ በማስረፅ ህልውናው የተረጋገጠ እንዲሆን አድርጓል፡፡ አብደል ወሃብ የእርሱን የእስልምና ትርጓሜ የማይቀበሉ ሰዎችን ሁሉ በከሃዲነት ይፈርጃል፡፡ የእርሱ አመለካከት ዛሬ የሳዑዲ አረብያ ኦፊሴላዊ የእስልምና ቅጂ ሲሆን  ወራሾቹ የሆኑት “የሼኹ ቤተሰብ” ከንጉሣዊ ቤተሰብ ጋር በመጋባት በሳዑዲ ፖለቲካ ውስጥ ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ሰው መርዛማ አስተምህሮ ተፅዕኖ ካደረባቸው ሰዎች መካከል ኦሳማ ቢንላደን ይጠቀሳል፡፡ የአልቃኢዳና የአይኤስ አባላት የዚህ ፍልስፍና ተከታዮች ሲሆኑ በዓለም ላይ የሚገኙትን አብዛኞቹን አሸባሪዎች እየፈለፈለ የሚያወጣውም ይኸው የወሃቢዝም ፍልስፍና ነው፡፡[89] ይህ እኩይ አስተምህሮ ወደ አገራችንም በመግባት ተቻችሎ የመኖር ባሕላችንን መናድ ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡

89 Campo. *Encyclopedia of Islam;* pp. 324-325

## ሰይድ ቁጥብ - "የሽብርተኝነት መሐንዲስ"

ሰይድ ቁጥብ (1906-1966) ቀለም ገብ የሚባል ዓይነት ሰው ነበር፡፡ የ24 ማጻሕፍት ደራሲ ሲሆን "ማሊም ፊ አል-ጠሪቅ" (የምልክት ድንጋዮች) በሚል ርዕስ የጻፈው መጽሐፉ ከሁሉም በላይ ዝነኛ አድርጎታል፡፡ ይህም መጽሐፍ ከዚያ ወዲህ በዓለም ላይ ለተነሱት እስላማዊ የሽብር ቡድኖች ሁሉ እንደ ዋና መመርያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡ በ1948 ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በመሄድ የትምህርት ሥርኣት ቀረፃ ትምህርቱን ባጠናበት ወቅት የታዘባቸውን ነገሮች *"እኔ ያየኋት አሜሪካ"* በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ያሰፈረ ሲሆን


ሰይድ ቁጥብ

በአሜሪካውያን የቴክኖሎጂ ምጥቀት መደመም ውስጥ መግባቱን ሳይሸሽግ "ቁሳዊነት የሚያጠቃውን" አመለካከታቸውንና "ምግባረ ብልሹ" የሆነውን የኑሮ ዘይቤያቸውን እንደተፀየፈ ተናግሯል፡፡ ዛሬ በብዙ ሙስሊሞች ዘንድ ለሰረፀው አሜሪካን እንደ ክፉት ሁሉ ምንጭ የመቁጠርና የመጥላት አመለካከት መሠረት የጣለው ሰይድ ቁጥብ ነው፡፡ ይህ ሰው ከእስልምና ውጪ የሚገኙትን ንፅረተ ዓለማት ሁሉ "ጀህሊያ" (ድንቁርና) በማለት ያብጠለጥላል፣ ይዘልፋል፣ ይኮንናል፤ በኃይል መወገድ እንዳለባቸውም ይናገራል፡፡ መሐመድና ተከታዮቻቸው መካን በመልቀቅ ወደ መዲና እንደተሰደዱት ሁሉ እውነተኛ ሙስሊሞችም "ጀህሊያን" ለቀው በመውጣት ራሳቸውን በመነጠል እንዲደራጁ አስተምሯል፡፡ ይህ አመለካከቱ ለብዙ ሽብርተኞች በቡድን መደራጀት ምክንያት ሆኗል፡፡ "ማሊም ፊ አል-ጠሪቅ" የሚለው መጽሐፉ ከታተመ በኋላ የዚህን ሰው መርዛማ አመለካከቶች አደገኛነት የተገነዘበው የግብፅ መንግሥት ነሐሴ 29/ 1966 ዓ.ም.

በስቅላት እንዲቀጣ አድርጎታል፡፡ መጽሐፍቱንም አግደፏቸዋል፡፡[90] ነገር ግን የግብፅ መንግሥት የወሰደው እርምጃ "ጅብ ከሄደ ..." ዓይነት ስለነበር ምንም ሊፈይድ አልቻለም፡፡ መርዛማ ትምህርቶቹ በብዙ ተከታዮቹ ዘንድ ከሰረፁ በኋላ የተወሰደው እርምጃ እንዲያውም ጂሃዳውያን ቁጥብን እንደ ጀግናና እንደ ሰማዕት በመቁጠር መርሆቹን አጥብቀው እንዲይዙና መጻሕፍቱም በብዙ ወጣቶች ዘንድ የመነበብ ጉጉት እንዲፈጥሩ ከማድረግ የዘለለ ውጤት አልነበረውም፡፡ የሞት ብያኔው ከተላለፈበት በኋላ "አልሀም ዱሊላህ፤ ይህንን የሰማዕትነት ዕድል እስካገኝ ድረስ ለአሥራ አምስት ዓመታት ጂሃድ አድርጌያለሁ..." ብሎ መናገሩ የጀግና አሟሟት መሞቱን ለማመልከ በተከታዮቹ ዘንድ ይጠቀሳል፡፡[91]

## አብዱላህ አዛም - "የዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት አባት"

አብዱላህ ዩሱፍ አዛም በምድረ ፍልስጥኤም የተወለደ ሲሆን የሙስሊም ወንድማማቾች ሕብረት መሥራች የሆነው የሐሰን አልባናን እንዲሁም የሰይድ ቁጥብን ሥራዎች በጥልቀት ያጠና ሰው ነበር፡፡ እስላማዊ ትምህርቶችን በሦርያና በግብፅ ውስጥ ካጠና በኋላ በሳዑዲ አረብያና በፓኪስታን ውስጥ በማስተማር አገልግሏል፡፡ በዘመኑ የነበሩትን የእስላማዊ ንቅናቄ መሪዎች ጽሑፎች በጥልቀት በማጥናት ሐሳቦቻቸውን መልክ አስይዞ ለተግባራዊ እርምጃ በሚረዳ መልኩ ወጥ የሆነ አስተምህሮ በማዋቀር በ1984 በአንድ ጥራዝ አሳትሞ ነበር፡፡ *"የሙስሊም ይዞታዎችን መጠበቅ"* የሚል ርዕስ ያለው ይህ መጽሐፉ ለዓለም አቀፋዊው ጂሃድ መሠረታውያን የሆኑ ተከታዮቹን ነጥቦች አካቷል፡-

- ሙስሊሞች በቅኝ ገዢዎችና ፍትሃዊ ባልሆኑ ሥርዓቶች ተዋርደዋል፡፡


[90] Mark Gabriel. *Islam and Terrorism;* pp.113-122

[91] Sayyid Qutb; Edited by A.B. al-Mehri. *Ma'alim fi'l-tareeq (Mile Stones);* 2006, p. III

- ሙስሊሞች ጂሃድን እንደ ግል ግዴታ ካልተቀበሉት እስልምና የመጨረሻው ሽንፈት ይደርስበታል፡፡
- እስልምና ከውድቀት መትረፍ የሚችለው ለአላህ ክብር ካሊፌት ሲቋቋም ብቻ ነው፡፡

አዛም በጂሃድ ራስን መሰዋትን በተመለከተ እንዲህ ብሏል፡-

> “ታሪክ መስመሮቹን የሚያሰምረው በደም ብቻ ነው፡፡ ክብር ማማዎቹን ሊገነባ የሚችለው በሰዎች የራስ ቅል ብቻ ነው፡፡ ሞገስና ክብር መሠረታቸውን የሚገነቡት በተቆራረጡ አካላትና በሬሳዎች ላይ ብቻ ነው፡፡”[92]



አብዱላህ አዛም

በአዛም እምነት መሠረት ለአንድ ሙስሊም ዓለም አቀፋዊውን ካሊፌት መልሶ ለማቆም ሲጋደል ከመሞት የበለጠ ክብር ሊኖር አይችልም፡፡

አብዱላህ አዛም በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ እጅግ የተከበረ የቁርአን ሊቅ በመሆኑ ምክንያት እርሱ ያወጣቸው ፈትዋዎች (ሃይማኖታዊ ድንጋጌዎች) በብዙ ሙስሊም ሊቃውንት ዘንድ ዕውቅና ተቸሯቸዋል፡፡ የሶቪዬት ሕብረት አፍጋኒስታንን በወረረበት ወቅት የነበረውን *የሙጃሂዲኖች* ንቅናቄ ወደ ዓለም አቀፋዊ ጂሃድ የለወጠው ይህ ሰው ነበር፡፡ ከበርቴ ከነበረው አባቱ ብዙ ሚሊዮን

[92] Sebastian Gorka. *Defeating Jihad: the Winnable War;* pp. 88

ዶላሮችን በውርስ አግኝቶ የነበረው ኦሳማ ቢንላደን በ1980ዎቹ መጀመርያ አካባቢ ብዙ ሺህ ወጣቶችን በመመልመል በፓኪስታን በኩል ወደ አፍጋኒስታን በማስረግና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ቁርአናዊ ተልዕኮውን ይወጣ በነበረበት ጊዜ ከአዛም ጋር ተወዳጅቶ ነበር፡፡ የሶቪዬት ጦር አፍጋኒስታንን ለቆ ከወጣ ከአንድ ዓመት በኋላ አብዱላህ አዛም በፓኪስታን ውስጥ ሲገደል በእርሱ የተመሠረተውን፣ ሃምሳ አምስት ሺህ የውጪ ሙጃሂድኖችን መልምሎ የነበረውን የጂሃድ ተቋም ለመምራት በወቅቱ ከቢንላደን የተሻለ ሰው አልነበረም፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይህ ተቋም *አልቃኢዳ* የሚል ስም በማግኘት ዓለም አቀፋዊ ተልዕኮን አንግቦ እንደ አዲስ ተደራጅቷል፡፡[93]

ከላይ የተጠቀሱት አራት ሰዎች በዚህ ዘመን ለሚገኘው የጂሃድ-ወሽብር አስተሳሰብ መሠረት የጣሉ ሰዎች በመሆናቸው ምክንያት ትኩረት ሰጠናቸው እንጂ በአደገኛ ትምህርቶቻቸው የሚታወቁ እስላማውያን ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡ በተለይ የአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ውጤቶች የሆኑት ከምድረ ግብፅ የፈለቁት ጂሃዳውያን የሽብር ስልቶችን በመንደፍ ረገድ ወደር አይገኝላቸውም፡፡ የሙስሊም ወንድማማቾች መስራች የነበረው ሐሰን አል-ባና፣ የሂዝቡ አል-ታህሪር (እስላማዊ የአርነት ንቅናቄ) መስራች የነበረው ሳላህ ሴሬያ፣ የአል-ተክፊር ወል-ሂጅራ መስራች የነበረው ሹክሪ ሙስጠፋ፣ የተብሊሒ ጀመዓት መስራች የነበረው ሙሐመድ ኢልያስ አል-ካንዝላዊ፣ የአል ጂሃድና የሌሎች ሽብርተኛ ቡድኖች መንፈሳዊ መሪ የነበረውና ፕሬዚዳንት ሳዳትን ያስገደለው አሁን በአሜሪካ እስር ቤት ውስጥ የዕድሜ ልክ እስር ላይ የሚገኘው “ዓይነ ስውሩ ሼኽ” ኦማር አብደልረህማን፣ የቢን ላደን ቀኝ እጅ የነበረውና የአልቃኢዳን የመሪነት ቦታ የተረከበው አይማን አል-ዘዋሕሪ፣ የብዙ አደገኛ መጻሕፍት ደራሲ የሆነውና በመገናኛ ብዙሃን የሰላም ጭምብል በመልበስ የሚቀርበው በመጻሕፍቱ ግን

[93] Ibid., pp. 86-94

የሸብርን መርዝ የሚያሰራጨው ዩሱፍ አል-ቀረዳዊ፣[94] ወዘተ. የመሳሰሉት ግለሰቦች በትምህርቶቻቸውና በጽሑፎቻቸው በሚሊዮኖች ደም የጨቀየውን፣ ሳይወድ በግድ የተዳፈነውን የሞት ማዕበል፣ የግፍ ረመጥ በመቆስቆስ የዘመናዊውን ጂሃድ ቋያ እሳት የለኮሱና እያነደዱ የሚገኙ በመሆናቸው ከአራቱ ግለሰቦች ያልተናነሰ ትኩረት ያሻቸዋል፡፡

## 1979 - ዓለም አቀፋዊው ሽብርና ሦስቱ ክስተቶች

በብዙዎች ግንዛቤ የዓለም አቀፋዊው ጂሃድ ጅማሮ ተደርጎ የሚታሰበው መስከረም 11/ 2001 በአሜሪካ ላይ የተፈፀመው ጥቃት ነው፡፡ ነገር ግን ጥቃቱ የዓለም አቀፋዊው ጂሃድ ውጤት እንጂ ጅማሬ አልነበረም፡፡ ማርክ እስቴይን በተሰኘ ጸሐፊ አባባል "መስከረም 11 ሁሉም ነገር የተለወጠበት ዕለት ሳይሆን ነገሮች ምን ያህል እንደተለወጡ ይፋ የወጣበት ዕለት ነበር፡፡"[95] በዘመናዊው ጂሃድ ታሪክ ከዚያ ይልቅ ልዩ ትርጉም ያለው 1979 ዓ.ም. ነው፡፡ ያ ዓመት ሽብርተኝነት ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዲኖረው ያደረጉ ተከታዮቹ ሦስት ታሪካዊ ኹነቶች የተፈፀሙበት ዓመት ነበር፡፡

### የኢራን አብዮት

እስላማዊው አብዮት ከመነሳቱ በፊት ኢራን የአሜሪካ ወዳጅ በነበረው የፓህላቪ ቤተሰብ ትመራ ነበር፡፡ በፈረንሳይ አገር ውስጥ በስደት ላይ የነበሩት አያቶላህ ኾሚይኒ መልዕክቶቻቸውን በካሴት በማሰራጨት ያፋፋሙት አብዮት ተሳክቶ

[94] የዩሱፍ አል ቀረዳዊ ሥራዎች በብዛት ወደ አማርኛ ተተርጉመው በእስላማዊ የመጽሐፍት መሸጫ መደብሮች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የዚህ ሰው ትምህርት ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ለማወቅ "ጂሉ ነስር አል-መንሹድ" በሚል ርዕስ ተጽፎ "ድል አድራጊ መፃዒ የሙስሊም ትውልድ" ተብሎ ወደ አማርኛ የተመለሰውን መጽሐፍ ማንበብ በቂ ነው፡፡ መጽሐፉን ያነበበ ሁሉ አሁን እየታየ የሚገኘውን እንደ አሸን የፈላውን፣ በጥላቻ፣ በእብሪትና፣ በአጉል ሃይማኖታዊ ቅንኣት የተጀነነውን፣ በጂሃድ የሚያምነውን ትውልድ በግልፅ ማየት ይችላል፡፡ የዚህን ሰው መርዛማ መጻሕፍት በብዛት ወደ አማርኛ በመመለስ እያሰራጨ የሚገኘው እዚሁ በምድረ ሐበሻ እየኖረ የሚገኝ ግለሰብ ነው፡፡

[95] Mark Steyn. *America Alone: the End of the World as We know it;* p. XI, 2006.

የቀደመው ሥርአት ከወደቀ በኋላ ወደ አገራቸው በመመለስ በሪፈረንደም እስላማዊ መንግሥት መሠረቱ፡፡ በሺአ እስልምና ትርጓሜ ላይ የተመሠረተ የሸሪአ ሕግም የእስላማዊቷ አገር ላዕላይ ሕግ ሆኖ ፀደቀ፡፡ በዚያው ዓመት ሚያዝያ 4 በቁጣ የተሞሉ የኾሜይኒ ወጣት ደጋፊዎች "ታላቋ ሰይጣን" በማለት የሚጠሯትን የአሜሪካን ኤምባሲ በመውረር ስድሳ ስድስት ዜጎቿን አገቱ፡፡ አሜሪካ የታገቱባትን ዜጎች በማስለቀቅ ላይ ከማተኮር የዘለለ በኢራን ውስጥ ሲከናወን የነበረውን ጉዳይ መረዳት ተስኗት ነበር ወይም "በምን ያመጣል" ስሕተት ማተኮር አልፈለገችም ነበር፡፡ አዛውንቱ ኾሜይኒ የመሠረቱት ሥርአት ጠንካራ ለነበረው የፓህላቪ ቤተሰብ አመራር አማራጭ በመሆን ይዘልቃል የሚል ግምት ስላልነበራትም ሊሆን ይችላል ጉዳዩን በቸልታ ተመለከተችው፤ ነገር ግን ያ ግምት ፍፁም የተሳሳተ ነበር፡፡

የኢራኑ እስላማዊ አብዮት በዚህ ዘመን እስላማዊ መንግሥት ማቋቋም እንደሚቻልና ምዕራባውያን አይደፈሬ አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ለብዙ ጂሃዳውያን የመነቃቃት ምክንያት ሆኗል፡፡[96]

## የመካ ከበባ

የቴህራኑ የአሜሪካ ኤምባሲ በተወረረ በአሥራ ሁለተኛው ቀን ሳዑዲ አረብያ ውስጥ አንድ ያልታሰበና ያልተጠበቀ ክስተት ተፈፀመ፡፡ ሦስት መቶ የሚሆኑ ሙስሊም ታጣቂዎች ታላቁን የመካ መስጊድ ተቆጣጠሩት፡፡ የታጣቂዎቹ መሪ ሲጠበቅ የነበረው መሐዲ እርሱ መሆኑን በማወጅ ዓለምን አስደመመ፡፡ እነዚህ ታጣቂዎች እንደ ምዕራባውያን አሻንጉሊት የሚቆጥሩትን የሳዑድን ቤተሰብ ጨምሮ ከአመለካከታቸው ጋር የማይስማሙትን ሙስሊሞች በሙሉ በከሃዲነት

96 Ibid., pp. 81-82

የሚፈርጁ *የተክፊሪ*[97] አመለካከት አራማጆች ነበሩ፡፡ ትግላቸው መጀመርያ ከእውነተኛው መንገድ ካፈነገጡት ሙስሊሞች ጋር እንደሆነና ሙስሊም ካልሆኑት ጋር የሚደረገው ፍልሚያ የመጀመርያው ተልዕኮ ከተሳካ በኋላ እንደሚቀጥል ያምኑ ነበር፡፡ ታጣቂዎቹ መደበኛ ሥልጠና ያልነበራቸውና ቀላል መሣርያዎችን የታጠቁ ቢሆኑም በማይታመን ሁኔታ ለሁለት ሳምንታት ያህል መስጊዱን ተቆጣጥረውት ከቆዩ በኋላ በፈረንሳይ ኮማንዶዎች እርዳታ አብዛኞቻቸው ተገድለው የተቀሩት በቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡

የሳዑዲ አረብያ የስለላ መረብ ከታጣቂዎቹ በስተጀርባ የነበሩትን ሰዎች ማንነት ካጣራ በኋላ የደረሰበት ነገር ለንጉሥ ሳዑድ ቤተሰብ በእጅጉ አስደንጋጭ ነበር፡፡ ግለሰቦቹ ቁልፍ በሆኑ ኡላማዎች (የሃይማኖት ሊቃውንት) ድጋፍ የተቸራቸውና ሊቃውንቱ ለሳዑዲ ገዢዎች የነበራቸውን ጥላቻ በተግባር የገለፁ ግለሰቦች ነበሩ፡ ፡ የጥላቻው መሠረት ደግሞ በገዢዎቹ ዳተኝነት ሕዝበ ሙስሊሙ እምነቱን በትክክል መተግበር ስለተሳነው ከሃዲያን የሆኑት የምዕራባውያን የበታች ሆኗል የሚል ነበር፡፡ አብዱል ወሃብ ከሳዑዲ ንጉሣውያን ቤተሰቦች ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን እንደገና ታድሶ ምዕራባውያን በአረብ ባሕረ ሰላጤ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመቀልበስ ጊዜው እንደሆነ አምነዋል፡፡

ከበባው ካከተመ በኋላ የሳዑዲ የስለላ መረብ በምርመራ የደረሰባቸውን ሊቃውንት አንገታቸውን ከመቅላት ይልቅ ንጉሡ ወደ ቤተ መንግሥት በመጋበዝ አጓጊ የሆነ የድርድር ነጥብ አቀረቡላቸው፡፡ ሊቃውንቱ በእስላም ምድርና በሙስሊሞች ላይ ጂሃድ መፈጸም ፍጹም *ሐራም* ወይም የተጠላ መሆኑን በማወጅ ዳግመኛ ለሳዑዲ መንግሥትና ለሳዑድ ቤተሰብ ስጋት መሆኑ እንዲቀር ለማድረግ፤ በምትኩ ደግሞ "በከሃዲያን" አገራትና በዓለም አቀፍ ደረጃ

---

[97] ተክፊሪ ሌሎች ሙስሊሞችን በከሃዲነት የሚፈርጅ የሱኒ ሙስሊም መጠርያ ነው፡፡

ለሚፈፀመው ጂሃድ ንጉሣዊ ቤተሰቡ ድጋፍ ለማድረግ ከስምምነት ተደረሰ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከነዳጅ የሚገኘውን ከፍተኛ ገቢ በመጠቀም አክራሪ እስልምናን በዓለም ዙርያ ለማስፋፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲሁም አሸባሪዎችን በመርዳት ረገድ ሳውዲ አረብያ ግንባር ቀደም ሚና መጫወቷን ቀጥላለች፡፡[98]

## የአፍጋኒስታን በሶቪዬት ሕብረት መወረር

የሶቪዬት ሕብረት ወዳጅ የነበረው የአፍጋኒስታን ሶሻሊስት መንግሥት በአገር በቀል ፅንፈኞች ይደርስበት የነበረውን ጥቃት መቋቋም ተስኖት ለመውደቅ ጫፍ ላይ በመድረሱ ምክንያት የውጪ ድጋፍ አስፈልጎት ነበር፡፡ በሕብረቱና በአፍጋኒስታን መንግሥት መካከል ከዚያ ቀደም በተፈረመው ስምምነት መሠረት ታህሳስ 24/ 1979 የሶቪየት ወታደሮች ወደ አፍጋኒስታን በመግባት በታጣቂዎች ላይ ጥቃቶችን መፈፀም ጀመሩ፡፡ ይህ ጦርነት ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ባላንጣዎች በሆኑት በራሽያና በአሜሪካ መካከል ወደሚደረግ ጦርነት ተሸጋገረ፡፡ ራሽያ በቀጥታ ውጊያው ውስጥ የገባች ስትሆን አሜሪካ ደግሞ አገር በቀሎቹን ሙጃሂዲኖች በመርዳት የራሽያን ዓላማ ለማክሸፍ ጥረቷን ተያያዘች፡፡ ሙጃሂዲኖች ከአሜሪካና ከሳውዲ አረብያ በሚጎርፈው ከሚፈለገው በላይ በሆነ ድጋፍ በመደራጀታቸው ምክንያት ለዓለም አቀፋዊው የሽብር ንቅናቄ ተግባራዊ መሠረት የተጣለው በዚያን ወቅት ነበር፡፡ የአፍጋኒስታን ጦርነት የነበረውን አንድምታ በተመለከተ የቢንላደን የበላይና የአልቃኢዳ ትክክለኛ መስራች የነበረው አብዱላህ አዛም የሚከተለውን ጽፎ ነበር፡-

> "አንዳንዶች ዓለም እንደጠፋችና ይህ ኡማ በሰማዕታት ጥማት እንዳረረ ተሰምቷቸው ነበር፡፡ ስለዚህ አላህ በምድረ አፍጋኒስታን ጂሃድን

[98] Ibid., pp. 83-84

በማፈንዳት ከተለያዩ የሙስሊም አገራት ወጣቶች ጂሃድና ሰማዕትነትን ፍለጋ እንዲጎርፉ አደረገ…”[99]

አብዱላህ አዛም፣ ቢንላደንና ጥቂት አረብ ጓዶቻቸው በአፍጋኒስታን ውስጥ የተደረገውን ጦርነት ወደ ዓለም አቀፋዊ የጂሃድ ንቅናቄ ለወጡት፡፡ አዛም ጂሃዳዊ ስልቶችን የመንደፍ ዕውቀት የነበረው ሲሆን ቢንላደን ደግሞ ገንዘብ ነበረው፡፡[100]

እነዚህ ሦስቱ ክስተቶች የዘመናዊው እስላማዊ ሽብርተኝነት መሠረቶች ምን እንደሆኑ በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ የኢራን አብዮት እስላማዊው አገዛዝ በዚህ ዘመን ሊተገበር የሚችል መሆኑን እንዲሁም የነፃውን ዓለም ተግዳሮት የመቋቋም አቅም እንዳለው በማሳየት ለጂሃዳውያን ወኔና ሰጥቷቸዋል፤ ሞዴልም ሆኗቸዋል፡፡ የመካ ከበባ ክስተት የሳዑዲ አረብያ መንግሥት ሽብርተኝነትን እንዲደግፍ በማሳመን የገንዘብና የአስተምህሮ ምንጭ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ የአፍጋኒስታን ጦርነት ደግሞ ለመደራጀትና ለመሰልጠን ምቹ የሆነ ከባቢን በመፍጠር ወደ ተግባራዊ እርምጃ እንዲገቡ ረድቷቸዋል፡፡ ከሽብርተኝነት ጋር በሚደረገው ፍልሚያ እነዚህን ሦስትዮሽ መሠረቶች ሳያፈርሱ ድልን ማሰብ የህልም እንጀራ የመብላት ያህል ነው፡፡ እስላማዊ ሽብርን ድል ለመንሳት እንደ ሞዴል የሚያየውን የወኔ መሠረቱን መደምሰስ፣ የአስተምህሮና የገንዘብ ምንጩን መድፈን እንዲሁም የርቢ መስኩን ምቹ እንዳይሆን ማድረግ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው፡፡

---

[99] Ibid., 85

[100] Ibid., pp. 84-86

# ክፍል 3

# ጂሃድና ኢትዮጵያ

❶

# ታሪክ እንደ ጂሃድ መሣርያ

የእስልምናና የኢትዮጵያ ግንኙነት የእስልምናን ያህል እድሜ ያለው ነው፡፡ የመጀመርያዎቹ ሙስሊም ስደተኞች እምነቱ በተመሠረተ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ነበር ወደ ኢትዮጵያ የመጡት፡፡ "አል-ነጃሺ" የተሰኘ የአክሱም ንጉሥ ጥሩ አቀባበል እንዳደረገላቸውና እንደሰለመ የሚናገሩ ትርክቶች በእስላማዊ መዛግብት ውስጥ በስፋት ይነበባሉ፡፡ ይህ ንጉሥ በብዙ እስላማዊ ጽሑፎች ውስጥ "አስሓማ ኢብን-አብጀር" ተብሏል፡፡ ስደተኞቹ ወደአገራቸው ከተመለሱ በኋላ መልካም መስተንግዶ እንደጠበቃቸውና ምንም ችግር እንዳልገጠማቸው የመሰከሩ ሲሆን ከዚህም የተነሳ ነቢዩ መሐመድ "ሐበሾች እስካልነኳችሁ ድረስ አትንኳቸው" ማለታቸው ይነገራል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች በየዘመናቱ የጂሃድ ሰይፍ ሲመዘዝባቸው ኖረዋል፡፡ የአገር ውስጦቹም ሆኑ የውጪ ጂሃዳውያን ቀን በፈቀደላቸው ቁጥር በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ ያላቸውን ጥላቻ በተግባር ሳይገልፁ ያለፉበት ዘመን አልነበረም፡፡

ዛሬ በውጪ የሚገኙት ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው ፅንፈኞችና በአገር ውስጥ የሚገኙት ነጫጭ እሾኾች የኢትዮጵያን ታሪክ በአዲስ መልክ ለመጻፍ እየሞከሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህም በመጠቀም ለክፍለ ዘመናት በመቻቻልና በፍቅር አብሮ የኖረውን ሕዝብ እርስ በርሱ ለማባላት ኢትዮጵያ ውስጥ ጂሃድ እንዲነሳ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ይህም በሁለት መልኩ ይገለፃል፡፡ የመጀመርያው "የአል-ነጃሺን" ጥንታዊ የአረቦች አፈ-ታሪክ እንደ አዲስ ማራገብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ግራኝ አሕመድን የመሳሰሉ በኢትዮጵያውያን ክርቲያኖች ላይ ወረራና ጥቃቶችን የፈፀሙ ጂሃዳውያንን ማወደስ ነው፡፡

# “ከአል-ነጃሺ” ታሪክ በስተጀርባ የሚገኝ ሤራ

ኢብን ኢስሐቅ የተሰኙት የመሐመድ ግለ ታሪክ ጸሐፊ “አል-ነጃሺ” እስልምናን በመቀበሉ ምክንያት ሕዝቡ እንዴት እንዳመፀበትና እርሱም ደግሞ እስላማዊውን *ታቂያ* (ማታለል) በመጠቀም እስልምናውን ሳይለቅ ሕዝቡንም ሳያስቆጣ እንዴት በዘዴ እንዳመለጠ ጽፈዋል፡-



በትግራይ ክልል የሚገኘው አል-ነጃሺ መስጊድ

ጃዕፋር ኢብን መሐመድ አባቱን ዋቢ አድርጎ እንደነገረኝ ሐበሾች ተሰብስበው “እምነታችንን ለቀሃል” አሉት፡፡ አመፁበትም፡፡ ስለዚህ መርከቦችን በማዘጋጀት ወደ ጃዕፋርና አብረውት ወዳሉት ሰዎች “እዚህ ላይ ተሳፍራችሁ ተዘጋጁ፤ እኔ ከተሸነፍኩኝ ወዳሰኛችሁ ቦታ ሂዱ፤ እኔ ድል ከቀናኝ ደግሞ ባላችሁበት ሁኑ” አላቸው፡፡ ከዝያም ወረቀት በመውሰድ “ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም መሐመድም ደግሞ መልእክተኛው ናቸው፤ የማርያም ልጅ ዒሳ ባርያው፣ መልእክተኛው ወደ ማርያምም የጣለው መንፈሱና ቃሉ ነው” ብሎ ጻፈ፡፡ ከለበሰው ካባ ስር በቀኝ ትከሻው በኩል በማስቀመጥ ተሰልፈው ሲጠባበቁት ወደነበሩት ሐበሾች መጣ፡፡ “እናንተ ሰዎች ሆይ እኔ ከመካከላችሁ የተመርጥኩ አይደለሁምን?” አላቸው፡፡ እነርሱም “አዎ ነህ” በማለት መለሱለት፡፡ “ሕይወቴስ በናንተ መካከል እንዴት ነው?” በማለት ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም “በጣም ጥሩ ነው” በማለት መለሱለት፡፡ “ታድያ ችግራችሁ ምንድነው?” በማለት ጠየቃቸው፡፡ “እምነታችንን በመካድ “ኢየሱስ ባርያ

ነው" ብለሃል" አሉት፡፡ "ታድያ እናንተ ኢየሱስ ማነው ትላላችሁ?" አላቸው፡፡ እነርሱም "እኛ እርሱ  የፈጣሪ ልጅ ነው እንላለን" አሉት፡፡ ንጉሡም እጁን በደረቱ ላይ በማድረግ የማርያም ልጅ ኢየሱስ "ከዚህ በላይ አይደለም" በማለት መሰከረ፡፡ "ከዚህ" ሲል የጻፈውን ለማለት ነው፤ ነገር ግን እነርሱ በተናገረው ነገር በመርካት ተመልሰው ሄዱ፡፡ ይህ ወሬም ነቢዩ ዘንድ ደረሰ፡፡ ንጉሡም ሲሞት ጸለዩለት፣ ኃጢአቱም ይቅር እንዲባልለት ለመኑለት፡፡[101]

"አል-ነጃሺ" የሚባል ንጉሥ በኢትዮጵያ ታሪክ እንደነበረ የሚናገሩት ብቸኛ ምንጮች እስላማዊ ጽሑፎች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት *"አሕመድ አል-ነጋሺ የሚባል ንጉሥ በኢትዮጵያ አልነበረም"* በሚል ርዕስ ባሳተማቸው ሁለት ተከታታይ ቡክሌቶች በዚህ ስም የሚታወቅም ሆነ ወደ እስልምና እምነት የተለወጠ ንጉሥ በኢትዮጵያ ታሪክ አለመኖሩን ማስረጃዎችን በመጥቀስ መልስ ሰጥቷል፡፡ በነዚህ ቡክሌቶች ውስጥ በአክሱም የነገሡት ነገሥታት ከመጀመርያው ጀምሮ በስም ተዘርዝረው የተቀመጡ ሲሆን "ነጃሺ" የሚል ስም ግን አይገኝበትም፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ የሚነገረው በ615 ዓ.ም. አካባቢ ሲሆን በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበረው ንጉሥ አካለ ውድም (615-623) እንደነበር ተመልክቷል፡፡[102] አንዳንድ የታሪክ ጸሐፍት በወቅቱ የአክሱም ንጉሥ የነበረው አርማሕ አለጸሐም እንደነበረ የሚናገሩ ቢሆንም በዝርዝሩ መሠረት ቀዳማዊ አርማሕ ቅድመ እስልምና በ442-456 ዓ.ም. የነገሥና ዳግማዊ አርማሕ ደግሞ

---

101 Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp. 154-155

102 በአንዳንድ ጸሐፍት የንጉሡ ስም አድርአዝ ነው መባሉ የዚህ ታሪክ ብቸኛ ምንጮች የሆኑትን እስላማዊ ጽሑፎች ውድቅ ያደርጋል፡፡ በዝርዝሩ መሰረት አድርአዝ ከ595-615 ነበር የነገሠው፡፡ ስደተኞቹ ወደ አክሱም መጡ በተባለበት ዘመን (615) ከሞተ ደግሞ ከመሐመድ ጋር የረጅም ጊዜ ግንኙነት እንደነበረውና የገፀ በረከት ልውውጥ እንዳደረገ በእስላማዊ ምንጮች ውስጥ መነገሩ ስህተት ነው ማለት ነው፡፡

ድህረ እስልምና በ817-822 ዓ.ም. የነገሠ በመሆኑ ትክክል ሊሆን አይችልም፡፡ በግዕዝ ነጋሢ በአማርኛ ደግሞ ነጋሽ የሚለው ስያሜ ግብር አስከፋዮች ለሆኑት ሹማምንት የሚሰጥ እንጂ ለነገሥታት የሚሰጥ ስም አልነበረም፡፡ በተለይ ባህር ነጋሺ የሚለው ስያሜ የሐማሴን የባሕር በር ኀላፊ መጠርያ የነበረ ነው፡፡ ስያሜው እንዲያውም ማዕርግ እንጂ መጠርያ ስም አይደለም፡፡[103] በተጨማሪም በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት የአክሱም ሳንቲሞች የመስቀል ምልክት የነበራቸውና ምንም የእስልምና ምልክት የሌላቸው ናቸው፡፡ የመጀመርያዎቹ ሙስሊሞች ወደ ኢትዮጵያ መሰደዳቸው እሙን ቢሆንም ንጉሡ ሰልሟል የሚለው በእስልምና መዛግብት ውስጥ የሰፈረው ትርክት በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ በማንኛውም የታሪክ ድርሳን ያልተመዘገበ የአርኪዎሎጂ ማስረጃም ሆነ የጽሑፍ ማስረጃ የሌለው የፈጠራ ታሪክ ነው፡፡

ነቢዩ መሐመድ "ሐበሾች እስካልነኳችሁ ድረስ አትንኳቸው" በማለት እንደተናገሩት የሚነገረው አባባል "ከአል-ነጃሺ" የመስለም ታሪክ ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ ይጠቀሳል፡፡ በርግጥ ይህ አባባል በትክክል በመሐመድ በመነገሩ ዙርያ በሙስሊም ሊቃውንት ዘንድ ጥርጣሬ አለ፡፡[104] አባባሉ ትክክል ቢሆን እንኳ በሁለት ምክንያቶች ኢትዮጵያ ከጦርነት ነፃ ልትሆን እንደማትችል ሙሐመድ ጦይብ የተሰኙ አረባዊ ጸሐፊ ይናገራሉ፡፡ የመጀመርያው የእስላም ሕግ ተፈጻሚ አለመሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይኩኖ አምላክ "ቃል ኪዳን በማፍረስ ሙስሊሞችን መዋጋቱ" ነው፡፡[105] ስለዚህ ሙስሊሞች "አል-ነጃሺ" እንደሰለመ ማመናቸው ኢትዮጵያ ከጂሃድ ነፃ እንድትሆን ያደርጋታል የሚለው አስተሳሰብ ዋስትና የለውም፡፡

---

103 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት፣ 2000 ዓ.ም.፣ *አሕመድ አል-ነጋሺ የሚባል ንጉሥ በኢትዮጵያ አልነበረም፤* ክፍል 1 እና ክፍል 2፡፡

104 ሙሐመድ ጦይብ፡፡ *ኢትዮጵያ እና ኢስላም፤* 1999፣ ገፅ 104፤ በኢድሪስ ሙሐመድ የተተረጎመ

105 ዝኒ ከማሁ

በአሁኑ ወቅት በተለይም በአክራሪ ሙስሊሞች ዘንድ እየጎላ የመጣው አመለካከት ኢትዮጵያ “በአል-ነጃሺ” መስለም ምክንያት “የእስላም ሕጋዊ ግዛት” የመሆኗ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ አመለካከት በብዙ ሙስሊም ጸሐፊያን ጽሑፎች ውስጥ በስፋት ተንፀባርቆ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ያህል አሊ አል-ሼኽ አሕመድ በክር የተሰኙ የሳዑዲ አረቢያ ጸሐፊ “መዓሊም  አል-ሒጅራተይን ኢለ አርድ አል-ሐበሽ” (ወደ ሐበሻ ምድር የተደረጉት የሁለቱ ሒጅራዎች ባህርያት) በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ አል-ነጃሺ እስልምናን በመቀበሉ ምክንያት ኢትዮጵያ የእስላም ግዛት አካል መሆኗን፣ እስልምና በአል-ነጃሺ መስለም ያስመዘገበው ድል በትክክል አለመጠበቁን፣ ጨቋኝ የሆነው የክርስትና እምነት ሙስሊሞችን በኢትዮጵያ ውስጥ ማዋረዱን፣ ኢትዮጵያ ሙስሊም አገር መሆኗን፣ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አረቦች መሆናቸውን፣ አሕመድ ግራኝ የፈፀመው ጂሃድ የኢስላምን ጠላቶች ለመጋፈጥ ጥሩ ሞዴል መሆኑን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው ጂሃድ በሙስሊም አገራት መታገዝ እንደሚገባው፣ ወዘተ. በስፋት ጽፈዋል፡፡[106]

ፕሮፌሰር ሓጋይ ኢርሊች የተሰኙ በኢትዮጵያ እስልምና ላይ ጥልቅ ጥናቶችን ያደረጉ ምሑር “የሰለመ አል-ነጃሺ” ማለትም “የሰለመ የኢትዮጵያ ንጉሥ” የሚለው ትርክት በመካከለኛው ምስራቅ በሚገኙት ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ባላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ዘንድ “ኢትዮጵያ የእስላም ምድር ናት” በሚል እንደሚተረጎም ይገልፃሉ፡፡ ፕሮፌሰሩ ካደረጉት ጥናት በመነሳት እንደገለፁት ሙስሊሙ “አል-ነጃሺ” በጦር አዛዦቹና በካህናቱ ተከድቶ ለብቻው እንዲገለል ከተደረገ በኋላ እንደሞተ መነገሩ እስልምና ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸነፈባት ምድር ተደርጋ እንድትቆጠርና የኢትዮጵያ የክርስትና ታሪክም “ሕገወጥ” ተደርጎ እንዲቀርብ ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ እስልምና በአፍሪቃ ውስጥ ያለውን መስፋፋት የገታችና ሙስሊም ዜጎቿን የምትጨቁን አገር ተደርጋ

[106] Haggai Erlich. *Saudi Arabia & Ethiopia;* 2007, pp. 194-200

ተቆጥራለች፡፡ በአክራሪ ሙስሊሞች አመለካከት መሠረት ኢትዮጵያ ሙስሊም መሪ እንደገና በማስቀመጥ ልትቤዥ ይገባታል፡፡ "የሰለመ አል-ነጃሺ" የሚለው መፈክር በመካከለኛው ምስራቅ ለሚገኙት ሙስሊሞች የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ ሥርኣት ለማጣጣልና የአፍሪቃ ቀንድ ሙስሊሞች ፖለቲካዊ ስልጣኗን እንዲቆናጠጡ ለማደፋፈር መጠቀሚያ ሆኗቸዋል፡፡ ይህ "የሰለመ አል-ነጃሺ" ታሪክ ጂሃዳውያን ኢትዮጵያ ላይ እንዲዘምቱ ምክንያት በመሆን በተደጋጋሚ አገሪቱን ለአደጋ አጋልጧታል፡፡ በአፄ ዮሐንስ ዘመን የሱዳን መሐዲዎች ለንጉሡ በጻፉት ደብዳቤ ውስጥ የአል-ነጃሺን ዱካ ተከትለው እስልምናን እንዲቀበሉ የሚያሳስብና እምቢ ካሉ ደግሞ ጥፋት እንደሚጠብቃቸው የሚገልፅ መልእክት መስፈሩን ፕሮፌሰር ሓጋይ ለዚህ እንደ ምሳሌ ይጠቅሳሉ፡፡ በምሑሩ ጥናት መሠረት ኢትዮጵያ ችግር ውስጥ በገባችባቸው ጊዜያት ሁሉ አገሪቱን ለመደገፍም ሆነ ከጠላቶቿ ወገን ለመሰለፍ እንደ ዋና ጉዳይ ተነስቷል፡፡ በኢጣሊያ ወረራ ወቅትም የሆነው ይህ ነበር፡፡[107]

"የአል-ነጃሺ" ጉዳይ የታሪክ ሃቀኝነት ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ የፅንፈኛ ሙስሊሞች ፍላጎት አንዳንድ የዋኀን እንደሚያስቡት የነቢዩን ወዳጆች በመልካም ሁኔታ ያስተናገደውን የአገራችንን ንጉሥ እንደ ሙስሊም በመቁጠር "አክብሮት መስጠት" አይደለም፡፡ ይህ ታሪክ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሙስሊም የነበረውን ንጉሥ አሰቃይተው ገድለዋል በማለት ይከሳል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በሙስሊም ባልጀሮቻቸው ዘንድ የተጠሉ እንዲሆኑ ለማድረግ እኩይ ዓላማ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ "ኢትዮጵያ የመጀመርያዎቹን ሙስሊም ስደተኞች ተቀብላ ያስተናገደች አገር ናት"፤ "ሐበሾችን ካልነኳችሁ አትንኳቸው"፤ "ኢትዮጵያ ለእስልምና ክብር የሰጠ ደግ ንጉሥ የነበራት አገር ናት"፤ ወዘተ. የሚሉት አባባሎች ጎልተው ይነገሩ የነበረ

107 Ibid., p. 3

ሲሆን አሁን ግን "ኢትዮጵያ ሙስሊም ንጉሷን አሰቃይታ የገደለች አገር ናት"፤ "ለእስልምና መስፋፋት እንቅፋት የሆነች አገር ናት"፤ "የእስላም ግዛት አካል ናት"፤ "ሙስሊም ዜጎቿን የምትጨቁን አገር ናት"፤ ወዘተ. የሚሉ ድምፆች አይለው እየተሰሙ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ "የሰለመ አል-ነጃሺ" የሚለው የፈጠራ ታሪክ ለአገር ደህንነትና ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ህልውና አደጋ የሚፈጥር ሤራ ከበስተጀርባው የሚገኝ በመሆኑ እንዲሁም ለዘመናችን ጂሃዳውያን የፕሮፓጋንዳ መሣርያ በመሆን እያገለገለ ስለሚገኝ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች አንድ ሊሉት ይገባል፡፡ በፈጠራ ታሪክ አገር ስለምን ለአደጋ ትጋለጥ?

# ውዳሴ አሕመድ ግራኝ

በተለምዶ አሕመድ ግራኝ ወይም በትክክለኛ ስሙ አሕመድ ኢብን ኢብራሂም አል-ጋዚ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ትልልቅ ጥፋቶችን ካደረሱ ጂሃዳውያን መካከል በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ ሰው አነሳሱ ከሐረር አካባቢ ሲሆን ከሶማሌ ዘር መሆኑ በአብዛኞቹ የታሪክ ጸሐፍት ዘንድ ይታመናል፡፡ ነገር ግን የዘር ግንዱ ከአረብ ይመዘዛል የሚሉም አልጠፉም፡፡[108] ግራኝ የተነሳበት ዘመን በየአገራቱ የጂሃድ ቋያ እሳት ይንቀለቀል የነበረበትና ፖለቲካዊውም እስልምና ከመቸውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ የሙስሊም አገራትን በማስተሳሰር ለአንድ ዓላማ እንዲሰለፉ ያስቻለበት ዘመን ስለነበር ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩትና ከሃይማኖት ይልቅ ወደ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ የበላይነት በሚያደሉት፤ እርስ በርሳቸውም በመዋጋት በሚታወቁት ሙስሊም ሱልጣኔቶች ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም፡፡ እነዚህን ሱልጣኔቶች ለአንድ ዓላማ በማሰለፍ እስልምና በኢትዮጵያ ላይ ሲመኝ የነበረውን የበላይነት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ማሳካት የቻለው አሕመድ ግራኝ ነበር፡፡ የአፄ ልብነ ድንግል ደካማ የአመራር ብቃትና በክርስትና እምነቱ ላይ የነበረው የላላ አቋም እንዲሁም የፊውዳሉ ብልሹና ኀላፊነት የጎደለው ሁኔታ የጂሃድ ጦር በኢትዮጵያውያን ላይ ድልን እንዲቀዳጅ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ደግሞ በኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ የነበሩትን ሕዝቦች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ማስተማር እንደተሳናትና በጥቃቅን ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በነበሩት የአመለካከት ልዩነቶች በጎራ የመከፋፈል ሁኔታም እንደነበር የታሪክ ጸሐፍት ይናገራሉ፡፡[109] ቱርኮችና ማምሉኮችን

---

[108] Siegbert Uhlig. *Encyclopedia Aethiopica;* 2003, A-C, p. 155

[109] Merdechai Abir. *Ethiopia and the Red Sea: the Rise and Secline of the Solomonic Dynasty and Muslim-European Rivalry in the Region:* 1980, pp. 80-82

የመሳሰሉት የውጪ የእስላም ኃይላት ለወራሪ ጂሃዳውያኑ የሚሰጡት ድጋፍም ቀላል አልነበረም፡፡ በዚያን ዘመን በአገር ውስጦቹ ላይ ብቻ ሳይሆን በውጪ አገራት በነበሩት ኢትዮጵያውያን ላይም ጭምር ጥቃቶች ይፈፀሙ ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል በ1518 እና በ1522 ቱርኮች ለጸሎት ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ በነበሩት ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ላይ ጭፍጨፋ ፈፅመዋል፡፡[110] ይህም ደግሞ በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ የተደረገው ጂሃድ ዓለም አቀፋዊ ገፅታ እንደነበረው ያሳያል፡፡



በሞቃዲሾ ለአሕመድ ግራኝ (አሕመድ ጉርዩ) የተሠሩለት የመታሰብያ ሐውልታት

የፎቶ ምንጭ Wikipedia.org

የሰሜኑ የክርስቲያን መንግሥት በጂሃዳውያን ላይ የበላይነቱን ማጣቱንና ታሪክ መቀየሩን ያመለከተው በ1529 በወርሃ መጋቢት የተደረገው የሽምብራ ኩሬ ጦርነት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የግራኝ ጦር ከቱርክ ባስመጣቸው አዳዲስ መድፎች በመጠቀም የአፄ ልብነ ድንግልን ሠራዊት ገጠመ፡፡ በዚህ ጦርነት ላይ 200

110 Ibid.

የሚሆኑ ሥልጡን የቱርክ ወታደሮችና ብዙ የአረብ ወታደሮች ተሳትፈዋል፡፡[111] በመድፎቹ ጥቃት የተደናገጡት የንጉሡ ወታደሮችም ነፍሳቸውን ለማትረፍ መሸሽ ግድ ስለሆነባቸው የጂሃድ ጦር ወሳኝ ድል ተቀዳጀ፡፡ ከዚያ ወዲያ የአፄ ልብነ ድንግል ወታደሮች ያሉበት ቦታ ታውቆ ለጥቃት እንዳይጋለጡ በመስጋት ምግባቸውን ለማብሰል እንኳ እሳት ማንደድ አልቻሉም ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥሬ ሥጋ መብላት የተጀመረው በዚያን ዘመን እንደነበር ይነገራል፡፡[112]

የመጀመርያውን ስኬት ተከትሎ የጂሃድ ጦር በድል ላይ ድልን እየደረበ እስከ ትግራይ ድረስ ዘለቀ፡፡ የትግራይ አምባዎች በቀላሉ የሚያዙ ስላልነበሩ ግራኝ አውራይ አቡይ የተሰኘ ሹሙን በመላክ ሦስት ትልልቅ መድፎችን ገዝቶ እንዲያመጣ አደረገ፡፡ ከሦስቱ መድፎች መካከል አንዱ በጣም ግዙፍ ነበር፡፡ ተኳሾቹም በመድፍ ተኩስ ጥበብ የተካኑ ከሕንድ የመጡ ቅጥረኞች ነበሩ፡፡[113] የጂሃድ ሠራዊት የአክሱም ፅዮን ማርያምን ቤተ ክርስቲያ ዘረፈ፣ አቃጠለ፡፡ ወደ ምዕራብም በመዘርጋት እስከ ኑቢያ ድረስ የነበረውን የክርስቲያን ምድር ወረረ፣ አጠፋ፣ አብያተ ክርስቲያናትንና ቅዱሳት መጻሕፍትን አቃጠለ፣ ካህናትና ምዕመናንን አረደ፣ ንዋዬ ቅዱሳትን ዘረፈ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑን በግድ አሰለመ፡፡ ሁለት ሦስተኛው የክርስቲያን ግዛት በጂሃዳውያን እጅ የገባ ሲሆን በክርስቲያን ምንጮች መሠረት ዘጠና ከመቶ በላይ የሚሆነውም ሕዝብ በግድ እንዲሰልም ተደርጎ ነበር፡፡[114] በሙስሊም ምንጮች መሠረት ግን በጣት የሚቆጠሩት ብቻ ሲቀሩ ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን ሰልሞ ነበር፡፡[115]

---

111 ይልማ ዴሬሳ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፤* 1959፣ ገፅ 64-65

112 United States Joint Publications Research Service: *Translations on Sub-Saharan Africa;* Issue 1767-1775, p. 62

113 ይልማ ዴሬሳ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፤* ገፅ 109

114 J. Spencer Trimingham. *Islam in Ethiopia;* 1952, p. 88

115 Ibid., 87

በዚያን ዘመን የእሳት ሲሳይ ከሆኑት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የደብረ ሊባኖስ ገዳምና የአትሮንስ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይጠቀሳሉ፡፡ የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኮሳት ቤተ ክርስቲያኒቱን ከቃጠሎ ለማትረፍ አቡበከር ከቲም ለተሰኘው የግራኝ የጦር መኮንን በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚገኘውን ኃብት፣ ከብርና ከወርቅ የተሰሩትን ንዋየ ቅዱሳት ሁሉ ቢሰጡትም ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመቃጠል አልዳነችም፡፡[116] በአትሮንስ ማርያም ላይ የተደረገውን በተመለከተ ይልማ ዴሬሳ የተሰኙት የታሪክ ጸሐፊ ተከታዩን አስፍረዋል፡-

> *መካነ ሥላሴን ካጠፉ በኋላ ግራኝ ወደ ሌላዋ ኃብታም ደብር ገሥግሦ አትሮንስ ማርያም የምትባለውን ታላቅ ደብር አዘርፎ አቃጠላት፡፡ ያትሮንስ ማርያም ዘረፋ ከስድስት ሰዓት እስከሚከተለው ጠዋት ድረስ ቆየ ይባላል፡፡ የግራኝ ሱማሌዎች ከመቅደሱ ግድግዳ ላይ የተለበጠውን ከፊይና የሙካሽ ጥልፍ ሥራዎች እየቀደዱ ከወሰዱ በኋላ ቁጥር የሌላቸውን የወርቅ ፅዋዎችና ሌሎችንም የንዋየ ቅዱሳት ዕቃዎች ሁሉ ዘረፉ፡፡ ከተወሰዱትም ምርኮዎች መካከል አንድ ሺህ ወቄት የሚመዝን የወርቅ ጽላትና በወርቅ ቅጠል ላይ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ይባላል፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በጣም የሚከብድ ስለነበረ አራት ሰዎች ሁነው ሊያነሱት አልቻሉም፡፡ ዘረፋው ከተፈጸመ በኋላ የግራኝ ሰዎች በዚህችም ደብር ላይ እሳት ለቀቁባት፡፡ ከመነኮሳቱም መካከል ቤተ ክርስቲያናቸው ስትቃጠል ባዩ ጊዜ በኀዘንና በወዮታ እየዘለሉ ከእሳቱ ውስጥ ወድቀው አብረው የተቃጠሉ ብዙዎች ነበሩ፡፡*[117]

---

116 ይልማ ዴሬሳ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፤* ገፅ 85
117 ዝኒ ከማሁ ገፅ 91

ጂሃዳውያን አንሰልምም ያሉትን ክርስቲያኖች አብዛኞቹን የገደሉ ሲሆን የተቀሩትን በነቢዩ መሐመድ ትዕዛዝ መሠረት ጂዝያ ያስከፍሉ ነበር፡፡[118]

በዚያን ዘመን ክርስቲያኖች እምነታቸውን ይዘው ለመቆየት ያሳዩትን ጀግንነት ሊገልፅ የሚችል አንድ ታሪክ እንጥቀስ፡-

> … ሁለት ክርስቲያኖችን ይዘው ወደ ኢማሙ ሰፈር በመመለስ በፊቱ አቀረቧቸው፡፡ እርሱም "አገሪቱ በሙሉ መስለሟን እያያችሁ እስልምናን የማትቀበሉት ለምንድነው?" በማለት ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም "አይ መስለም አንፈልግም" አሉት፡፡ "ስለዚህ የምናስተላልፍባችሁ ፍርድ ራሳችሁን መቁረጥ ነው" አላቸው፡፡ እነርሱም "ይሁን" አሉት፡፡ ኢማሙም በመልሳቸው ተደነቀ፤ እንዲገደሉም አዘዘ፡፡[119]

አሕመድ ግራኝ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ምድሪቱን ሲያስጨንቅ ከቆየ በኋላ ንግሥት እሌኒ በነበራት ፖለቲካዊ ብስለት ያስመጣቻቸውንና አፄ ልብነ ድንግል አስቀይሞ የመለሳቸውን ፖርቹጋሎች እንደገና ለማስመጣት ቤርሙዴዝ የተባለ መልእክተኛ ተላከ፡፡ የእርዳታ ጥያቄውም አዎንታዊ ምላሽ በማግኘቱ 400 የሚሆኑ የፖርቹጋል ወታደሮች ከነረዳቶቻቸው ክርስቶፈር ዳጋማ[120] በተሰኘ የ25 ዓመት ወጣት የጦር አዛዥ መሪነት ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ በጂሃድ ጦር ከፍተኛ የሞራል ውድቀት ውስጥ ገብቶ የነበረውም የንጉሡ ሠራዊት ወኔው ተነሳሳ፡፡ ግራኝ የፖርቹጋሎቹን መምጣት በሰማ ጊዜ ከንጉሡ ጋር እንዳይገናኙ ለማድረግ በተለያዩ ጊዜያት ውጊያ የገጠማቸው ሲሆን በመጀመርያው ውጊያ በጥይት ቆስሎ ለጥቂት ከመያዝ ተርፎ ሸሽቷል፡፡[121] ነገር ግን ኋላ ላይ ተሳክቶለት ክርስቶፈር

---

118 Trimingham. *Islam in Ethiopia;* p. 88
119 Ibid., 88-89
120 ክርስቶፈር ዳ ጋማ የዝነኛው ፖርቹጋላዊ አሳሽ የቫስኮ ዳ ጋማ ልጅ ነበር፡፡
121 Trimingham. *Islam in Ethiopia;* p. 89

ዳጋማን በመማረክ ገድሎታል፡፡ የክርስቶፈርን አሟሟት በተመለከተ ሚጉኤል ዴ - ካስታንጓዞ የተሰኘ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት የፖርቹጋል ወታደሮች መካከል አንዱ የነበረ ሰው በስፋት ጽፏል፡፡


> ... ዶም ክርስቶፍ መሆኑን በትጥቁ ወዲያውኑ ስላወቁት በያዙት ጊዜ በጣም ደስ አላቸው፡፡ በመንገድም ላይ በጣም እያላገጡበትና በጣም እንዳልሆነ እያደረጉት ይዘውት ሄዱ፡፡ ከዚያ በኋላ እርሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን በግራኝ ፊት አቀረቧቸው፡፡ ግራኝም ከመቶ ስድሳ የሚበልጡ የፖርቱጋሎች ራስ ከድንኳኑ ፊት በእንጨት ሰክቶ ተክሎ ስለነበረ ባደረገው ድል በጣም ደስ አለው፤ ለያንዳንዱ የፖርቱጋልን ራስ ለሚቆርጥ ወታደር ዋጋ አድርጎለት ስለነበረ ይህንኑ ዋጋ ለማግኘት ሰዎቹ ከጦሩ ሜዳ ያገኟቸውን ሁሉ ይዘው ሄዱ፡፡
>
> ዶም ክርስቶፍ ከድንኳኑ ፊት በቀረበ ጊዜ የበለጠ ጭንቀት እንዲያድርበት ለማድረግ ይህ ውሻ የፖርቱጋሎችን ራሶች ከፊቱ አስመጥቶ የማን ራሶች ናቸው? እያለ አላገጠባቸው፡፡ እነዚህ ዶም ክርስቶፍ ከነርሱ ጋር ሁኖ አገሩን ሊወስዱበት የነበሩት መሆናቸውን (በቀልድ እያመለከተ) ዶም ክርስቶፍ እንዲህ ዓይነት ነገር በማሰቡ እብደቱ እንደሚታይ እያስገነዘበ ለዚህ ድፍረቱም ትልቅ ክብር ሊያደርግለት መፍቀዱን ለመግለጥ ዶም ክርስቶፍን ልብሱን እንዲያወልቁ፣ ሁለት እጆቹን እንዲያስሩና በጭካኔ እንዲገርፉት በባርያዎቹ ጫማም ፊት ፊቱን እንዲመቱት አደረገ፡፡ ሪዙን የሙብራት ክር በማድረግ ብዙ ሠም ካስቀባ በኋላ እንዲያያይዙት አደረገ፡፡ የሰደደለትንም መቀስ አስመጥቶ ምን ጊዜም ለእርሱ ስላቆየው እርሱም ሆነ ወታደሮቹ አልሰሩበትም እያለ ቅንድቡንና ሽፋሉን አስቆረጠው፡፡ ይህንን ሁሉ ካስደረገ በኋላ ለእረፍት ድንኳኖቹን ሁሉና የጦር አለቆቹን

እንዲጎበኝ አዘዘ፡፡ ከዚያም ብዙ የውርደት ሥራ ተሠራበት፡፡ (ዶም ክርስቶፍም) ከክርስቲያኑ አገር መቶ ማይል ከያዘ በኋላ ለዚህ ስላበቃው እግዚአብሔርን እያመሰገነ ይህንን ሁሉ በትዕግስት ተቀበለው፡፡ የጠላትም ጭፍሮች ጊዜውን በእርሱ ካሳለፉ በኋላ ወደ ግራኝ ድንኳን መልሰው አመጡት፡፡ ይህም ራሱን ለሌሎች ለማስቆረጥ የማይበቃው ስለሆነ እርሱ በእጁ ራሱን ቆረጠው፡፡[122]

ይህ የክርስቶፈር ዳ ጋማ ታሪክ በዚህች አገር ላይ ክርስትናን ለማቆየት ምን ያህል ዋጋ እንደተከፈለ ያሳየናል፡፡

በዚህ የግራኝ አስነዋሪና ዘግናኝ ድርጊት የተበሳጩ ብዙ ቱርኮች ግራኝን በመተው ወደ መጡበት እንደተመለሱ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ ለቱርኮች ከግራኝ መለየት አገሪቱ በድህነት መመታቷና የሚፈልጉትን ምርኮ ለማግኘት ተስፋ ሰጪ ሁኔታ አለመኖሩም እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡ ግራኝም የፖርቹጋሎችን መበታተንና የመሪያቸውን ሞት እንደ ጦርነቱ ፍፃሜ ስለቆጠረ ቱርኮች ወደ መጡበት በመመለሳቸው ቅሬታ አልነበረውም፡፡ ነግር ግን ቱርኮችን ማሰናበቱ ከባድ ስህተት ነበር፤ ዋጋም አስከፍሎታል፡፡[123]

ረጅሙ ታሪክ ሲቋጭ፤ የተረፉት የፖርቹጋል ወታደሮች ከንግሥት ሰብለ ወንጌልና ከልጇ ከአፄ ገላውዴዎስ ጋር ተገናኙ፡፡



D. CHRISTOVÃO DA GAMA'S AUTOGRAPH.
(From the Portuguese Official Records, traced from the Lisbon Geographical Society's Edition of Castanhoso's work.)
የክርስቶፈር ዳ ጋማ ፊርማ
የፎቶ ምንጭ Wikipedia.org

---

122 ሚጉኤል ዴ - ካስታንኋዞ፡፡ *የፖርቱጋሎች ጀግንነት*፣1952፣ ገፅ 68፤ በዶ/ር ሙራድ ከሚል እና በዮናስ ቦጋለ ወደ አማርኛ የተመለሰ
123 ይልማ ዴሬሳ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፤ ገፅ 187-189

የካቲት 22/ 1543 ዓ.ም. ወይና ደጋ በሚባል ቦታ በተደረገ ጦርነት 9,000 የነበረው የገላውዴዎስና የፖርቹጋሎች ሠራዊት አረቦችና ቱርኮች የተካተቱበትን 15,000 የግራኝ ሠራዊት ድል ነሳ፡፡ ግራኝም በውጊያው ላይ በአንድ የፖርቹጋል ወታደር በተተኮሰ ጥይት ከቆሰለ በኋላ አዝማች ካሊት የተባለ ሰው በሰይፍ ራሱን ቆረጠው፡፡ አገሪቱን እንደ አንበጣ አልብሷት የነበረው የጂሃድ ሠራዊት መሪው መሞቱን ባወቀ ጊዜ ወኔው ስለተሰለበ ተፍረክርኮ ከክርስቲያን ምድር ተጠራርጎ ወጣ፡፡ የግራኝ ሚስት ባቲ ድል ወንበራም ከተወሰኑ የቱርክ ወታደሮች ጋራ ከተዘረፈው ኃብት የቻለችውን ያህል በመውሰድ ወደ ሐረር ሸሽታ ከተመች፡፡[124]

ዛሬ ምን እየሆነ ነው? በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ ይህንን ታላቅ ጭፍጨፋ ያደረሰው አሕመድ ግራኝ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ በሚዘጋጁ ብዙ እስላማዊ የህትመት ውጤቶች ውስጥ እንደ ጀግና እየተወደሰ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ያህል አሕመዲን ጀበል “ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የጭቆናና የትግል ታሪክ” በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፉ ውስጥ “ታላቁ ወጣት ሙጃሒድ ኢማም አሕመድ በ37 ዓመቱ በፌብሩዋሪ 22/ 1443 ተሰዋ” በማለት ሙሾ ያወርድለታል፡፡[125] ሐሰን ታጁ የተሰኘ ጸሐፊም “ታላቁ ኢትዮጵያዊ ጀግና” በማለት ያወድሰዋል፡፡[126] ይኸው ጸሐፊ በሌላ መጽሐፉ የግራኝን ወንጀሎች ለማስተባበል ጥረት ሲያደርግ ይታያል፡፡ የአገራችንን ታላላቅ የታሪክ ጸሐፍትንም ታሪኩን በትክክል አላቀረቡም በሚል ከፉኛ ይወርፋል፡፡[127] ውዳሴ አሕመድ ግራኝ በግለሰቦች ብቻ ሳይሆን በመንግሥት በጀት በሚታተሙ የህትመት ውጤቶችም ውስጥ ይስተዋላሉ፡፡ ሺሃብ አድ-ዲን አሕመድ ቢን

---

[124] ዝኒ ከማሁ ገፅ 93-201

[125]አሕመዲን ጀበል፡፡ *ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከ615-1700 የጭቆናና የትግል ታሪክ፤* ቅፅ 1፣ 2003፣ ገፅ 212

[126] ሐሰን ታጁ፡፡ *የሐመረ ተዋሕዶን ቅጥፈት በእስልምና እውነት፤* አልበያን ሊሚትድ፣ አንደኛ ዕትም፣ 2002፣ ገፅ 86

[127] ሐሰን ታጁ፡፡ *ሰይፉን ፍለጋ፤ ከመካ እስከ ቫቲካን፤* አንደኛ ዕትም፣ 2006፣ ገፅ 332-234

አብደልቃድር በተሰኘ የአረብ ጸሐፊ ተጽፎ በሐረሪ ክልል ጉባኤ አማካኝነት “ሐበሻን የማቅናት ዘመቻ” በሚል ርዕስ ወደ አማርኛ የተመለሰው ባለ ሁለት ቅፅ የግራኝ ዜና መዋዕል ለዚህ እማኝ ነው፡፡ “ፉቱሑል ሐበሽ” የሚለው የመጽሐፉ የአረብኛ ርዕስ “የሐበሻ ሽንፈት” የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን ላዩን ለማሳመር “ሐበሻን የማቅናት ዘመቻ” ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ይህም ጦርነቱ የተደረገው ለሐበሾች ታስቦ እንደሆነ ያስመስላል፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ ሐበሾች ጠማሞች ናቸው የሚል ውስጠ ወይራዊ ስድብን ያዘለ ነው፡፡ ይህ የጂሃድ መጽሐፍ አዲሱን ትውልድ ለአመፅ ለማነሳሳት ታልሞ የተተረጎመ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሲደረግ ሀይ የሚል አካል መጥፋቱ ጂሃዳውያን በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ምን ያህል እንደተሰገሰጉና ጡንቻቸው ምን ያህል እንደፈረጠመ የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች በቸልታ የሚታለፉ ከሆነ ነገ መንግሥትንም ሆነ ሕዝብን ዋጋ ማስከፈላቸው የማይቀር ነው፡፡

አሕመድ ግራኝ በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ላይ “የተጫነውን የጭቆና ቀንበር” ለመስበር እንደተዋጋ የነፃነት አርበኛ እየተቆጠረ ሲሆን ነገር ግን ከአረብና ከቱርክ ተስፋፊዎች ጋር በመመሳጠር አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠል፣ ቅርሶችን በማውደም፣ ንብረት በመዝረፍ፣ ምዕመናንና ካህናትን በመግደል የፈፀመው የውድመትና የእልቂት ወንጀል ችላ እየተባለ ይገኛል፡፡ የጠቡም መነሻ ክርስቲያኖች እንደሆኑ በማስመሰል እየተነገረ ይገኛል፡፡ ነገር ግን በሰሜን የነበረውን የባህር በር በመያዝ ክርስቲያኑ መፈናፈኛ እንዲያጣ ያደረጉት ሙስሊሞች ነበሩ፡፡ በደቡብ የነበረውን የባህር በር የያዘው የእስላም ኃይል ከሰሜኑ የሚያንስ ስለነበረ በዚህ የባህር በር ለመጠቀም በዚያ አካባቢ የነበሩትን እስላማዊ አንጃዎች ማስገበር አስፈላጊ ስለነበር የክርስቲያን ነገሥታት ወታደራዊ ኃይላቸውን ተጠቅመዋል፡፡ ትኩረታቸውም የባህር በርና የንግድ መስመሮችን ከሥጋት ነፃ ማድረግ እንጂ ሙስሊሞችን ማጥፋት አልነበረም፡፡ የሰሜን ነገሥታት

በደቡብ ከነበሩት ሱልጣኔቶች ጋር በየጊዜው ውጊያ ቢገጥሙም ነገር ግን በግዛቶቻቸው ውስጥ የነበሩትን ሙስሊሞች በተመለከተ የተለየ ፖሊሲ ይከተሉ ነበር፡፡ አናሳ የነበሩት ሙስሊም ማሕበረሰቦች ከመንግሥታዊ ሥልጣን ቢገለሉም ነገር ግን በሙሉ ነፃነት ይንቀሳቀሱ እንደነበር የታሪክ ሃቅ ነው፡፡[128] አሕመድ ግራኝ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ላይ የፈፀመው ወረራ በአረቦችና በቱርኮች የታገዘ ክርስትናን ሙሉ በሙሉ የማጥፋትና በምትኩም እስልምናን የማስቀመጥ የጂሃድ ወረራ እንጂ ራስን የመከላከል ጦርነት አልነበረም፡፡ ያንን ዘመን የሚመኙና ለግራኝ የሚዘምሩለት የአገር ውስጦቹና የውጪዎቹ ጂሃዳውያን ቀን ቢሰጣቸውና እድል ቢያገኙ ተመሳሳይ ታሪክ ከመድገም ወደ ኋላ እንደማይሉና ክርስትናን ለማጥፋት የሚቋምጡ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ምቹ ጊዜ እስኪመጣላቸው ድረስ አጉርጠው አድብተዋል፡፡

---

128 M. Abir. *Ethiopia and the Read Sea;* p. 731

2

# ጂሃድ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ

የግራኝ ወረራ በወቅቱ ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርስም ነገር ግን በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የሃይማኖት ስብጥር ላይ የነበረው ተፅዕኖ የተጠበቀውን ያህል አልነበረም፡፡ ከግራኝ ሽንፈት በኋላ ሙስሊም ሱልጣኔቶች የተደካሙና እንቅስቃሴያቸውም የተገደበ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ቀድሞ ይዞታዋ ተመልሳለች፡፡ ይህ በንዲህ እንዳለ ቱርክን የመሳሰሉት የውጪ ጂሃዳውያን ኢትዮጵያን በማስለም ረገድ የነበራቸው ተስፋ እንዳልተሟጠጠ ታይቷል፡፡ ቱርኮች ተሸንፈው ከአገር ከተባረሩ በኋላ በ1557 የምፅዋን ወደብ የተቆጣጠሩ ሲሆን እስከ ደብረ ዳሞ ገዳም ድረስ ዘልቀው በመምጣት በመነኮሳቱ ላይ ጭፍጨፋ እንደፈፀሙና ገዳሙንም እንዳረከሱ፤ የወቅቱ ባህረ ነጋሽ የነበረው ይስሐቅም ድል በመንሳት ከአካባቢው እንዳባረራቸው የታሪክ ድርሳናት ይዘክራሉ፡፡[129] ከግራኝ ሽንፈት በኋላ የክርስቲያኑን ምድር ከበው የነበሩት ሙስሊም ማሕበረሰቦች ተዳክመው የነበረ ሲሆን የሰሜኑ ግዛት በደቡብ በነበሩት ሕዝቦች እንቅስቃሴ ከመረበሽ በስተቀር የገጠመው ያን ያህል የጎላ ችግር አልነበረም፡፡ ቤተ ክርስቲያን በአንድ አካባቢ ሕዝቦች ላይ ብቻ በማተኮር እንቅስቃሴዋ የተገደበ ባይሆን ኖሮ ዛሬ እስልምናን ተቀብለው የሚታዩትና ከሌሎች ጋር ተደባልቆ ለመኖር የማይቸገሩት ወርቃማ ባሕል ያላቸው የኦሮሞ ሕዝቦች ክርስትናን ይቀበሉ እንደነበር ትሪሚንግሃም የተሰኙት የታሪክ ሊቅ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡[130]

---

129 Trimingham. *Islam in Ethiopia;* p. 92
130 Ibid., p. 114

# የግብፅ ወረራዎች

በአባይ ወንዝ ላይ ካላት ጥቅም የተነሳ ግብፅ ኢትዮጵያን የመቆጣጠርና የማስለም የረጅም ጊዜ ምኞት እንደ ነበራት ይታወቃል፡፡ በተለያዩ ዘመናት የተነሱት የግብፅ ገዢዎች ኢትዮጵያን በኃይል መቆጣጠር ቀላል እንዳማይሆንላቸው ይገባቸው ስለነበር የማስለም መርሃ ግብሩን በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ያስፈፅሙ እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡ በተለይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳትን ስታገኝ የነበረው በገዢዎቹ መልካም ፈቃድ ስለነበረ ከእነዚህ ጳጳሳት ጋር የተለያዩ ስምምነቶችን በማድረግ እስልምናን የማስፋፋት ሙከራዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህል አባ ሳዊሮስ የተሰኙ ጳጳስ (1080 ዓ.ም.) ገና ተሹመው ከመምጣታቸው ሰባት መስጊዶችን አስገንብተው የነበረ ሲሆን ይህ ድርጊታቸው የሕዝቡን ቁጣ በመቀስቀሱ ምክንያት ለእስር ተዳርገው መስጊዶቹም ፈርሰዋል፡፡[131] ነገር ግን ከግብፅ የሚመጡት ጳጳሳት እንዲህ ያለውን ድርጊት የሚፈፅሙት ወደው ሳይሆን ሙስሊም ገዢዎች በግብፅ ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን እንደ መያዣ በመጠቀም ስለሚያስገድዷቸው ነበር፡፡ የግብፅ ሙስሊሞችም ክርስቲያን በመምሰል ወደ አገር ውስጥ የገቡባቸውና በቤተ ክርስቲያን ላይ ጉዳት ያደረሱባቸው ጊዜያትም ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህል አብዱን የተሰኘ ሙስሊም፣ ክርስቶዱሎስ (1047-78 ዓ.ም.) በተሰኙት ጳጳስ ዘመን በሀሰተኛ ሰነዶች ተጠቅሞ በመግባትና ተቀባይነትን በማግኘት ለጳጳሱ አገልግሎት እንቅፋት ሆኖ እንደነበር በታሪክ ሰፍሯል፡፡[132]

በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሙሐመድ አሊ የተባለ ሰው የግብፅን በትረ ሥልጣን በመጨበጥ ግዛቱን የናይል ተፋሰስ አገራት ውስጥ ለማስፋፋት እቅድ ይዞ ተነስቶ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ሱዳንን በመያዝ በ1830 ነጭ አባይና ጥቁር

---

131 Ibid., p. 63
132 Ibid.

አባይ በሚገናኙበት ቦታ ላይ የካርቱም ከተማን ቆረቆረ፡፡ ልጁ ኢብራሂምንም “የሂጃዝና የአቢሲኒያ አስተዳዳሪ” በማለት ከሾመ በኋላ ኢትዮጵያን የመውረር እቅዱን ለአውሮፓውያን ሸሪኮቹ ግልፅ አደረገ፡፡ ነገር ግን በወቅቱ በካይሮ የብሪቲሽ ቆንስላ ጄኔራል የነበረው ሳልት እቅዱን በመቃወም አውሮፓውያን ኃይላት ለዘመናት ክርስትናዋን ጠብቃ የቆየች ብቸኛዋ አፍሪቃዊት አገር እንድትወረር እንደማይፈቅዱ ገለፀለት፡፡[133] ነገር ግን አውሮፓውያን ጥቅማቸው እስካልተነካ ድረስ ለክርስትና ግድ እንደሌላቸው በኋለኞቹ ዘመናት ግልፅ ሆኗል፡

ሙሐመድ አሊ በሦርያ ያደረገው ወረራ ስላልተሳካለት ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በ1838 በሱዳን በኩል ቀለበት በተባለ የድንበር መግቢያ ወራሪ ሠራዊቱ ወደ አገር ውስጥ እንዲዘልቅ አድርጓል፡፡ ወረራው በጎንደር ከተማ ውስጥ ከፍተኛ ሽብርን ያስከተለ ሲሆን ጂሃዳውያኑ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን የማርከስ አስነዋሪ ተግባራትን ፈፅመዋል፡፡ ይህ ደግሞ በሕዝቡና በመሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ቁጣን ቀስቅሶ በደጃች ክንፉ የተመራ ሠራዊት በወኔና በቁጭት ክፉኛ በመቅጣት አባሯቸዋል፡፡ ሙሐመድ አሊ ሽንፈቱን ለመበቀል ቢፈልግም ነገር ግን ፈረንሳይና ብሪቴን ጫና ስላሳደሩበት እቅዱን ሳይፈፅም ቀርቷል፡፡[134]


ከዲቭ ኢስማኤል (ኢስማኤል ፓሻ)

ግብፅ ኢትዮጵያን የመውረር እቅዷን እንደገና በኢስማኢል ፓሻ ዘመን ለመተግበር የተንቀሳቀሰች ቢሆንም ህዳር 16/ 1875 በምዕራባውያን ቅጥረኞች

---

133 Ibid., pp. 114-115
134 Ibid., pp. 115-116

እየተመራ በምፅዋ በኩል የገባው የግብፅ የጂሃድ ሠራዊት ጉንደት በተባለ ቦታ ላይ የአፄ ዮሐንስን ሠራዊት በመግጠም ሙሉ በሙሉ ተደመሰሷል፡፡ የመጀመርያውን ሽንፈት ለመቀልበስ ለሁለተኛ ጊዜ መጋቢት ወር ላይ ተመልሶ የመጣውም ወረሪ የጂሃድ ሠራዊት ጉራ በተባለ ቦታ ላይ ተደመሰሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ግብፅ ጦር አዝምታ ኢትዮጵያን ለማስለም የነበራት ምኞት ሊከሽፍ ችሏል፡፡[135]

## የሱዳን መሐዲስቶች ጥቃት

ግብፅ ሱዳንን በመያዟ ምክንያት የመሐዲ እንቅስቃሴ ሱዳን ላይ ተነስቶ ነበር፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ዋና አላማው በእንግሊዛውያን የምትደገፈውን ግብፅን ማሸነፍ ቢሆንም አፄ ዮሐንስ በመሐዲዎች የተከበበውን የግብፅ ሠራዊት በኢትዮጵያ ግዛት በኩል ለማስወጣት ያደረጉት ስምምነት መሐዲስቶች ትኩረታቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመልሱ ምክንያት ሆኗል፡፡ በወቅቱ የጎጃም ንጉሥ የነበሩት ተክለሃይማኖት በጥር ወር 1887 የመሐዲስቶች ይዞታ በነበረችው የመተማ ከተማ ላይ ጥቃት ፈፅመው ነበር፡፡ በቀጣዩ ዓመት የመሐዲስቶች ሠራዊት እስከ ጎንደር ድረስ ዘልቆ በመግባት አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥሏል፣ ሕዝበ ክርስቲያኑን ጨፍጭፏል፣ ብዙዎችንም ማርኮ ለባርነት ወስዷል፡፡ በዚህም ምክንያት መጋቢት 9 እና 10 በመተማ ላይ በተደረገው ጦርነት አፄ ዮሐንስ ሕይወታቸውን ያጡ ሲሆን መሐዲስቶችም ራሳቸውን በመቁረጥ ወደ ሱዳን ወስደዋል፡፡ የመሐዲስቶቹ ትኩረት ዋና ጠላታቸው ወደሆነችው ወደ ግብፅ ስለተመለሰ ኢትዮጵያን ከመውረር ታቅበዋል፡፡[136] ግብፅና ሱዳን ሙሉ በሙሉ በብሪቲሽ ቅኝ ግዛት ስር ከገቡ በኋላ በውጪ እስላማውያን ኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰው የጂሃድ ስጋት ለጊዜውም ቢሆን ጋብ ማለቱ አልቀረም፡፡

---

[135] Ibid., pp. 120-121
[136] Ibid., p. 116-125

# የልጅ ኢያሱ የማስለም ሤራ

ሌላው ለኢትዮጵያ ክርስትና በጣም አደገኛ ዘመን እንደነበረ የሚነገረው የልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት ነበር፡፡ አፄ ሚኒሊክ የአልጋ ቁራኛ ከሆኑ በኋላ በ1907 የልጅ ልጃቸው የነበሩትን ልጅ ኢያሱን የአልጋ ወራሽ፤ ራስ ተሰማን ደግሞ እንደራሴ አድርገው ሹመው ነበር፡፡ በ1911 የራስ ተሰማን ሞት ተከትሎ ልጅ ኢያሱ ከእስልምና ወደ ክርስትና ከመጡት ከአባታቸው ከራስ ሚካኤል ጋር በመሆን ሥልጣናቸውን ካጠናከሩ በኋላ ወደ እስልምና እምነት ማድላት እንደጀመሩ የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ትሪሚንግሃም ይናገራሉ፡፡


ልጅ ኢያሱ

በጸሐፊው መሠረት ልጅ ኢያሱ ወደ ሐረር ከተማ በመሄድ እስልምናን መለማመድ ጀምረው ነበር፡፡ ክርስቲያን የነበሩትን ባለቤታቸውን ሮማን ወርቅን ገሸሽ በማድረግ ሙስሊም ሴቶችን አግብተዋል፡፡ መስጊዶችንም በድሬ ደዋና በጅጅጋ አስገንብተዋል፡፡ በዚህ ሳያበቁ ኢትዮጵያ በሃይማኖት ከቱርክ ስር መሆኗን ለማመልከት በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ የጨረቃ ምልክትና የእስልምናን የእምነት መግለጫ (ላኢላሀ ኢለላ መሐመደን ረሱል አላህ) በማድረግ ለቱርክ ቆንስላ ጄነራል ላኩለት፡፡ ለራሳቸው ሙስሊም ባለሥልጣናትም ተመሳሳይ ባንዲራዎችን በመላክ ለጂሃድ እንደሚመሯቸው ቃል ገቡ፡፡ ከኦጋዴኑ የሶማሌ መሐዲ ሙሐመድ ኢብን አብደላህ ጋር ስምምነት በማድረግም ጠብመንጃዎችንና ጥይቶችን ላኩለት፡፡ በክርስቲያኖች ላይ ለሚያደርጉት ጂሃድ እንዲከተሏቸውም

ለሶማሌዎች ጥሪ አቀረቡ፤ ወደ ጂጂጋም በመሄድ ሠራዊት መለመሉ፡፡ በመጨረሻም እቅዳቸው ግቡን ሳይመታ ከሥልጣን እንዲወርዱ ተደረገ፡፡[137]

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ከተጻፉት የታሪክ መጻሕፍት በመነሳት የልጅ ኢያሱን ታሪክ ከላይ በተቀመጠው መልኩ ማየት ሚዛናዊነት እንደሚጎድለው ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም አንባቢያን ታሪኩን ከሌላ ፅንፍ የሚያሳዩ ምንጮችን እንዲያገናዝቡ እንመክራለን፡፡

## የፋሺስት ኢጣሊያ እስላማዊ ተልእኮ

በኢጣሊያ ወረራ ወቅት በኢትዮጵያ ክርስትና ላይ የተደቀነው አደጋ ቀላል አልነበረም፡፡ ቤኒቶ ሞሶሎኒ ኢትዮጵያን ለመውረር ዝግጅት ሲያደርግ ሳለ በአገር ውስጥና በውጪ አገራት ከነበሩት ሙስሊሞች ዘንድ ድጋፍ ለማሰባሰብ የተጠቀመው ዘዴ የኢትዮጵያን ክርስትና በማዋረድ እስልምናን ከፍ እንደሚያደርግ ቃል መግባት ነበር፡፡ የሞሶሎኒን የወረራ እቅድ በመቃወም ከኢትዮጵያ ጎን የተሰለፉ አረብ ሙስሊሞች ቢኖሩም ነገር ግን ብዙዎቹ ለወራሪው ኃይል ድጋፍ ሰጥተዋል፡፡ ልጅ ኢያሱም ትክክለኛው የኢትዮጵያ መሪ መሆኑን በማወጅ እስላማዊውን አገዛዝ እንደሚመልስ ቃል መግባቱ በሐረር፣ በኦጋዴን፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ሙስሊሞችና በአዲስ አበባ ይኖሩ በነበሩት አረብ ነጋዴዎች ዘንድ ተቀባይነትን አስገኝቶለት እንደነበር የኢጣሊያ ምንጮች ይገልፃሉ፡፡ ከጦርነቱ በፊት አፄ ኃይለ ሥላሴ ሚያዝያ 7/ 1935 ወደ ሳውዲ አረብያ የላኩት የልዑካን ቡድን ምንም ተስፋ ሰጪ ነገር ሳያገኝ ወደ ካይሮ አቅንቷል፡፡ በወቅቱም ንጉሥ ኢብን ሳውድ የልዑካን ቡድኑ አባል ለነበሩት ለኢትዮጵያዊው ሙስሊም ለአሕመድ ሳሊቅ፡- “ኢትዮጵያ በሙስሊሞች ላይ የፈፀመችውን ሁሉ አውቃለሁ፤ አባ ጂፋር ከሥልጣን ወርዷል ልጆቹም ከአገር

---

137 Ibid., 130-131

ተሰደዋል፡፡ ለክፍለ ዘመናት የኖረው የጅማ እስላማዊ መንግሥት ጠፍቷል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የረባ ሥልጣን ያለው ሙስሊም የለም፡፡ ኢትዮጵያን ልረዳት አልችልም” በማለት መናገራቸው ተመዝግቧል፡፡ ይህም ለሞሶሎኒ አስደሳች ዜና ነበር፡፡[138]

ኢትዮጵውያኑ ባዶ እጃቸውን ከሳዑዲ በተመለሱ ልክ በወሩ በልኡል ሳዑድና ሐምዛ በተባለ ኢትዮጵያን በሚጠላ ሰው የሚመራ የልዑካን ቡድን ሮም ደረሰ፡፡ ሞሶሎኒ “ትክክልኛ የእስልምና ወዳጅ እንደሆነና በክርስትና ቀንበር ስር ለሚሰቃዩት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ትክክለኛ ጠባቂ” እንደሆነም ተገለፀ፡፡ ሳዑዲ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት በሁለት ክርስቲያን አገራት መካከል የሚደረግ ጦርነት መሆኑን በመግለጽ ገለልተኛነትን ትመርጣለች በሚል ሰበብ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንደምታቋርጥ፤ ለኢጣሊያ ወታደሮች የሚሆን ምግብ እንደምትሸጥ፤ ፀረ ኢጣሊያ የሆነን የትኛውንም ፕሮፓጋንዳ እንደምታግድ፤ በምትኩም ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ኢጣሊያ ለሳዑዲ አየር ኃይል ድጋፍ እንደምታደርግና መሣርያ በመስጠት ውለታዋን እንደምትመልስ የሚገልጽ ምስጢራዊ ስምምነት ተደረሰ፡፡ ሳዑዲ 12,000 ግመሎችን ለሞሶሎኒ ለመሸጥ በመስማማት ድጋፏን ቸራለች፡፡ በቀጣዩ ክረምት ንጉሡ ሌላ የልዑካን ቡድን ወደ ሳዑዲ ቢልኩም ነገር ግን ውጤት አልነበረውም፡፡ በ1935 ኢትዮጵያን የወረረው የሞሶሎኒ ሠራዊት ከሶማሊያ፣ ከኤርትራና ከሊብያ የተውጣጡ ቁጥራቸው ከሰባ ሺህ በላይ የሚሆኑ ሙስሊም ወታደሮችን ያካተተ ነበር፡፡[139]

ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረባቸው በነዚያ አምስት ዓመታት እስልምናን ለማስፋፋት ጥረት ያደረገ ሲሆን አብያተ ክርስቲያናትን አውድሟል፤ ብዙ ክርስቲያኖችንም በጥይት፣ በመድፍና በመርዝ ጋስ ጨፍጭፏል፡፡ በአርሲና

---

138 Erlich. *Saudi Arabia & Ethiopia;* pp. 39-45
139 Ibid., p. 46-67

በሲዳማ አካባቢ የነበሩት ሕዝቦች እንዲሰልሙ ይበረታቱ ነበር፡፡ በሦስት ግዛቶችም ላይ እስልምና አፌሴላዊ ሃይማኖት ሆኖ ታውጆ ነበር፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ ጣሊያኖች እስላማዊ ትምህርት ቤቶችን ይደጉሙ ነበር፡፡ ሙስሊሞችም እስላማዊውን ሕግ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር፡፡ የሐጅ ቢሮ እንደ አዲስ በመደራጀት ተጓዦች በብዛት እንዲሄዱ ይበረታቱ፤ ድጋፍም ይደረግላቸው ነበር፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኘውን ታላቁን የአንዋር መስጊድን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ መስጊዶች በመላ አገሪቱ እንዲገነቡ ተደርጓል፡፡ ለአንዋር መስጊድ ግንባታ ሞሶሎኒ በግሉ ድጋፍ አድርጓል፡፡ የሐረር ከተማ "የቁርአንን ብርሃንና የእስልምናን ሥልጣኔ የምታበራ" የእስልምና ቅድስት ከተማ እንደምትሆን በግራዚያኒ ቃል ተገብቶ ነበር፡፡ አረብኛ የመማርያና የሥራ ቋንቋ



ቤኒቶ ሞሶሎኒ "የእስላም ሰይፍ" የሚል መፈክር በማሰማት ራሱን የእስላም ጠባቂ አድርጎ ያወጀበት የትሪፖሊ ትዕይንት

እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የአረብኛ መጻሕፍትና ጋዜጦች ይታተሙ ነበር፡፡ የአረብኛ ሬዲዮ ጣብያዎችም ተቋቁመው ነበር፡፡ ሁሉም ጋዜጦች አንድ የአረብኛ አምድ እንዲኖራቸው ግዴታ ሆኖ ነበር፡፡ በ1936 ግራዚያኒ የዒድ አል ፈጥር በዓል ላይ ለመጀመርያ ጊዜ መድፍ እንዲተኮስ አድርጓል፡፡ ወራሪዎቹን የተቃወሙ የኃይማኖት አባቶችና ካህናት በጅምላ ተጨፍጭፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ጋር የነበራት ታሪካዊ ትስስር እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ባጠቃላይ ያ ዘመን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጭንቅ ዘመን ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ በ1937 ሞሶሎኒ ሊብያን በጎበኘበት ወቅት ፈረስ እየጋለበ "የእስላም ሰይፍ!" የሚል መፈክር በማሰማት "በሊብያና በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተረጋገጠው፤

ካሊፌት ከጠፋ ወዲህ የእስልምና ዋና ጠባቂ" እርሱ መሆኑን ያወጀበት ትርዒት የሞሶሎኒን እስላማዊ ፕሮፓጋንዳ ከፍታ ጫፍ ያሳየ ነበር፡፡[140] ነገር ግን ፋሺስት ኢጣሊያ በቂ ጊዜ ስላላገኘ አገሪቱን የማስለም እቅዱ ግቡን ሳይመታ ቀርቷል፡፡

## የዚያድ ባሬና የሶማሊያ የሽብር ቡድኖች ሙከራ

ዚያድ ባሬ "ታላቋ ሶማሊያን" የመመሥረት እቅዱን ለማሳካት የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ውድቀትና የአገሪቱን አለመረጋጋት ተከትሎ በ1977 በአገሪቱ ላይ ጦርነትን አውጆ ብዙ አካባቢዎችንም ተቆጣጥሮ ነበር፡፡ ነገር ግን ከስምንት ወራት እልህ አስጨራሽ ፍልሚያ በኋላም ተሸንፎ ከአገሪቱ ሊወጣ ችሏል፡፡ የኢትዮጵያን ግዛቶች ቆርሶ የእስላማዊቷ ሶማሊያ አካል የማደረግ ህልሙም መና ቀርቷል፡፡ ከዚያድ ባሬ ውድቀት በኋላ በሳዑዲ አረብያ መንግሥትና ካርቱም ላይ በነበረው የአልቃኢዳ እርዳታ የተለያዩ እስላማዊ የሽብር ቡድኖች ሶማሊያ ውስጥ ተመስርተው ነበር፡፡ ከነዚህ መካከል  አል-ተክፊር ወል ሒጅራ፣ አል-ኢስላህ እና አል-ተብሊሂ ይጠቀሳሉ፡፡[141]

በዚያድ ባሬ አስተዳደር ከአገር የተሰደዱት ግለሰቦችና በኦጋዴን ውስጥ የተሸነፉት ሶማሌ ታጣቂዎች በመተባበር በሳዑዲ አረብያ ውስጥ በ1978 አል-ኢትሃድ አል-ኢስላሚ (እስላማዊ ሕብረት) የሚል የሽብር አንጃ በማቋቋም በኢትዮ-ሶማሌ ድንበር አካባቢ መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር፡፡ ይህ የሽብር ቡድን የሶማሊያን ሽብርተኞች ከዓለም አቀፉ የሽብር መረብ ጋር አስተሳስሮ ነበር፡፡ በ1980ዎቹ ውስጥ ደግሞ የተወሰኑ የሶማሌ "ሙጃሂዲኖችን" በአፍጋኒስታን ጦርነት ውስጥ እንዲሳተፉ ልኮ ነበር፡፡ በ1984 ብዙ የሽብር ቡድኖችን አባል በማድረግ ኃይሉን ያጠናከረ ሲሆን አልቃኢዳን ለመሳሰሉት የሽብር ቡድኖች እርዳታን በመስጠት

---

140 Ibid., 67-61

141 Ibid., p. 205

በሚታወቁት አል ሐራሚን የተባለውን የሳዑዲ አረብያ የእርዳታ ድርጅትን በመሳሰሉት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይታገዝ ነበር፡፡ በ1991 ዚያድ ባሬ ከወደቀ በኋላ ህልውናውን ይፋ በማድረግ ሼኽ ዳሂር አዌይስን መሪው አድረጎ ሾመ፤ በኢትዮጵያ ላይም ጂሃዳዊ ጥቃቶቹን መፈፀም ጀመረ፡፡ በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ላይ ብዙ ጥቃቶችን ከፈፀመ በኋላ በ1995-1996 ዓ.ም. (የዘመን አቆጣጠሮቹ እንደ ጎርጎሮሳውያኑ አቆጣጠር መሆናቸው ይታወስ) በአዲስ አበባ ከተማም ውስጥ የቦምብ ጥቃቶችን ፈፀመ፡፡ እነዚህ ሁሉ የሽብር ጥቃቶች አል ሐራሚን በተባለው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትና በአልቃኢዳ ይደገፉ እንደነበር ይነገራል፡፡ ኋላ ላይም የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ሶማሊያ በመግባት ብዙ የአል-ኢትሃድን ካምፖች አጥፍቷል፡፡ ሽብርተኞቹንም ድል በመንሳት በታትኗቸዋል፡፡ የተበታተኑትም ሽብርተኞች ኋላ ላይ በመሰባሰብ "የእስላማዊ ፍርድቤቶች ሕብረት" የተባለውን ድርጅት የመሠረቱ ሲሆን ይህ የሽብር ቡድን በኢትዮጵያና በአሜሪካ የሚደገፈውን የሶማሊያ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት በማስወገድ ሞቃዲሾን ተቆጣጥሮ በሸሪኣ የሚመራ መንግሥት መሥርቶ ነበር፡፡ አጋዴንም የአዲሱ ካሊፌት አካል እንደሆነ በማወጅም በኢትዮጵያ ላይ ጂሃድን አውጆ ነበር፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በ2006 ወደ ሶማሊያ በመግባት ዓለምን ባስደመመ ፍጥነት ድል ነስቶ በታትኖታል፡፡ የሽግግር መንግሥቱም መልሶ ቦታውን እንዲይዝ አድርጓል፡፡[142]

[142] Ibid., 204-207

3

# ወሃቢዝም በኢትዮጵያ ውስጥ

ኢህአዴግ ደርግን በማስወገድ አገሪቱን ከተቆጣጠረ ወዲህ ለሁሉም ሃይማኖቶች እኩልነትን በማወጅ ለተግባራዊነቱ ብርቱ ጥረት ማድረጉ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በአገሪቱ ውስጥ የሰላምና የነፃነት አየር ነፍሷል፡፡ ነገር ግን ይህንን ነፃነት የለአግባብ የተጠቀሙና የጥፋት መርዛቸውን በትውልዱ መካከል ለማሰራጨት የተጉ፣ ከዚህም የተነሳ ብዙ ጥፋቶችን ያስከተሉ ቡድኖች መኖራቸው አልቀረም፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ የወሃቢዝም (ሰለፊ) ፍልስፍናን የሚከተሉ ወገኖች ይጠቀሳሉ፡፡ ዛሬ በአገሪቱ ውስጥ በብዛት ተሰራጭቶ በሕዝቦች መካከል ያለውን የመቻቻልና አብሮ የመኖር ባሕል እያደፈረሰ የሚገኘው ወሃቢዝም ይህንን ነፃነት ተጠቅሞ የተስፋፋ ይሁን እንጂ እግሩን  በአገሪቱ ውስጥ ካሳረፈ ብዙ አሥርተ ዓመታት አልፈዋል፡፡

## በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን


ቀደም ሲል እንደገለፅነው ፋሺስት ኢጣሊያ ሙስሊሞች የሐጅ ጉዞ እንዲያደርጉ ያበረታታ ነበር፡፡ በገንዘብም በመደጎም ይልክ ነበር፡፡ በ1933 ለሐጅ ወደ መካ የተጓዙት ኢትዮጵያውያን ቁጥር 11 ብቻ ሲሆን ከ1934-1935 የሄዱት 29፣ ከ1935-1936 ደግሞ 7 ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ነገር ግን በ1937 ይህ ቁጥር ወደ 1,700 አድጓል፡፡ ሁሉም ደግሞ በኢጣሊያ መንግሥት ድጎማ የሄዱ ነበሩ፡፡[143] ሳዑዲ አረብያ ለሐጅ የሚሄዱትን ኢትዮጵያውያን በወሃቢዝም ፍልስፍና አጥምቃ ወደ አገር ውስጥ በማስረግ ፍልስፍናውን የማስፋፋት ሥራዋን የጀመረችው ኢጣሊያ

143 Ibid., p. 73

ኢትዮጵያን ከመውረሯ በፊት ነበር፡፡ በተለይም ደግሞ ሼኽ ዩሱፍ አብደል ረህማንና ሐጂ ኢብራሂም ሐሰን የተሰኙ ሁለት ሰዎች ለዚህ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ሁለቱም ወደ ሳዑዲ የተጓዙት በ1930ዎቹ መጀመርያ አካባቢ ነበር፡፡ ሼኽ ዩሱፍ በ1939 ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በሐረር ከተማ የወሃቢዝም ትምህርታቸውን ማስተማር የጀመሩ ሲሆን የሐረርን ከተማ የቀድሞ ነፃነት ለመመለስ የከተማይቱን ሙስሊም ሊቃውንት አደራጅተው ፊርማ በማሰባሰብ በወቅቱ የብሪቲሽ የአካባቢው አማካሪ ለነበሩት ለኮሎኔል ዳላስ ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ ነገር ግን ኮሎኔሉ ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር ሼኽ ዩሱፍ ለረጅም ጊዜ ትግል መሠረት ለመጣል የወሰኑት፡፡ ከዚያም ብሔራዊ እስላማዊ ማሕበር (አል-ጀማዒያ አል-ወኒያ አል-ኢስላሚያ) ወይም አል-ዋታኒ የተሰኘ ማሕበር በማቋቋም መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡ የማሕበሩ አባላት በሙሉ ሐረርን “ከኢትዮጵያ ቅኝ” ነፃ በማውጣት አሕመድ ግራኝ ባስቀመጠው ምሳሌነት መሠረት እስላማዊ መንግሥት እንደገና ለማቋቋም ቃል ኪዳን ገቡ፡፡ የሐረርን ሕዝብ በሚገባ ሳያስተምሩ መንግሥትን መጋፈጥ እንደማይቻል ስለተገነዘቡም ዋታኒ እስላማዊ ማሕበር ቀደም ሲል የተሠራውን ትምህርት ቤት በመጠቀም እስላማዊውን ትምህርት በማስተማር ላይ እንዲያተኩር ተወሰነ፡፡ ትምህርት ቤቱም ዘመናዊ መልክ ኖሮት አረብኛና በሐጂ ኢብራሂም ሐሰን አማካይነት ደግሞ የወሃቢዝም ትምህርት እንዲሰጥ ተባለ፡፡ ሐጂ ኢብራሂምም በከፍተኛ ትጋት በየምሽቱ በቤታቸውም ጭምር ይህንን ፍልስፍና ማስተማር ተያያዙ፡፡ የግራኝ ታሪክና ወታደራዊ አካሄድ እንደ አንድ ዋና ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ ዋታኒ እስላማዊ ማሕበር በሚያዘጋጃቸው ክብረ በዓላት ላይ በአሕመድ ግራኝ ዙርያ የሚያጠነጥኑ ግጥሞችና የውዳሴ መዝሙሮችም ተዘጋጅተው በተማሪዎች ይዘመሩ ነበር፡፡ ሼኽ አብደል ረህማን ደግሞ በአዲስ አበባ ውስጥ በነበራቸው የመጻሕፍት መደብር አማካይነት በአረብኛ የተዘጋጁ የወሃቢያ መጻሕፍትን እያስመጡ ያከፋፍሉ ነበር፡፡

ኋላ ላይ የትምህርት ሚኒስቴር ሆነው የተሾሙት ከበደ ሚካኤል ትምህርት ቤቱን በጎበኙበት ወቅት ለግራኝ የሚዜሙትን መዝሙሮች ትርጉም ከሰሙ በኋላ እንዳይዘመሩ ያገዱ ሲሆን አማርኛም የመማርያ ቋንቋ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር፡፡[144]

ነገር ግን ከመንግሥት ይልቅ የዋሃቢዝም ዋና ጠላት የነበሩት ሼኽ አብደላህ ኢብን ሙሐመድ ኢብን ዩሱፍ (አብደላህ አል-ሐረሪ) የተሰኙ ሙስሊም ሊቅ ነበሩ፡፡ እኚህ ሰው የአገራችን አብዛኛው ሙስሊም የሚከተለው በአንፃራዊነት ሰላማዊ ሊባል የሚችለው የሱፊ እስልምና ተከታይ ሲሆኑ ከፀረ ሰላም ትምህርቱ በተጨማሪ አሁን በዝርዝር የማናያቸውን የወሃቢዝም አስተምህሮዎች ይቃወሙ ነበር፡፡ ሼክ አብደላህ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ውሏቸውን በመርካቶ አካባቢ በማድረግ ሙስሊሙን ህብረተሰብ በማስተማር ዝነኛ ሆነው ነበር፡፡ ኋላም ወደ ሊባኖስ በማቅናት በመካከለኛው ምስራቅ ትምህርታቸውን በማስፋፋት በዓለም ላይ ዋነኛ ፀረ ወሃቢዝም ለሆነው ዓለም አቀፍ እስላማዊ ማሕበር ሊቀ መንበር ሆነዋል፡፡[145] የኚህን



ሼኽ አብደላህ አል-ሐረሪ

ኢትዮጵያዊ ትምህርት አረቦች “አሕባሽ” በማለት ይጠሩታል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሐጂ አብደላህ ከሐበሻ ምድር የመጡ መሆናቸው ነው፡፡ ትምህርቱ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት የኖረውና አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝበ ሙስሊም የሚከተለው የሱፊ እስልምና እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ትምህርቱን የተቀበሉና

144 Ibid., 80-83
145 Ibid., 84

ከኢትዮጵያዊው የተማሩ ሊቃውንት ስልጠናዎችን ለመስጠት ከሊባኖስ በመጡበት ወቅት ወሃቢዮች “መንግሥት አሕባሽ የሚባል አዲስ ሃይማኖት አመጣብን” በማለት ሁከት መፍጠር ጀመሩ፡፡ እነርሱ ባለ አገር ሆነው የአገሪቱን የሱፊ ሊቃውንት ማሳደድና መግደል ተያያዙ፡፡

ሼኽ አብደላህ በአንድ ወቅት በሐረር ውስጥ በነበረው የወሃቢዮች ትምህርት ቤት ላይ ባስነሱት ተቃውሞ ምክንያት ለእስር ተዳርገው ነበር፡፡ አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ ሐጂ ኢብራሂም ለአንድ የአረብኛ ጋዜጣ በጻፉት መጣጥፍ ክርስቲያናዊት ኢትዮጵያንና ንጉሡን ማጣጣላቸውን ለመንግሥት መረጃ እንደሰጡም ይነገራል፡፡ በዚህም ምክንያት ሐጂ ኢብራሂምና የትምህርት ቤቱ የወሃቢያ መምህራን ታስረው ለፍርድ የቀረቡ ሲሆን ሐጂ ኢብራሂም ከሐረር ከተማ ወደ ሌላ የኢትዮጵያ ክፍል ሄደው እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል፡፡ እኚህ ሰው አሁን በሕይወት የሉም፡፡ ኋላ ላይ ሼኽ አብደላህ የሐረር ከተማ ሙፍቲ ሆነው በመሾማቸው ምክንያት ወሃቢዮች ድምፃቸውን አጥፍተው ለመኖር የተገደዱበት ሁኔታ ነበር፡፡ የሐረር ወሃብዮች በ1948 “የሶማሌ ወጣቶች ክበብ” ተብሎ በመንግሥት ፈቃድ በተቋቋመው ቡድን ውስጥ እጃቸውን አስገብተው የነበረ ሲሆን የአሕመድ ግራኝ “መንፈስ” እንደገና በመምጣት ከተማይቱ ላይ አንዣቦ ነበር፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ይፋ በመሆኑ ጥር 1948 ዓ.ም. 200 የሚሆኑ የክበቡ አባላት በቁጥጥር ስር ዋሉ፡፡ ወጣቶቹ ይቅርታ በመጠየቅ የተፈቱ ሲሆን 81 የሚሆኑ የወሃቢያን እንቅስቃሴ የሚመሩ የዋታኒ ማሕበር አባላት ከተማይቱን በመልቀቅ እንዲበተኑ ተደርጓል፡፡ በዚሁ ዓመት ኢትዮጵያ የኦጋዴን ግዛቷን በማግኘቷ ምክንያት በሐረር ላይ ያላት ሙሉ ቁጥጥር እውን ስለሆነ በ1936 በሐረር ከተማ የተጀመረው በወሃቢዝም የተመራው የእስላማዊ ፖለቲካ መነቃቃት ሊከሽፍ ችሏል፡፡[146]

146 Ibid., 85-92

## በዘመነ ደርግ

የደርግ መንግሥት ባጠቃላይ ሃይማኖትን በተመለከተ ይከተል ከነበረው ፖሊሲ የተነሳ ያን ያህል የጎላ የወሃቢዝም እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ የተሠሩ ሥራዎች እንደነበሩ እሙን ነው፡፡ በ1958 ከየመን በመጣ ስደተኛ የተመሠረተው የአል-አወልያ ትምህርት ቤት በዘመነ ደርግ ጥብቅ በሆነ የመንግሥት ቁጥጥር ስር ነበር፡፡[147] ደርግ ወደ መውደቂያው አካባቢ "የሰርገኛ መጣ..." ዓይነት የፖሊሲ ለውጦችን በማድረጉ ምክንያት ለሳዑዲ እንቅስቃሴዎችም በር ከፍቶ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት የዓለም የሙስሊሞች ሊግ ከእርዳታ ማስተባበርያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን (እማማኮ) ጋር በመተባበር ትምህርት ቤቶችን፣ እጓለ ሙታንንና ክሊኒኮችን ለማቋቋም ስምምነት አደረገ፡፡ መንግሥትና ሊጉ ያላቸው ግንኙነት መጥበቁን ከሚያመለክቱ ተግባራት መካከል አንዱ ሊጉ የሃይማኖትና የአረብኛ ቋንቋ ሥልጠናዎችን እንዲሰጥ መፈቀዱ ነበር፡፡ በ1991 ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት የመጣው የሊጉ ልዑካን ቡድን በወሎ፣ በሐረር፣ በአዲስ አበባና በደብረ ዘይት ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ሥራ ላይ መሆኑን መግለፁ ኢትዮጵያን የማስለም እንቅስቃሴው በአዲስ መልክ መጀመሩን አመላካች ነበር፡፡[148]

## በዘመነ ኢህአዴግ

ከ1991 ወዲህ የተደረገውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ በአገራችን ውስጥ የተገኘውን የእምነት ነፃነት ሽፋን በማድረግ ብዙ ጥፋቶች ተፈፅመዋል፡፡ በተለይ የወሃቢዝም ፍልስፍና ተከታዮች ነፃነቱ የሰጣቸውን ክፍተት በመጠቀም የማንይደፍረኛል ፅንፈኛ ትምህርቶችን በማስተማር ግርምቢጠኛ ባህርያቸው

---

[147] Ibid., 189-190

[148] ኤፍሬም እሸቴ፡፡ *አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ፣* 2000፣ ገፅ 142-143

ከልክ አልፎ በሚያሰራጯቸው ጽሑፎችና የድምፅ እንዲሁም የምስል መልዕክቶች ሌሎች ሃይማኖቶችን በነገር በመጎሸመጥ አገሪቱን ሲያምሱ ቆይተዋል፡፡ የተሰጣቸውን የመንግሥት ሥልጣን ለእምነታቸው ማስፋፍያ በመጠቀም ብዙ በደሎችንም የፈፀሙ ባለሥልጣናት ነበሩ፡፡ በአንድ ወቅት ከውጪ አገራት በገፍ በመግባት አገሪቱን ያጥለቀለቁት የጂሃድ ፊልሞችና አክራሪነትን የሚሰብኩ የህትመት ሥራዎች ያስከተሉት ውጤት በገሃድ ታይቷል፡፡ በተለይ ከሳዑዲ አረብያ በሚመጣው የነዳጅ ዶላር የተገነቡት መስጊዶችና እስላማዊ ማዕከላት አገሪቱን እንደሙጃ ውጠዋታል፡፡ በበጎ አድራጎት ሥም ወደ አገር ውስጥ የገቡ በርካታ እስላማዊ ድርጅቶችም ውስጥ ለውስጥ ጂሃዳውያንን እያሰለጠኑና የገንዘብ ድጋፍ እያደረጉ  አገሪቱን ወዳልተጠበቀ አደጋ መርተዋታል፡፡ የሂደቱ ገደብ አልባነት እንደ አነሳሱ ቢቀጥል ኖሮ  ሊከተል የሚችለውን አደጋ ማሰብ በእጅጉ ይዘገንናል፡፡ አደጋውን ከማስቀረት አንፃር መንግሥት ይበል የሚያሰኙ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ በተለይም የወሃቢዝም ዋነኛ የርቢ ማዕከል የሆነው አል-አወልያ እስላማዊ ትምህርት ቤት ከወሃቢዮች እጅ ወጥቶ ለተገቢው አካል መሰጠቱ ይበል የሚያሰኝ ነበር፡፡ ከአንደኛ ደረጃ ተነስቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በምስራቅ አፍሪቃም ጭምር ግምባር ቀደም እስላማዊ ትምህርት ቤት ለመሆን የበቃው ይህ የፅንፈኞች ማዕከል በአገሪቱ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ የተወሰደው እርምጃ ከረፈደ በኋላ ቢሆንም ነገር ግን ከመሸ በኋላ አለመሆኑ ተስፋ ሰጪ ነው፡፡

# የማጠቃለያ ሐሳቦች

በመጽሐፉ ማጠቃለያ መላው የአገራችን ሕዝብ፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የመንግሥት አካላትም ሆኑ ሰላም ፈላጊው ሙስሊሙ ወገናችን የሽብር ምንጭ ስለሆነው ስለ አክራሪ እስልምና ማወቅ ያሉባቸውን ቁልፍ ነጥቦች መጥቀስና የመፍትሔ ሐሳቦችን መጠቆም አስፈላጊ ነው፡፡

## መታወቅ ያለባቸው ወሳኝ እውነታዎች

ꕥ

### ☙ አክራሪ ሙስሊሞች ለሽብር ተግባሮቻቸው ማፅደቂያ ሊጠቅሷቸው የሚችሉ ብዙ እስላማዊ አስተምህሮዎች አሉ

እስልምና የሰላም ሃይማኖት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ በአሁኑ ወቅት በዓለም ዙርያ አነጋጋሪ ከሆኑት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ክርስትናን ጨምሮ ብዙ የዓለም ሃይማኖቶች ይብዛም ይነስም በአንድ ወቅት የነውጠኝነት (violence) ታሪክ እንደነበራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ሃይማኖት መለካት ያለበት በተከታዮቹ ሁኔታ ሳይሆን የእምነቶቹ መመርያ የሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት በሚያስተምሩት ትምህርት መሆኑ እሙንና ቅቡል ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍቱ ሰላምና ፍቅርን የሚሰብኩ ሆነው ሳሉ የእምነቱ ተከታዮች መመርያውን ባለመታዘዝ ነውጠኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነውጠኝነትን የሚሰብኩ መጻሕፍትን እንደ ሃይማኖት መመርያ የተቀበሉ ነገር ግን ባለማወቅም ይሁን መመርያዎቹን በተለየ መንገድ በመተርጎም ወይም ሆነ ብሎ ባለመታዘዝ በህሊናቸው የሚመሩና ከሌሎች ጋር በሰላም የሚኖሩ ወገኖች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመርያው ክፍል በሆነው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ግልፅ በሆነ አውድ፣ ለአንድ የተወሰነ ዘመን፣ ለአንድ ሕዝብና ውሱን ለሆነ ዓላማ

የተሰጡ ጦርነትንና የኃይል እርምጃን የሚያፀድቁ መመርያዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ማንም ሰው በዚህ ዘመን እንዲተገብራቸው በሚያነሳሳ ወይም በሚፈቅድ ሁኔታ አልተጻፉም፡፡ የመለኮታዊ መገለጥ መደምደምያ በሆነው አዲስ ኪዳን ውስጥ የተሰጡት መመርያዎች ደግሞ በቀልን፣ ጥላቻን፣ ጦርነትንና ማንኛውንም የኃይል እርምጃ አጥብቀው የሚከለክሉ በመሆናቸው ነውጠኝነት ክርስቲያናዊ እንዳልሆነ ያረጋግጣሉ (ማቴዎስ 5፡44፣ ማርቆስ 11፡25፣ ሉቃስ 6፡27-36፣ ዕብራውያን 12፡14፣ ኤፌሶን 4፡32፣ 1ተሰሎንቄ 5፡15፣ የሐዋርያት ሥራ 7፡60፣ ያዕቆብ 3፡18፣ ሮሜ 12፡18፣ 14፡19፣ 1ጴጥሮስ 3፡9-11፣ 1ቆሮንቶስ 14፡33)፡፡ የእምነታችን ጀማሪና ፈፃሚ የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር ሰላምን ሰብኳል፡፡ የክርስቲያኖች እምነት ጀማሪ፣ መሠረት፣ ምሳሌና ሞዴል የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ እንዲሁም የእርሱን ተልዕኮ ይዘው የቀጠሉት ሐዋርያቱ እጅግ ሰላማውያን ነበሩ፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሮማ ኢምፓየር ፖለቲካ መጠቀሚያ እስከተደረገችበት እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የነበሩት ክርስቲያኖች መገደልን እንጂ መግደልን፣ መሰደድን እንጂ ማሳደድን አያውቁም ነበር፡፡ ኮሎሲዩም በተሰኘው የሮም የመጫወቻ እስታዲዮም ውስጥ ጫወታዎችን የሚያሳዩ ጎበዞች ክርስትናን መቀበላቸው የሚታወቅበት አንዱ መንገድ ከአውሬዎች ጋር የመታገል ትዕይንት ቢያሳዩም ከሰዎች ጋር በሚደረግ ደም አፋሳሽ ትግል ላይ አለመሳተፋቸው ነበር፡፡ ከሰዎች ጋር በሚደረግ ትግል ውስጥ ሌላውን ወገን ከመግደል ይልቅ መሣርያዎቻቸውን በመጣል መገደልን ይመርጡ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ትምህርትና ምሳሌነት የነበራት መታመን የተሸረሸረው “የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር” የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ችላ በማለት የቄሣሮች መጠቀምያ ከሆነች ወዲህ ነበር፡፡

በአንፃሩ ከክርስቶስ ልደት ስድስት መቶ ዓመታት በኋላ የተሰበከውን የእስልምናን ታሪክ፣ ጀማሪው የሆኑትን የመሐመድንና የተተኪዎቻቸውን ሕይወት ስንክሳር ስናጠና የክርስቶስና የመጀመርያዎቹ ክርስቲያኖች እምነትና ኑሮ ተቃራኒ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሁለተኛው ኸሊፋ ኡሥማን ተገደሉ፡፡ ሦስተኛው ኸሊፋ ዑመር ተገደሉ፡፡ የነቢዩ መሐመድ የአጎት ልጅና የልጃቸው ባል የነበሩት አራተኛው ኸሊፋ አሊም ተገደሉ፡፡ የአሊ ልጅ ሁሴን የአባታቸውን ሥልጣን ለማስመለስ ሲዋጉ ተገደሉ፡፡ የመሐመድ ሚስት አይሻ ደጋፊዎቻቸውን በማደራጀት ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር ሲዋጉ ነበር፡፡

ነቢዩ መሐመድ ለተተኪዎቻቸው ምሳሌ ሊሆን የሚችል ሰላማዊ ሕይወት አልነበራቸውም፡፡ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በጦርነት፣ በሽምቅ ውጊያ፣ በዝርፍያና ተቃዋሚዎቻቸውን ከአገር በማባረር ነበር የኖሩት፡፡ ባጠቃላይ ትምህርቶቻቸውና ያሳለፏቸው ታሪኮች በምንም መስፈርት የሰላም ሰው እንደሆኑ እንድንናገር አያስደፍሩንም፡፡ ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እናያለን፡፡

የእስልምና ጀማሪ የሆኑት መሐመድ እንዲህ ማለታቸው ተነግሯዋል፡- "**በሽብር** ድል ነሺ ተደርጌያለሁ፡፡"[149] በሌላ ዘገባም "**በሽብር** እታገዛለሁ" ማለታቸው ተዘግቧል፡፡ ይህም ከሌሎች የቀደሙት ነቢያት ሁሉ ልዩ እንደሚያደርጋቸው በኩራት ተናግረዋል፡፡ [150]

ቁርአንም የእስልምና አምላክ የሆነው አላህ ሽብርን እንደሚነዛ ይናገራል፡-

> "በእነዚያ በካዱት ሰዎች ልቦች ውስጥ አላህ በእርሱ አስረጅ ያላወረደበትን ነገር በአላህ በማጋራታቸው ምክንያት **ፍርሃትን**

---

[149] Sahih Al-Bukhari; Volume 4, book 52, Number 220

[150] Sahih Muslim; Book 004, Number 1062, 1063, 1066, 1067

እንጥላለን፡፡ መኖሪያቸውም እሳት ናት፡፡ የበዳዮችም መኖሪያ ምን ትከፋ!” የዒምራን ቤተሰብ ምዕራፍ 3፡151 (በተጨማሪም ሱራ 8፡12፣ 8፡59-60፣ 33፡25-27፣ 59፡2፣ 59፡4፣ 59፡13)፡፡

በነዚህ ቦታዎች ላይ “ፍርሃት” ተብሎ የተተረጎመው በአብዱላህ ዩሱፍ አሊ የእንግሊዘኛ ትርጉም “Terror” ተብሎ ተቀምጧል፡፡

በተከታዩ የቁርአን ጥቅስ መሠረት ደግሞ አላህ ሙስሊሞች ሙስሊም ያልሆኑትን ሰዎች ለማሸበር እንዲዘጋጁ ይነግራቸዋል፡-

“...ለእነሱም ከማንኛውም ኃይልና ከታጀቡ ፈረሶችም የቻላችሁትን ሁሉ በእርሱ የአላህን ጠላትና ጠላታችሁን ሌሎችንም ከእነርሱ በቀር ያሉትን የማታውቋቸውን አላህ የሚያውቃቸውን (መናፍቃን) **የምታሸብሩበት** ስትኾኑ አዘጋጁላቸው፡፡” (የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ 8፡60)

በኒ ቁረይዛ የተሰኘ የአይሁድ ጐሣ በመሐመድ ዘመን በአረብያ ባህረ ሰላጤ ከሚገኙ ጠንካራ የአይሁድ ማህበረሰቦች መካከል አንዱ ነበር፡፡ መሐመድም ገብርኤል ተገልጦላቸው ይህንን ማህበረሰብ **እንዲያሸብሩ** እንደነገራቸው ለተከታዮቻቸው ተናገሩ፡፡ እናም ወንዶቻቸው እንዲገደሉ ያደረጉ ሲሆን ሴቶችና ህፃናትን ለሙስሊሞች ከፋፍለዋል፡፡ በሕይወት የተረፉትን ደግሞ ባርያዎች አድርገዋቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከመገደላቸው በፊት መሐመድ በመዲና የገበያ ስፍራ መካከል ጉድጓድ አስቆፍረው ነበር፡፡ ከዚያም በጥቂቱ 700-800 የሚገመቱ አይሁዳውያንን ወደዚያ ሥፍራ በመውሰድ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ሁሉንም በአንድ ላይ አሳረዷቸው፡፡[151]

---

[151] Sunan Abu Dawud; 14:2665; 38:4390; Sahih Al Bukhari 4:52:280

የሱኒ ዕውቅ ሐታች የሆኑት ኢብን ከሢር የአይሁድን በጅማ መታረድ እንዲህ በማለት ገልፀዋል፡- “ከዚያም የአላህ መልእክተኛ ጉድጓዶች እንዲቆፈሩ አዘዙ፤ ተቆፈሩም፡፡ እነርሱም ትከሻቸው ላይ ታስረው እንዲመጡ ከተደረገ በኋላ ታረዱ፡፡ ቁጥራቸውም ከሰባት መቶ እስከ ስምንት መቶ ይገመታል፡፡ ህፃናትና ሴቶችም ተማረኩ፤ ንብረታቸውም ተወረሰ፡፡”[152]

አሳዛኙ ነገር የበኒ ቁረይዛ አይሁድ መሐመድ ወረዱልኝ በሚሏቸው “መገለጦች” አይሁድን በማንቋሸሻቸው ምክንያት ከማኩረፋቸው የዘለለ ሙስሊሞችን አጥቅተው የማያውቁ መሆናቸው ነው፡፡ እንዲያውም “የምሽጎች ዘመቻ” (The Battle of Trenches) በተሰኘ የጦርነት ውሎ ወቅት ለሙስሊሞች መሸሸግያን በማዘጋጀት ረድተው ነበር፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ ከመካ ነዋሪዎች ጋር ቢያብሩ ኖሮ ሙስሊሞችን ሙሉ በሙሉ የማጥፋት አቅም ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ያንን አላደረጉም፡፡ መሐመድና ተከታዮቻቸው ግን የእነርሱን ውለታ ወንዶቻቸውን በማረድ፣ ሴቶችና ህፃናቶቻቸውን ባርያ በማድረግና ንብረታቸውን በመዝረፍ ነበር የመለሱት፡፡

መሐመድ በጦርነት ወቅት ህፃናትና ሴቶች እንዳይገደሉ እንዳዘዙ የሚናገሩ ሐዲሶች ብዙ ጊዜ ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ግን የመሐመድ ትምህርት እርስ በእርሱ የሚጣረስና ወጥነት የሌለው መሆኑን ከማረጋገጥ የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡ ህፃናትና ሴቶች እንዳይገደሉ ይናገራሉ የተባለላቸውን የእስልምና ትውፊቶች ስናጠና ሴቶችና ህፃናት የሚገደሉበት አውድ መኖሩን እንደሚናገሩ ማየት እንችላለን፡፡ አንድ ሐዲስ እንዲህ ይላል፡-

---

[152] Tafsir Ibn Kathir – The Campaign against Banu Qurayzah www.tafsir.com

“የአላህ መልእክተኛ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) ህፃናትን አይገድሉም ነበር ስለዚህ አል ኸዲር ስለገደለው ህፃን ያወቀውን ነገር የምታውቁ ካልሆናችሁ በስተቀር ወይንም አማኝ በመሆን በሚያድግና አማኝ ባለመሆን በሚያድግ ህፃን መካከል መለየት ካልቻላችሁ አትግደሉ፡፡ ስለዚህ አማኝ የማይሆነውን ትገድላላችሁ፤ አማኝ የሚሆነውን ደግሞ ትተዋላች፡፡”[153]

እንግዲህ በዚህ ሐዲስ መሠረት ሙስሊሞች አማኝ ሳይሆን ሊያድግ እንደሚችል የተረዱትን ህፃን መግደል ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ሙስሊም ያልሆኑ ህፃናትን ከወላጆቻቸው ነጥሎ በሙስሊሞች መካከል እንዲያድጉ የማድረግ እድል ከሌለ “ካፊሮች” ከሆኑት ወላጆቻቸው ጋር አንድ ላይ መግደል የተፈቀደ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሙስሊም ሽብርተኞች በአዋቂዎች ስብስብ መካከል ህፃናት መኖራቸውን እያወቁ አደጋ የሚያደርሱት፡፡

በአንድ ወቅት ደግሞ መሐመድ የከሃዲያንን ወይንም ደግሞ መድብለ አማልክትን የሚያመልኩ ሰዎችን ሴቶች እና ሕፃናት መግደል ይቻል እንደሆን ተጠይቀው ነበር፡፡ እርሳቸውም ሲመልሱ “እኔ ልክ እንደ ወላጆቻቸው ነው የምቆጥራቸው” በማለት ነበር፡፡[154] በሌላ አባባል ወላጆች ከሃዲዎች ከሆኑ ልጆቻቸውን መግደል የተፈቀደ ነው ማለት ነው፡፡

መሐመድ ሴቶችንም በእንቶ ፈንቶ ምክንያቶች ያስገድሉ እንደነበር በእስላማዊ ምንጮች ውስጥ ተጠቅሶ እናያለን፡-

153 Sahih Muslim 4457
154 Sahih Muslim; 4322; Sahih Al Bukhari 52:256

"ሁለት ልጃገረዶች፣ ፈርተና እና ጓደኛዋ ስለ መልእክተኛው ምፀታዊ የቅኔ መዝሙር ሲዘምሩ ስለነበር እንዲገደሉ አዘዙ፡፡"[155]

መሐመድን የሚተች ቅኔ በመናገሯ ምክንያት አስማ ቢንት ማርዋን የተባለች አንዲት ብልህ ሴት እንዲሁ ተገድላለች፡፡ አስማ የተገደለችው ልጇን እያጠባች ሳለች እንደሆነ እስላማዊ ምንጮች ዘግበዋል፡፡[156] ነቢዩ ለአረጋዊያንም የሚያዝን ልብ አልነበራቸውም፡፡ አቡ አፋክ በመባል የሚታወቅ እድሜው 120 እንደነበር የተነገረ በጣም የሸመገለ አይሁዳዊ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው የመሐመድን ነቢይነት በጥርጣሬ ከሚመለከቱ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ በሰይፍ ተወግቶ እንዲገደል ተደረገ፡፡[157]

ተከታዮቹ የቁርአን ጥቅሶች ሙስሊሞች ጎረቤቶቻቸው የሆኑትን የሌሎች እምነቶች ተከታዮች በመዋጋት እንዲያስጨንቁና ለእስላማዊ ሕግጋት እንዲያስገዙ ያበረታታሉ፡-

> "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እነዚያን በአቅራቢያችሁ ያሉትን ከሓዲዎች ተዋጉ፡፡ ከእናንተም ብርታትን ያግኙ፡፡ አላህም ከሚጠነቀቁት ጋር መኾኑን ዕወቁ፡፡" (የንስሐ ምዕራፍ 9፡123)
>
> "አንተ ነቢዩ ሆይ! ከሓዲዎችንና መናፍቃንን ታገል፡፡ በእነሱም ላይ ጨክን፡፡ መኖሪያቸውም ገሀነም ናት፡፡ መመለሻይቱም ከፋች፡፡" (የንስሐ ምዕራፍ 9፡73)

---

155 Guillaume. *The Life of Muhammad;* p. 819

156 Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp. 675-676; Ibn Sa'd. *Kitab al-tabaqat al-kabir* pp. 30-31; Ibn Sa'd al-Baghdadi. *The Book of the Major Classes* Vol. 2, pp. 32

157 *Kitab al-Maghazi;* translated by Faizer R., Ismail A., & Tayob, A. K. (2011); Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp.86-87

“የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፡፡ ያዙዋቸውም፣ ከበቡዋቸውም፣ ለእነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ፡፡ ቢጸጸቱም፣ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡” (የንስሐ ምዕራፍ 9፡5)

“ሁከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሏቸው፡፡ ቢከለከሉም አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡” (የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ 8፡39)

በእስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ የሚከተለው ዘገባ ሰፍሮ እናገኛለን፡

“ኢብን ዑመር እንዳስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፤ ሰዎች ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው እንደሌለና መሐመድም ደግሞ መልእክተኛው መሆኑን እስኪመሰክሩ ድረስ እንዲሁም ሶላትን ደንቡን ጠብቀው እስኪሰግዱ ድረስና ዘካትን እስኪሰጡ ድረስ እንድዋጋቸው (በአላህ) ታዝዣለሁ፡፡ ይህንን የሚያደርጉ ከሆነ በእስልምና ሕግ ከተደነገገው በስተቀር ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን ከእኔ ይታደጋሉ፤ ድርሻቸውም በአላህ ይታሰብላቸዋል፡፡”[158]

“ነቢዩ ‹ማንኛውንም እስልምናን ለቆ የሚወጣ ሰው **ግደሉት**› ብለዋል፡፡ ”[159]

ቁርአን ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ከፍጥረት ሁሉ ከፉ እንደሆኑ ይናገራል፡-

[158] Sahih Al-Bukhari; Vol. 1 Book 2, Number 24

[159] Sahih al-Bukhari, 52:260; 83:37; 84:57; 89:271; 84:58; Abu Dawud, 4346

“እነዚያ ከመጽሐፉ ሰዎች የካዱት፣ አጋሪዎቹም በገሀነም እሳት ውስጥ ናቸው፤ በውስጧ ዘውታሪዎች ሲኾኑ እነዚያ እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ ከፉ ናቸው፡፡” (የግልፅ አስረጅ ምዕራፍ 98፡6)

ትክክለኛ ሙስሊሞች ያልሰለሙ ቤተሰቦቻቸውን እንኳ ወዳጅ የማያደርጉ መሆናቸውን ቁርአን እንዲህ በማለት ይናገራል፡-

“በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣ ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፡፡ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፡፡ ከእርሱም በኾነ መንፈስ ደግፏቸዋል፡፡” (የመከራከር ምዕራፍ 58፡22)

በዚህ መሠረት ሙስሊም ያልሆኑትን ቤተሰቦቹን መጥላት ያልቻለ ሰው የእስልምናን መንፈስ አልተቀበለም፡፡

ክርስቲያኖችንና አይሁድን ስለ መጥላት እስላማዊ ትውፊት እንዲህ ይላል፡-

“ነቢዩ (የአላህ ሰላምና በረከት በእሳቸው ላይ ይሁንና) እንዲህ ብለዋል ‹አይሁድን ወይንም ክርስቲያኖችን ቀድማችሁ ሰላም አትበሉ፡፡ በመንገድ ላይ ቢመጡባችሁ ወደ ጠባቡ የመንገድ ጠርዝ ግፏቸው፡፡›”[160]

እንዲሁም በቁርአን ውስጥ የእርግማንን ቃላት በክርስቲያኖችና በአይሁድ ላይ ሲናገሩ እንመለከታለን፡-

“አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አለች፡፡ ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ፡፡ ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፡፡

---

160 Sahih Muslim, 2167; Sahih al-Bukhari Book 25, Number 5389 በተጨማሪም ኢማም አን-ነወዊ፡፡ *ሪያዱ ሷሊሒን፤* ከሐዲስ ቁጥር 811-1896፣ ቅፅ 2፤ ትርጉም በሐሰን ታጁ፣ ገፅ 42 ይመልከቱ

የእነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፡፡ አላህ ያጥፋቸው፡፡ (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ!" (የንስሐ ምዕራፍ 9፡30)

መሐመድ ሕይወታቸው ከማለፉ በፊት የተናገሩት የመጨረሻው ንግግራቸው አይሁድንና ክርስቲያኖችን መርገም እንደነበር እስላማዊ ትውፊቶች ይናገራሉ፡:

"አይሻና አብዱላህ እንደዘገቡት ፡ የአላህ ምልእክተኛ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁንና) የመጨረሻ እስትንፋሳቸውን ሊተነፍሱ በነበሩበት ጊዜ ፊታቸውን በአንሶላው ሸፈኑ፤ ትንሽ ከተረጋጉ በኋላ ፊታቸውን ገለጡና በዚያ ሁኔታ እያሉ እንዲህ አሉ ‹የሐዋርያቶቻቸውን መቃብሮች እንደ ፀሎት ቦታ በመጠቀማቸው በአይሁድና በክርስቲያኖች ላይ እርግማን ይሁን፡፡› (ተከታዮቻቸውንም) (አይሁድና ክርስቲያኖች) የሚያደርጉትን ነገር እንዳያደርጉ አስጠንቅቀዋል፡፡"[161]

ተከታዩ ጥቅስ መሐመድና ትምህርታቸውን የተቀበሉ ሰዎች ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች ላይ ጨካኞች እንደሚሆኑ ይናገራል፡-

"የአላህ መልክተኛ ሙሐመድ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉት (ወዳጆቹ) በከሓዲዎቹ ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው አዛኞች ናቸው፡፡" (አገር የመከፈት ምዕራፍ 48፡29)

ይህ ጥቅስ በአረብኛ ሲነበብ መሐመድና ተከታዮቻቸው "በካፊሮች" ላይ ምህረት የለሽ ጨካኞች (Ruthless) እና እርስ በእርሳቸው ደግሞ የሚተዛዘኑ መሆናቸውን የሚናገር ነው፡፡ በሚከተለው ጥቅስ ውስጥ ደግሞ "በካፊሮች" ላይ መጨከን የአላህ ትእዛዝ መሆኑን እናያለን፡-

161 Sahih Muslim; 1082; Sahih Al-Bukhari; 2:23:472

“አንተ ነቢዩ ሆይ! ከሓዲዎችንና መናፍቃንን ታገል፡፡ በእነሱም ላይ ጨክን፡፡ መኖሪያቸውም ገሀነም ናት፡፡ መመለሻይቱም ከፋች፡፡” (የንስሐ ምዕራፍ 9፡73)

በአንድ ወቅት የተወሰኑ ሰዎች ወደ መሐመድ በመምጣት እስልምናን ተቀበሉ፡፡ መሐመድም በደህና አስተናገዷቸው፡፡ የመዲና የአየር ሁኔታ ስላልተስማማቸው ወደ ግመል መንጋ በመሄድ ወተታቸውንና ሽንታቸውን ለመድኃኒትነት እንዲጠጡ አዘዟቸው፡፡ ሰዎቹ ከተሻላቸው በኋላ የመሐመድን እረኛ በመግደል ግመሎቹን ወስደው ሄዱ፡፡ መሐመድም ጠባቂዎቹን በመላክ ተከታትለው ይዘዋቸው እንዲመጡ አደረጉ፡፡ ከዝያም “ዓይን ስለ ዓይን ጥርስ ስለ ጥርስ” በሚለው ትእዛዝ መሠረት ሳይሆን ለመስማት በሚዘገንን ሁኔታ ቀጧቸው፡፡ ቡኻሪ የተሰኙት የትውፊት ዘጋቢ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡-

“(ነቢዩ) እጆቻቸውና እግሮቻቸው እንዲቆረጡ አዘዙ፤ ተቆረጡም፡፡ ዓይኖቻቸውም በጋለ ብረት ተጠብሶ እንዲጠፋ ተደረገ፡፡ ከዝያም እስኪሞቱ ድረስ በአል ሀራ (ፀሐያማ የሆነ የመዲና ደረቅ ቦታ) ላይ ተጣሉ፡፡ ውኃ በጠየቁ ጊዜ ምንም ውኃ አልተሰጣቸውም ነበር፡፡”[162]

በሚከተለው ሐዲስ መሠረት ነቢዩ መሐመድ ለገንዘብ ብለው ሰዎችን ያሰቃዩ እንደነበር እናያለን፡፡ በሐዲሱ ውስጥ የተጠቀሰው ሰው በኸይበር የሚገኙ አይሁድ መሪ የነበረ ወጣትና አዲስ ሙሽራ ነበር፡፡ መሐመድ ካስገደሉት በኋላ መልከመልካም የ17 ዓመት ወጣት የነበረችውን ሰፊያ የተሰኘች ሚስቱን ለራሳቸው ወስደዋል፡፡ ሐዲሱ እንዲህ ይነበባል፡-

[162] Sahih Al-Bukhari; 7:71:623; 5:59:505; 1:4:234; 4:52:261; Sahih Muslim; 16:4131; 16:4130; 16:4132; 16:4134; Abu Dawud; 38:4356; 36:4357

“ነቢዩ ኪናና የተባለውን ሰው በተመለከ ለዙባይር እንዲህ የሚል ትእዛዝ ሰጡ ‹በውስጡ የደበቀውን ሁሉ እስኪያወጣ ድረስ አሰቃየው፡፡› ስለዚህ ዙባይር ኪናና ለሞት እስኪቃረብ ድረስ ደረቱ ላይ እሳት አስቀመጠበት፡፡ ከዚያም ነቢዩ ለመስለማህ አሳልፈው ሰጡት፡፡ እርሱም አረደው፡፡”[163]

መሐመድ ሰዎች በእሳት እንዳይቃጠሉ እንደከለከሉ የሚናገሩ ሐዲሶች አሉ ነገር ግን ደግሞ ሰዎች በእሳት እንዲቃጠሉ ያዘዙባቸው ቦታዎችም አሉ፡፡[164]

ሌላው እጅግ አሰቃቂና ለመስማት የሚዘገንን የነቢዩ መሐመድና የተከታዮቻቸው የጭካኔ ታሪክ አል-ጦበሪ እና ኢብን ኢስሐቅ በጻፏቸው የመሐመድ ታሪኮች ውስጥ ይገኛል፡-

“የ80 ዓመት ዕድሜ ባለጠጋ የሆነች ትክክለኛ ስሟ ፋጢማ ቢንት ሩቢያዐ የተሰኘ ኡም ቂርፋ የምትባል ሴት ነበረች፡፡ መሐመድን የሚተች ግጥም በማዘጋጀትም ትደግም ነበር፡፡ 13 ወንዶች ልጆች የነበሯት ሲሆን ሁሉም ጎልማሶችና የአይሁድ ጎሣ መሪዎች ነበሩ፡፡ በዘይድ የሚመራ አጥቂ ቡድን በረመዳን ወቅት በኡም ላይ ዘመተ፡፡ በዚያን ጊዜ ኡም አሳቃቂ አሟሟት ሞተች፡፡ ዘይድ እግሮቿን በገመድ አድርጎ በሁለት ግመሎች መካከል አሰራት፡፡ በተቃራኒ አቅጣጫዎችም እንዲሄዱ አደረገ፤ እርሷም ለሁለት ተሰነጠቀች፡፡ በጣም ያረጀች ሴት ነበረች፡፡ ከዝያም የኡምን ልጅና አብዱላን ወደ ነቢዩ አመጧቸው፡፡ የኡም ልጅ፣ የማረካት

---

163 Al-Tabari; Vol. 8, p. 122

164 Sahih Al-Bukhari; 11:626; Guillaume. *The Life of Muhammad;* p. 316

የሰላማህ ንብረት ሆና ነበር፡፡ መሐመድም ሰላማህን ስለ እርሷ ጠየቁት፡፡ ሰላማህም እርሷን ሰጣቸው፡፡"[165]

ዋና ዋና የሚባሉት እስላማዊ ምንጮች ስለ ነቢዩ መሐመድና ስለ ተከታዮቻቸው ከላይ የተባሉትን እውነታዎች የሚገልጡ ከሆነ በመሐመድ የተሰበከውና የተኖረው ትክክለኛው እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑን ለመናገር የሚያስደፍር መሠረት የለንም፡፡

## ❧ ሙስሊሞች ሁሉ አንድ አይደሉም

ሙስሊሞች ለቁርአናዊ ትምህርቶች ያላቸውን ታማኝነትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚወስኑ የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ማወቅና ጎረቤቶቻችን ምን ዓይነት ሙስሊሞች እንደሆኑ መለየት ጥንቃቄ ከማድረግ በተጨማሪ በጭፍን ፈራጆች እንዳንሆን ይረዳናል፡፡

ሙስሊሞች የሚከተሉትን አመለካከት የሚወስነው የመጀመርያው ነገር ያሉበት የአስተሳሰብ ጎራ ወይም ቤተ እምነት ነው፡፡ እስልምና እንደማንኛውም ሃይማኖት በውስጡ ክፍፍሎች ያሉበት ሃይማኖት ነው፡፡ ሱኒ እና ሺአ የተሰኙ ሁለት አበይት ክፍሎች ሲኖሩት በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ብዙ ጎራዎች ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሱኒዎች ሲሆኑ አብዛኞቹ የሱፊ አስተምህሮ አራማጆች ናቸው፡፡ ሱፊ እስልምና በአንፃራዊነት ሰላማዊ ሊባል የሚችል ነው፡፡ በዚህ ጎራ ውስጥ የሚገኙት ሙስሊሞች ከምንም በላይ ከአምላካቸው ጋር የግል ሕብረት በማድረግ ላይ ያተኩራሉ፡፡ በሰላምና በፍቅር ስለሚያምኑ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ለመኖር ብዙም አይቸገሩም፡፡ ሱፊዎች ከሚታወቁባቸው ነገሮች መካከል አንዱ መንፈሳዊ በረከቶችን ለማግኘት "ቅዱሳን" እንደሆኑ የሚያምኗቸውን ሰዎች

165 Al-Tabari; Vol. 8, p.96; Guillaume. *The Life of Muhammad;* pp. 664-665

መቃብሮች መንብኘት ነው፡፡ ይህ ተግባራቸው በተለይም በወሃቢዝም (ሰለፊ) ፍልስፍና ተከታዮች ዘንድ እንዲነቀፉና እንደ እውነተኛ ሙስሊሞች እንዳይቆጠሩ እንዲሁም የጥቃት ዒላማ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አብዛኞቹ ሱፊዎች ሲሆኑ በአገሪቱ ውስጥ ትልቁ የሱፊ ማዕከል በመባል የሚታወቀው በባሌ ዞን የሚገኘው የድሬ ሼሁሴን መስጊድ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያን ሙስሊሞች “እንደገና የማስለም” መርሃ ግብር ተይዞ የሱፊ እስልምናን በማጥፋት በወሃቢዝም ለመተካት ከፍተኛ ሩጫ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የታዩት የአመፅና የሽብር ተግባራት የዚህ መርሃ ግብር ውጤቶች ናቸው፡፡ ይህንን በትጋት እየፈፀሙ የሚገኙት ደግሞ በዋናነት ሳዑዲ አረብያ፣ ቱርክና ካታር ናቸው፡፡

ሙስሊሞችን ስለ ሃይማኖታቸው ባላቸው የዕውቀት ደረጃ ላይ ተመስርተን ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ ላይ የደረሱ፣ መሠረታዊ ዕውቀት ያላቸውና አነስተኛ ዕውቀት ያላቸው ብለን ልንመድባቸው እንችላለን፡፡ ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ ላይ የደረሱትን በማሕበረሰባቸው ውስጥ ባላቸው ቦታና ደረጃ መለየት የምንችል ሲሆን ብዙኀኑ ሕዝበ ሙስሊም በጣም ውሱን እውቀት ያለው ነገር ግን ለሃይማኖቱ ታማኝ መሆን የሚፈልግ ነው፡፡ ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ ላይ የደረሱ የተባሉት በተለይም የወሃቢዝም ፍልስፍና አቀንቃኞች ከሆኑ ብዙ ጊዜ በሽብር ተግባራት ውስጥ በቀጥታ ሲሳተፉ ባይታይም የሐሳቡ አመንጪዎች፣ የሽብርተኞች መልማዮችና የአተገባበር ስልት ነዳፊዎች እነርሱ ናቸው፡፡ ለሽብር ተግባሮቻቸው ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙት ደግሞ ስለ ሃይማኖቱ አነስተኛ ዕውቀት ያለውን ሙስሊም ነው፡፡

## ፩ ጂሃድ ደረጃዎች አሉት

ጂሃድ ሦስት ደረጃዎች አሉት፡፡ የመጀመርያው ደረጃ አክራሪ ሙስሊሞች ደካሞችና ሙስሊም ያልሆኑ ሕዝቦች በሚበዙበት አገር ውስጥ ሲኖሩ የሚተገበር ነው፡፡ የአገሪቱን ሕግ በማክበር ቢኖሩም ነገር ግን ቁጥራቸውን በመጨመርና ኢኮኖሚያዊ የበላይነትን በመቀዳጀት ላይ በትጋት ይሠራሉ፡፡ በዚህ ደረጃ መሐመድ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ "በሃይማኖት ማስገደድ የለም" በማለት የተናገሩትን ቃል ተግባራዊ ያደርጋሉ (የላም ምዕራፍ 2፡256)፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የሚተገበረው የንግግር ነፃነት የሚፈቅድላቸውን የመጨረሻ ነፃነት በመጠቀም በጽሑፍና በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች በሌሎች እምነቶች ላይ ትችቶችን ይሰነዝራሉ፤ የአደባባይ ሙግቶችን ያደርጋሉ፤ በአካባቢው መገኘታቸው እንዲታወቅ እስላማዊ አልባሳትን ይጠቀማሉ፡፡

ሁለተኛው የጂሃድ ደረጃ የዝግጅት ደረጃ በመባል ይታወቃል፡፡ ተግባራዊ የሚሆነውም አክራሪ ሙስሊሞች ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም ነገር ግን ተፅዕኖ ማሳደር ወደሚችል ማሕበረሰብ ካደጉ በኋላ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በቀጣይ አገሪቱን ለመቆጣጠር በገንዘብ፣ በዕውቀት፣ በወታደራዊ ሥልጠናዎች፣ የጦር መሣርያዎችን በማከማቸትና በመሳሰሉት ራሳቸውን ያዘጋጃሉ (የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ 8፡59-60)፡፡ ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠሩላቸው ጥቃቶችን ይሰነዝራሉ፡፡ እስልምናን በአደባባይ የሚቃወሙትን ግለሰቦች በማጥቃት የትችት አንደበቶችን ይዘጋሉ፡፡ ራሳቸውን ከሌሎች ማሕበረሰቦች በመነጠል በእስላማዊ ሕጎች የሚተዳደሩትን አካባቢዎች ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ መካከል ደግሞ ሙስሊም አሸባሪዎች ጥቃቶችን በፈፀሙ ቁጥር ሽብር እስላማዊ አለመሆኑንና እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑን በመስበክ ሕብረተሰቡን ግራ የሚያጋቡ ግለሰቦች

ይኖራሉ፡፡ የተለያዩ የመገናኛ ብዙኀንን በገንዘብ በመደለል የእስልምናን በጎነት እንዲሰብኩ ያደርጋሉ፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው የፍልሚያ ደረጃ ነው፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ አክራሪ ሙስሊሞች የግድ ከሌላው ሕብረተሰብ በቁጥር መብለጥ አይጠበቅባቸውም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ላይ በተጠቀሱት የዝግጅት መንገዶች ከሌላው ማሕበረሰብ ከተሻሉና ስኬታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ካሉ ሙሉ እርምጃ ወደ መውሰድ ይገባሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ፅንፈኛ ሙስሊም ጂሃዳውያን የአምላካቸው እርዳታ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና ድልን እንደሚሰጣቸው ከልባቸው ስለሚያምኑ አናሳዎች ሆነው ሳሉ እንኳ አገሪቱን ለመቆጣጠር ሙሉ ወደሆነ ፍልሚያ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ፍልሚያው የማያዋጣቸው ከሆነ ደግሞ ወደ መጀመርያው ወይም ወደ ሁለተኛው ደረጃ በመመለስ ትግሉን ለጊዜው ሊገቱት ይችላሉ፡፡[166]

## ❧ አስመሳይነት የአክራሪ እስልምና ቁልፍ አስተምህሮ ነው

በእስልምና ውስጥ ብዙ የተፈቀዱ የውሸት ዓይነቶች አሉ፡፡ የሱኒ ሙስሊሞች “ሙደራት” የተሰኘ የአታላይነት አስተምህሮ አላቸው፡፡ በሺአ ሙስሊሞች ዘንድ ደግሞ “ታቂያ” በመባል ይታወቃል፡፡ ከኡላማ (ከእስልምና ሊቃውንት) ክበብ ውጪ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ስለዚህ አስተምህሮ ብዙም አያውቁም፡፡ “ሙደራት” ማለት ማደናነቅ፣ የግብዝነት አድናቆት፣ ማታለል፣ ቆዳን ማስወደድ፣ ማጭበርበር፣ እኩል መራመድ፣ መሸፈን፣ መደበቅ ወይንም መሰወር ማለት ነው፡፡ ይህ የማታለል ጠባይ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ሰዓት ሁሉ በማንም ላይ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን *የሱኒ* ምሑራን በቋሚነት *የሙደራት* ዒላማ ውስጥ መግባት አለባቸው ያሏቸውን አሥር ዓይነት ሰዎች ለይተው አስቀምጠዋል፡፡

[166] Mark A. Gabriel. *Islam and Terrorism;* 2002, pp. 85-89

*ካፊር* (ሙስሊም ያልሆነ ሰው)፣ "ከፉ" የሆነ መሪ፣ አዲስ የሰለሙ ሰዎች፣ ከእስልምና ልቡ ያፈነገጠውን ሰው ወደ እስልምና ለመመለስ፣ አማኞች ያልሆኑትን በመምሰል የሳተን ሙስሊም ለመመለስ፣ የተማረን ሰው ወይንም ሳይንቲስት ከዕውቀቱ ለመጠቀም፣ ጓደኛን ለማስደሰት፣ ከጠላት ለማምለጥ ወይም ለመጉዳት፣ የትዳር አጋርን ለማስደሰት፣ የታመመ ሰው (ለምሳሌ ያህል ደህና እንደሚሆን ወይንም ደህና መምሰሉን በመንገር)፡፡ የሱኒ ሊቃወንት ይህንን አመለካከት ለማፅደቅ የተለያዩ የቁርአን ጥቅሶችን ይጠቅሳሉ፡፡[167] የእስልምና ነቢይ የሆኑት መሐመድ "ጦርነት ማታለል ነው" በማለት መናገራቸው በትውፊቶች ውስጥ ተዘግቧል፡፡[168] ፅንፈኛ ሙስሊሞች ደግሞ ዘወትር ከኩፋሮች (ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች) ጋር በጦርነት ውስጥ እንደሆኑ ነው የሚያምኑት፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ ማንነታቸውን ለመሰወር፣ ሃይማኖታቸውን ለመጥቀምም ሆነ ሙስሊም ያልሆኑትን ለመጉዳት የትኛውንም የማታለል አካሄድ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

---

167 Sam Solomon & E. Al-Maqdisi. *Al-Hijra, Islamic Migration: Accepting Freedom or Imposing Islam?;* 2009, pp. 72-79
168 Sunan Abu Dawood *Book 14, Number 2631:* Narrated Ka'b ibn Malik

# የአክራሪ እስልምናን አደጋዎች ለመቀልበስ የሚጠቅሙ ሐሳቦች

1. **ከችግሩ ውጤቶች ይልቅ በችግሩ መንሥኤ ላይ ማተኮር፡፡** የሽብር ተግባራት የአክራሪ እስልምና ትምህርት ውጤቶች በመሆናቸው ዛፉ ከሥር ሳይቆረጥ የዛፉን ፍሬዎች እየቆረጡ መጣል መፍትሄ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ መፍትሄ ማምጣት ይቻል ዘንድ አክራሪነትን የሚሰብኩ እስላማዊ መጻሕፍትን መጋፈጥ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ዋና ዋና የሚባሉት እስላማዊ ምንጮች ቢሆኑ እንኳ የሚያስተላልፏቸውን ፀረ ሰላም መልዕክቶች እንዴት መቀልበስ እንደሚቻል መዘየድ አስፈላጊ ነው፡፡
2. **ከአረብኛ ወደ አገሬው ቋንቋዎች በሚተረጎሙ ሽብርተኝነትን በሚያስተምሩ መጻሕፍት ላይ ቁጥጥር ማድረግና ማስወገድ፡፡** በአገራችን ውስጥ በአንድ ወቅት ተተርጉመው ገበያውን ያጥለቀለቁ ሽብርን የሚሰብኩ መጻሕፍት የትየለሌ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል የዩሱፍ አል-ቀረዷዊ መጻሕፍት በብዛት ተተርጉመው በአገራችን ውስጥ ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ባለፉት ዘመናት በአገራችን ውስጥ ለተቀሰቀሱት እስላማዊ አመፆች ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከታቸው አያጠራጥርም፡፡ እንዲህ ዓይነት የዋሃቢዝምን አስተሳሰብ የሚሰብኩ መጻሕፍትን ሁሉ ተከታትሎ ማጥፋትና እንዳይታተሙ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
3. **የጂሃድ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ በአገራችን ቋንቋዎች የታተሙ የሥነ-ጽሑፍ ውጤቶችን፣ የድምፅና የምስል ሥራዎችን፣ የሬድዮና የቴሌቪዥን ጣብያዎችን በመቆጣጠር ላይ በትጋት መሥራት፡፡** በአገራችን ውስጥ የጂሃድ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ በመንግሥት በጀት ሳይቀር የታተሙ የሥነ

ጽሑፍ ውጤቶች መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል "ፉቱሑል ሐበሸ" በሚል ርዕስ ተጽፎ "ሐበሻን የማቅናት ዘመቻ" በሚል ርዕስ በሐረሪ ጉባኤ የተተረጎመው መጽሐፍ አሕመድ ግራኝ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ የፈፀመውን አሳቃቂ ግፍ የሚያወድስና አሁን ያለው ትውልድ ተመሳሳይ ነገር እንዲፈፅም የሚያበረታታ መጽሐፍ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ወንጀል እንዳይደገምና መሰል ተግባራትን የሚፈፅሙ መንግሥት የሰጣቸውን ሥልጣን ያለአግባብ የሚጠቀሙ ወገኖችን በሕግ ተጠያቂ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህንም መጻሕፍት ማገድ ጊዜ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡

4. **የሽብርተኝነት አስተሳሰብና አሠራር በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ገብቶ እንደሆን በየጊዜው መፈተሽ፤ ባለ ሥልጣናት በአክራሪነት አስተሳሰብ የተጠመቁ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡** አንዳንድ ባለ ሥልጣናት በፍትህ እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ የተሰጣቸውን ኀላፊነት በመዘንጋት ክርስቲያኖችን በመጨቆንና መስጊዶችን እንዲሁም እስላማዊ ተቋማትን በማስፋፋት ሥራ ላይ ተሰማርተው እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት አገር አጥፊዎችን ተከታትሎ ጥብቅ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ ለአሥርና ለሃያ ዓመታት ሲሠሩ ቆይተው አገሪቱን የመስጊድ ውቂያኖስ ካደረጉና የሚፈልጉትን ግብ ካሳኩ በኋላ ነቅቶ እርምጃ መውሰድ ፋይዳ የለውም፡፡

5. **ከእስልምና ወገን አዳዲስ ጥያቄዎች ሲነሱ ምላሽ ከመስጠት በፊት ኤክስፐርቶችን ማማከር፡፡** አንዳንድ ጥያቄዎች ቀላልና የኃላ ችግር የሌላቸው ይመስላሉ ነገር ግን በረጅም ጊዜ ሂደት ችግር የሚያስከትሉና ለሌሎች የሽብር ተግባራትም መንገድን የሚጠርጉ ናቸው፡፡ ስለዚህ ውሳኔዎችን ከማስተላለፍ በፊት ባለሙያዎችን ማማከር አስፈላጊ ነው፡፡

6. **ሽብርተኝነትን በመደገፍ ወደሚታወቁት አገራት ለትምህርትና ለሥራ እንዲሁም ለሃይማኖታዊ ጉዞ በመሄድ በሚመለሱት ወገኖች ላይ ክትትል ማድረግ፡፡** አንዳንዶች በትምህርትና በሥራ ስም በመሄድ የሽብርተኝነት ሥልጠናዎችን ወስደው ይመለሳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ለሃይማኖታዊ ጉዞ በመሄድ ተመልምለው ተልዕኮዎችን ተቀብለው ይመለሳሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ለአሸባሪዎች የመግቢያ በር እንዳይሆኑ ጥብቅ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

7. **የሙስሊም ተቋማትና ግለሰቦች የገንዘብ ምንጭ ምን እንደሆነ መፈተሽ፡፡** ለሽብር ተግባራት ማስፈፀምያና የአክራሪነትን ትምህርቶች ለማስፋፋት ጥቅም ላይ የሚውል ገንዘብ የሚያስተላልፉ ተቋማትና ግለሰቦች በየጊዜው የአሠራር ሥልቶቻቸውን በመቀያየር ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በኢኮኖሚም ቢሆን የተለየ አጀንዳ ያለው ማሕበረሰብ ከሌላው ተነጥሎ የሚያድግ ከሆነ አገር ትጠፋለች፡፡ አንድ እግር ከሌላው ተነጥሎ ብቻውን ቢረዝም መራመድ እንደማይቻል ሁሉ አንዱ ማሕበረሰብም ከሌላው ተነጥሎ ብቻውን የሚያድግ ከሆነ አገር መራመድ አትችልም፡፡ ከውጪ በሚገባ ገንዘብ የሚያድግ ማሕበረሰብ ደግሞ የውጪውን አካል ዓላማ ለማስፈፀም የሚኖር ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ በገንዘብ ፍሰት ላይ ቁጥጥር በማድረግ መንግሥት ኀላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡

8. **የመስጊዶችና የእስላማዊ ተቋማት ግንባታዎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ፡፡** ይህ ነጥብ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ አፅንዖት ሰጥቶ መናገር ያስፈልጋል፡፡ መስጊድ ማለት እንደ ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርአት ብቻ የሚፈፀምበት ተቋም የሚመስላቸው ወገኖች አሉ፡፡ ነገር ግን የመስጊድ አገልግሎት ከአርብ የጸሎት ስርኣት ማስፈፀሚያነት ያለፈ ነው፡፡ የመስጊድን ምንነትና አገልግሎት በተመለከተ አቡ ሱመያ (አሕመድ አሊ) የተሰኙ የአገራችን ሙስሊም ጸሐፊ

በመጽሐፋቸው ውስጥ ያሠፈሩትን እስኪ እንመልከት፡፡ በጥቁር የቀለሙትን ቃላት ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡-

“መስጂድ ከሙስሊሞች ጋር ከመያያዙም በላይ ኢስላምን ለመተግበር ከሚያስፈልጉ ተቋማት አንዱና ዋነኛው መሆኑ ይታወቃል፡፡ መስጂድና ኢስላም፣ መስጂድና ሙስሊም፣ መስጂድና መንግሥት፣ መስጂድና ሌሎችም ... ግንኙነታቸው ጠንካራ፣ አስፈላጊና ግዴታ ነው፡፡ በሙስሊሞች ታሪክ ውስጥ እንደሚታወቀው ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ከመካ ወደ መዲና ለኢስላም ብለው ሲሰደዱ መጀመርያ ያቋቋሙት መስጂድን ነው፡፡ ከዚህ ታላቅ ታሪክ የምንማረው ከሰዎች መኖርያ (መጠለያ) ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ለመስጂድ መሆኑን ነው፡፡

መስጂድ **ፖለቲካ የሚወራበት**፣ ሃይማኖት የሚሰበክበት፣ ማሕበራዊ ጉዳዮች የሚዳሰሱበት፣ ስለ ኢኮኖሚ የሚነገርበት ... ሰርግ የሚደገስበት፣ ችግረኞች የሚረዱበት፣ **የጦር ስልት የሚመከርበት**፣ **ወታደር የሚሰለጥንበት**፣ የተበዳይ ክስ የሚሰማበት፣ ፍርድ የሚሰጥበት ... መንፈሳዊ እርካታና የአእምሮ እርጋታ የሚገኝበት፣ **አካላዊ እንቅስቃሴ** የሚደረግበት፣ መጥፎ የሚወገዝበትና መልካም የሚነገርበት ... ከባለ ፀጋዎችና **ከጦር ምርኮ የሚሰበሰብ ገንዘብና ንብረት የሚቀመጥበት**፣ መሃይም የሚማርበት፣ አዋቂ የሚያስተምርበት፣ ኃብታምና ደኻ፣ ሴትና ወንድ፣ ልጅና አዛውንት፣ ወጣትና ጎልማሳ እኩል የሚስተናገዱበት ... የእውቀት ማምረቻና ማከፋፈያ ተቋም፣ የባሕርይ መለወጫ (ፀባይ ማረምያ) ኮሌጅ፣ ፍትህ መስጫ **ፍርድ ቤት** ... የእርዳታ ማሰባሰብያ፣ **የአገር መከላከያ ማዘዣ**፣ የፈጣሪን ትዕዛዝ ማክበርያ ... ንብረትና ገንዘብ ማስቀመጫ ባንክ፣ የድሆች ማረፍያ፣ ማደርያ፣ መጠለያ .... የሰዎች መገናኛ፣ የሰላምታ መለዋወጫና የውይይት መድረክ፣ የስብሰባ አዳራሽ፣ የአእምሮ ማረፍያና ማረጋግያ፣ የመዝናኛ ስፍራ ... **ቤተ መንግሥት**፣ **ፍርድ**

**ቤት፣** ባንክ ቤት፣ **ምክር ቤት፣ እስር ቤት፣** ገንዘብ **ሚኒስቴር** … ማስረጃ የሚሰጥበት፣ መረጃ የሚገኝበት፣ ዜና የሚነገርበት፣ **ማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ መከላከያ ሚኒስቴር፣ ማሕበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት** … የህፃናት መኮትኮቻ አጸደ ህፃናት፣ የዕውቀት መገበያያ ዩኒቨርሲቲ፣ **መንፈሳዊና አካላዊ ተቋም፣ የፖለቲካ ጽ/ቤት፣** የኢኮኖሚ **ሚኒስቴር፣** የንጽህና ትምህርት መቅሰሚያ ጤና ጣብያ፣ ባሕላዊ ጨዋታ የሚታይበት የባሕል አዳራሽ፣ **የጦር ስልት ትርዒት የሚደረግበት** ስታዲዮም፣ በሽተኛ በተለይም (**በእስላም ትግል ላይ የቆሰለ**) የሚታከምበትና የሚያገግምበት ሆስፒታል … በመሆኑም መስጂድና ኢስላም መስጂድና ሙስሊ የጠበቀ፣ የጠነከረ፣ ለዘለዓለም የማይነጣጠሉና ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ማስተዋል ይገባል፡፡ በአጠቃላይ "ዓሳ ያለውሃ ሙስሊም ያለመስጂድ" መኖር አይችሉም፡፡"[169]

አቡ ሱመያ በዚህ መጽሐፋቸው ውስጥ ጥናቱን ባደረጉበት ዓመት፣ ማለትም በ2004 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙት የመስጊዶች ብዛት 158 መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡[170] አባ ሳሙኤል ደግሞ "በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን?" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ በ2000 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙት የመስጊዶች ብዛት 180 እንደሆነና የአብያተ ክርስቲያናት ብዛት ደግሞ 130 መሆኑን ይገልፃሉ፡፡[171] በተመሳሳይ ኤፍሬም እሸቴ የተሰኙ ጸሐፊ በ1999 በአዲስ አበባ ከተማ 139 መስጊዶችና 114 አብያተ ክርስቲያናት እንደሚገኙ ይገልፃሉ፡፡[172] ከነዚህ ከሦስቱ ጥናቶች እቅጩ ቁጥር የትኛው እንደሆነ ማወቅ ባይቻልም ነገር ግን በነዚህ ዓመታት የአዲስ አበባ መስጊዶች ብዛት ከ160 እስከ 180 መካከል እንደሚሆን ግምት መያዝ

---

169 አቡ ሱመያ፣ የመስጂዶች ታሪክ በአዲስ አበባ፣ ከምኒልክ እስከ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.፣ 2004፣ ገፅ 17-19
170 ዝኒ ከማሁ ገፅ 43
171 አባ ሳሙኤል፣ በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን? ፣ 2000፣ ገፅ 47
172 ኤፍሬም እሸቴ፣ አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ፣2000፣ ገፅ 180

ይቻላል፡፡ በመላ አገሪቱ በየመንገዱ ዳር፣ በአብያተ ክርስቲያናት፣ በትምህርት ቤቶችና በመንግሥት ተቋማት አጠገብ የተገነቡትን የመስጊዶች ብዛት ስንመለከት ደግሞ እውነት ሙስሊሙ ማሕበረሰብ ይህን ያህል ብዛት ያለው መስጊድ አስፈልጎት ነው ወይንስ ሌላ ሤራ አለ? ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን፡፡ ከነዚህ መስጊዶች መካከል ብዙዎቹ የተገነቡት ከሳዑዲ በመጣ ገንዘብ መሆኑ አያስገርምም፡፡[173]

እንግዲህ መሪዎቻችን የመስጊድ ግንባታዎችን በፈቀዳችሁ ቁጥር ሕገ ወጥ የሆኑ የፖለቲካ ውይይት አዳራሾችን፣ የጦር ስልት መመካከርያ ቦታዎችን፣ ወታደራዊ ማዘዣዎችን፣ የጦር መሳርያ ማከማቻዎችንና የፖለቲካ ጽ/ቤቶችን እያበዛችሁ እንደሆነ እወቁ፡፡[174] መስጊዶችን በዚህ መልኩ መጠቀም ለክፍለ ዘመናት የኖረ በእስላማዊ ነገረ መለኮት ውስጥ ጠልቆ የተመሠረተ መርህ እንጂ ዛሬ የተጀመረ አይደለም፡፡ እነዚህ በሃይማኖት ካባ ተሸፍነው የሚሠሩ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ማዕከላት የሚፈጥሩትን አደጋ የመቀነሻ መንገዱ ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ የተገነቡትንና ካርታ የሌላቸውን መዝጋት፣ አዳዲስ ለሚገነቡት ፍቃድ ሲሰጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ግንባታዎች ሲፈፀሙ ሚስጥራዊና የመሬት ውስጥ ክፍሎች አለመሠራታቸውን ማረጋገጥ፣ ከአምልኮ ሥርኣትና በሕግ ከተፈቀዱት እንቅስቃሴዎች ውጪ ሌላ እንቅስቃሴ አለመኖሩን ለማረጋገጥ በየጊዜው በደህንነት ኃይሎች ክትትልና ፍተሻዎችን ማድረግ፣ ወዘተ. ያስፈልጋል፡፡ አገር አጥፊና የሽብር ሁሉ ምንጭ የሆነው የወሃቢዝም ትምህርት የሚሰጡባቸውንና በፍልስፍናው ተከታዮች ቁጥጥር ስር የሚገኙትን መዝጋት ጊዜ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡

173 Haggai Erlich. *Ethiopia and Saudi Arabia;* 2007, p. 4

174 የመስጊድን አደገኛነት ለመረዳት Belteshazar & Abdnego በተሰኙ ምሑራን The Mosque and its Role in the Society በሚል ርዕስ የተጻፈውን መጽሐፍ ታነቡ ዘንድ እንጠቁማለን፡፡

*ተከታዮቹ ነጥቦች "አይኤስ እስላማዊ ነውን?" በሚል ርዕስ ከጻፍኩት ቡክሌት መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎላቸው የተወሰዱ ናቸው፡፡*[175]

# ከክርስቲያኖች ምን ይጠበቃል?

1. **<u>ሙስሊሞችን መውደድ</u> ፡-** የክርስቶስ መንገድ የፍቅር መንገድ ነው፡፡ እኛ ውጊያችን ከደምና ከሥጋ ጋር ስላልሆነ አክራሪ እስልምናን እንጂ ሙስሊሞችን ልንቃወም አይገባንም፡፡ ለሰይፍ መልስ ሰይፍ የምንመዝ ከሆነ ውድቀታችንን እናፈጥናለን፡፡ ምንም ያህል ኢ-ምክንያታዊ ቢመስልም ለሰይፍ በሰይፍ ምላሽ መስጠት ክርስቲያናዊ መርህ አይደለም፡፡ ክርስቲያናዊ መርህ ፍቅርና ይቅርታ ነው፡፡

   *"ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። "*
   *የሐንስ 3፡16*

   *"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም። ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም።"*

   *ማርቆስ 12፡29-31*

   *"እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፥ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና።"*

   *ሮሜ 13፡8*

[175] ኑረዲን ኢብን አል-መሲህ፡፡ *አይኤስ እስላማዊ ነውን?*፣ አንደኛ ዕትም፣ 2008፣ ገፅ 32-37፡፡

*"በሕዝብህ መካከል በሸንጋይነት አትዙር በባልንጀራህም ደም ላይ አትቁም እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ወንድምህን በልብህ አትጥላው በባልንጀራህ ምክንያት ኃጢአት እንዳይሆንብህ ገሥጸው። አትበቀልም፥ በሕዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ፥ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።"*

*ሌዋ. 19፡16-18*

*"ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፥ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ።"*

*ሉቃስ 6፡26-27*

*"ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፤ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ። ለሚለምንህ ስጥ፥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል። ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ*

*እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።"*

*ማቴ 5፡38-48*

በርግጥ አክራሪ እስልምና የክርስቲያኖችን የፍቅርና የትህትና ምላሽ እንደ ውርደትና እንደሽንፈት ነው የሚቆጥረው፡፡ ቢሆንም ግን ከዚህ የክርስቶስ መርህ መውጣት አልተፈቀደልንም፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት ቢሊዮን በላይ ተከታዮችን ያፈራውና የሮምን ኢምፓየር ከእግሩ በታች ያንበረከከው ሽንፈት በሚመስል የፍቅር ምላሽ ነበር፡፡ የምንጎዳ መስሎ ቢሰማንም እንኳ ይህንን የክርስቶስን መርህ መከተል ግድ ይለናል፡፡ ሙስሊሞችን እንውደዳቸው፣ እንዘንላቸው፣ ደግ እንዋልላቸው፣ መልካም ጎረቤቶች እንሁናቸው፣ እውነትን በፍቅር እንንገራቸው፡፡ ፍቅር ተሸናፊ ቢመስልም ምን ጊዜም አሸናፊ ነውና፡፡

2. <u>**እውነትን መናገር**</u> **፡-** ክርስቲያኖች የፍቅር ሰዎች መሆን እንደሚገባቸው ሁሉ ለእውነት የሚቆሙ ሰዎችም መሆን ይገባቸዋል፡፡ እስልምናን በተመለከተ "እስላም ሰላም ነው"፣ "ቁርአን የሰላም መጽሐፍ ነው"፣ "ሽብርተኝነት ከእስልምና ጋር ምንም ግንኙነት የለውም"፣ "እስልምና በሰይፍ አልተስፋፋም"፣ "ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች አንድ ዓይነት አምላክ ነው የሚያመልኩት"፣ "የግራኝ መሐመድ ጦርነት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንጂ ሃይማኖታዊ አልነበረም"፣ ወዘተ. የሚሉትን የውሸትና የሽንገላ ንግግሮች መቀበል የለብንም፡፡ ፍቅር ማለት እውነትን ማለባበስ ማለት አይደለምና፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የፍቅር አንዱ መገለጫ እውነትን መናገር ነው

(1ቆሮ 13፡6)፡፡ ውሸትና ሸንገላ የፍቅር መገለጫ ሊሆን አይችልም፡፡ በጥበብ በመመላለስና እንደ ጠቢባን በመናገር ለእውነት ዘብ ልንቆም ይገባናል፡፡

3. **<u>ፍርሃትን አውጥቶ መጣል</u> ፡-** ሙስሊም ሽብርተኞች አሳቃቂ ቪድዮዎችን እየቀረፁ የሚለቁበት ዋናው ምክንያት ፍርሃትና ሽብርን ለመንዛት ነው፡፡ ከፈራንላቸው ዓላማቸው ግቡን መቷል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አለመፍራታችንን በተግባር በማሳየት ዓላማቸው መክሸፉን ልናሳውቃቸው ይገባል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ነገሮች መጪውን አደጋ ከመከላከል አንፃር የችግሩን መንስኤና ታሪካዊ ሂደቱን በማወቅ መፍትሄ ለማፈላለግ እንጂ እንድንፈራና ሙስሊም ጎረቤቶቻችንን በጥርጣሬ እንድንመለከት አይደለም፡፡

   *"ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።"*

   *1ዮሐ 4፡18*

4. **<u>መጸለይ</u> ፡-** ጸሎት በቃላት የማይነገር ኃይል ያለው ትልቅ የክርስቲያን መሣርያ ነው፡፡ አክራሪ እስልምና የሰው ፍልስፍና ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ከበስተጀርባው ሆኖ የሚሠራበት አስተሳሰብ ነው፡፡ ክርስቲያኖች በጸሎት የምንተጋ ከሆነ ከበስተጀርባው የሚሠራውን ክፉ መንፈስ በማሰር አቅም ልናሳጣው እንችላለን፡፡ (ኤፌሶን 6፡10-18)

5. **<u>ወንጌልን ለሙስሊሞች</u> ማብሰር ፡-** የአክራሪ እስልምናን ንፅረተ ዓለም ማንኮታኮት የሚችለው ብቸኛ ንፅረተ ዓለም በእውነተኛው የክርስቶስ ወንጌል ላይ የተመሠረተው ክርስትና ነው፡፡ ሙስሊም አገራትንም ከምዕራባውያን የጦር መሣርያዎች ይልቅ ብርክ የሚያሲዛቸው የክርስቶስ ወንጌል ነው፡፡ ወንጌል የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ኃይል ደግሞ መቋቋም የሚችል ምንም ዓይነት ኃይል የለም፡፡ አክራሪ እስልምና

አቅም የሚያገኘው እኛ ወንጌልን ከመስበክ ወደ ኋላ ስንል ነው፡፡ ሽብርተኝነትንም የሚጠቀመው ወንጌልን የመቋቋም አቅም ስለሌለው ነው፡፡ የወንጌሉን ብርሃን ይዘን ወደ ጨለማው ዓለም በመሄድ የታሰሩትን ነፃ ማውጣት የኔና የናንተ ድርሻ ነው፡፡ አምላካችን ደግሞ ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ተስፋን ሰጥቶናል፡፡

*“ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። “*

*ማቴ 27፡18-20*

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስባታሊ ጉዳዮቻችን ከወንጌል ጋር ያልተያያዙ ሥጋዊ ጉዳዮች መሆናቸው በእጅጉ የሚያሳዝን ነው፡፡ በጎጠኝነትና በምድራዊነት እግረሙቅ ስለታሰርን የጨለማው ግዛት እየሰፋ እኛ ግን መብራቱን ይዘን መሄድ ተስኖናል፡፡ የረሳነውን ተልዕኳችንን እናስታውስ፤ በአጭር ታጥቀን የጌታችንን ትዕዛዝ ለመፈፀም እንነሳ፤ ትውልዱን እንታደግ፡፡

6. <u>**አቃቤ እምነታዊ አገልግሎትን ማበረታታት**</u> ፡- እስልምና በክርስትና ላይ ትችቶችን ያለማቋረጥ ይሰነዝራል፡፡ ቁርአን የክርስትናን አስተምህሮዎች በሚያንቋሽሹ ትምህርቶች የተሞላ ነው፡፡ ሙስሊሞችም ደግሞ በየጊዜው መጽሐፍ ቅዱስንና የክርስትናን መሠረታዊ ትምህርቶች የሚያብጠለጥሉ ጽሑፎችንና ቪዲዮዎችን እያሳተሙ ያሰራጫሉ፡፡ ለእነዚህ ትችቶችና ጥያቄዎች የማያዳግም ምላሽ ለመስጠት መትጋትና ሕዝባችንንም በዚህ ማስታጠቅ ያስፈልገናል፡፡ በአቃቤ እምነት አገልግሎት ላይ የተሰማሩትንም

ወገኖች አስፈላጊ በሆነው በማንኛውም መንገድ በመደገፍ ማበረታታት ያስፈልገናል፡፡

*"ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።"*

*1ጴጥ. 3፡15*

*"በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር  አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥ መታዘዛችሁም በተፈጸመች ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ልንበቀል ተዘጋጅተናል።"*

*1ቆሮ 10፡4-6*

*"በልቤ ስላላችሁ እንዲህ ማሰቤ ተገቢ ነው፡፡ በእስራቴም ሆነ ወንጌልን ስመክት እና ሳጸናው ሁላችሁም ከእኔ ጋር የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ናችሁና፡፡" (አ.መ.ት.)*

*ፊልጵ. 1፡7*

*"ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።"*

*ይሁዳ 3*

7. **<u>ክርስቲያኑን ማህበረሰብ በኢኮኖሚ ለማጠናከር መሥራት</u>** ፡- ኢኮኖሚ የአንድን ማሕበረሰብ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ አቅም ይለካል፡፡ ለክርስቲያኖች

የሥራ ዕድሎችን መፍጠር፣ ከክርስቲያን ነጋዴዎች ላይ መግዛት፣ ተደራጅቶ አንድ ላይ መሥራት፣ መረዳዳት፣ ወዘተ. ያስፈልገናል፡፡ (ሮሜ 12:13)

8. <u>**ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻችንን በትክክል ማወቅና መጠቀም**</u> **፡-** ሕገ መንግሥታችን የሰጠንን መብቶች አሟጠን በመጠቀም መብቶቻችንን በማስከበር ከእስላማዊ ጭቆና ራሳችንን ነፃ ማድረግ ያስፈልገናል፡፡ ከሕገ መንግሥቱ ውጪ እስልምናን ለመጥቀም የሚፈፀሙ በደሎች ካሉ አስፈላጊውን የሕግ አካሄድ ሁሉ በመጠቀም መብቶቻችንን ማስከበር ያስፈልገናል፡፡ በዞንና በክልል ደረጃ የሚፈፀሙ ፍትህን የማጉደል ተግባራትን ትክክለኛውን አካሄድ በመጠቀም እስከ አገሪቱ ዋና መሪዎች ድረስ የመውሰድ ፅናት ሊኖረን ይገባል፡፡

*“በነጋም ጊዜ ገዢዎቹ። እነዚያን ሰዎች ፍታቸው ብለው ሎሌዎቻቸውን ላኩ። የወኅኒውም ጠባቂ ትፈቱ ዘንድ ገዢዎቹ ልከዋል፤ እንግዲህ አሁን ወጥታችሁ በሰላም ሂዱ ብሎ ይህን ቃል ለጳውሎስ ነገረው። ጳውሎስ ግን፡- እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወኅኒ ጣሉን፤ አሁንም በስውር ይጥሉናልን? አይሆንም ራሳቸው ግን መጥተው ያውጡን አላቸው። ሎሌዎቹም ይህን ነገር ለገዢዎች ነገሩ። የሮሜ ሰዎችም እንደ ሆኑ በሰሙ ጊዜ ፈሩ፤ መጥተውም ማለዱአቸው፥ አውጥተውም ከከተማ ይወጡ ዘንድ ለመኑአቸው።”*

*ሐዋ 16፡35-39*

*“ፊስጦስ ግን አይሁድን ደስ ያሰኝ ዘንድ ወዶ ጳውሎስን፡- ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተህ ስለዚህ ነገር ከዚያው በፊቴ ትፋረድ ዘንድ ትወዳለህን? ብሎ መለሰለት። ጳውሎስ ግን፡- እፋረድበት ዘንድ በሚገባኝ በቄሳር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ። አንተው ደግሞ ፈጽመህ እንደምታውቅ አይሁድን ምንም አልበደልሁም። እንግዲህ በድዬ ወይም*

*ሞት የሚገባውን ነገር አድርጌ እንደ ሆነ ከሞት ልዳን አልልም፤ እነዚህ የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደሆነ ግን ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠኝ ዘንድ ማንም አይችልም፤ ወደ ቄሳር ይግባኝ ብዬአለሁ አለ። በዚያን ጊዜ ፊስጦስ ከአማካሪዎቹ ጋር ተማክሮ። ወደ ቄሳር ይግባኝ ብለሃል፤ ወደ ቄሳር ትሄዳለህ ብሎ መለሰለት።"*

*ሐዋ 24፡9-12*

9. **<u>ክርስቲያኖች አንድ መሆን</u>** ፡- እስልምና የክርስትና ቤተ እምነቶችን ነጣጥሎ የመምታት አካሄድ አለው፡፡ ለምሳሌ ያህል በጅማ ዞን የተፈፀሙትን የሽብር ጥቃቶች ስንመለከት መጀመርያ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮችን ነጥሎ የማጥቃት ሁኔታ ነበር፤ ከዝያ በኋላ ደግሞ ሰበብ ፈልጎ ፕሮቴስታንቶችን ብቻ የማጥቃት ዘመቻ ተደርጎ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ለእንዲህ ዓይነት መሰሪ እስላማዊ አካሄዶች መመቸት የለባቸውም፡፡ የክርስቶስን መስቀል ምልክቱ ያደረገ የትኛውም ማሕበረሰብ ሲጠቃ በአንድነት መቆም ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት የጋራ አንድነትን በመፍጠር እስላማዊውን ተግዳሮት መጋፈጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ዘመኑ ልዩነቶቻችንን የምናጎላበት ዘመን ሳይሆን ሜዳውን ለማዳን የምንረባረብበት ዘመን ነው፡፡ ይህንን በማድረግ ረገድ ከመሪዎቻችን ትልቅ ሥራ ይጠበቃል፡፡

10. **<u>ጥቃት ሲፈፀም ድምፃችንን በጋራ ማሰማት</u>** ፡- እስላማዊ የሽብር ጥቃቶችና በደሎች ተድበስብሰው መቅረት የለባቸውም፡፡ ሙስሊሞች ችግር ከፈጠሩ በኋላ ነገሩ ተድበስብሶ እንዲቀር ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን አስፈላጊው የፍትህ እርምጃ እስካልተወሰደ ድረስ ተመሳሳይ ችግር መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ብዙ ጊዜ ሙስሊም ሽብርተኞች የሆነ በደል ይፈፅሙና ይፈትሹናል፡፡ ምላሻችን የቸልታና የተቀዛቀዘ ከሆነ የባሰ ጥቃት ይፈፅማሉ፡፡ ክርስቲያናዊ

ፍቅርና ይቅርታ ማለት ወንጀለኞች እንደ በግ ሊያርዱን ሲወስዱን ዝም ብሎ መነዳት ማለት አይደለም፡፡ “ቀኝህን ለሚመታህ ግራህን ስጠው” የሚለውም ቃሉን አንብበው ሊመቱን የሚመጡ ሰዎች እንዲያላግጡብን የተጻፈ አይደለም፡፡ ሚዛናዊ መሆን ያፈልገናል፡፡

11. **<u>ሕጋዊ አካሄዶችን ብቻ መከተል</u>** ፡- በፅንፈኛ ሙስሊሞች ለሚፈፀሙ በደሎች ክርስቲያኖች ምላሽ መስጠት ያለባቸው ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንጂ ፍትህን በራሳቸው እጅ ለመፈፀም በመሞከር በሕገወጥ አካሄድ መሆን የለበትም፡፡ እንደዚያ ዓይነቱ አካሄድ ለአገር ሰላም አይበጅም፡፡ ክርስትናንም ያስነቅፋል፡፡ ነገር ግን ሰይፍን እንዲታጠቅ እግዚአብሔር የሾመው አካል አለ፡፡ ይህም አካል መንግሥት ነው፡፡ በመንግሥት ለሚወሰድ የፍትህ እርምጃ እግዚአብሔር እውቅናን ይሰጣል፡፡ በደለኞችን ለመቅጣት የእግዚአብሔር መሳርያ እንደሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡

*“ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፥ ከሁሉ በላይ ነውና፤ ለመኳንንትም ቢሆን፥ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ።”*

*1ጴጥ 2፡13-14*

ስለዚህ በደል ሲፈፀም እግዚአብሔር በደለኞችን እንዲቀጣ ለሾመው አካል ለመንግሥት ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

12. **<u>ህፃናትና ወጣቶች ላይ ትኩረት በማድረግ መሥራት</u>** ፡- ልጆቻችንን በሚገባ በእግዚአብሔር ቃልና በዕውቀት ኮትኩተን ካላሳደግን እንዲሁም ወጣቶቻችንን በሚገባ ካላስተማርን አገሪቱን ለሌላ ለማስረከብ እየተዘጋጀን ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለህፃናትና ለወጣቶች ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት መሥራት ይጠበቅባታል፡፡

*“ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።”*

*ምሳሌ 22፡6*

13. **<u>የአገሪቱን የክርስትና ታሪክ ማጉላት</u>** ፡- በአሁኑ ወቅት የክርስትና እሴቶች በጣም በረቀቀ ሁኔታ ከአገሪቱ አደባባዮች እየተወገዱ ይገኛሉ፡፡ ክርስትናን የሚገልፁ ምልክቶች እየተለወጡ ይገኛሉ፡፡ ከመማርያ መጻሕፍትም ውስጥ የክርስትና እሴቶችና ታሪኮች ቀስ በቀስ በመውጣት በእስላማዊ እሴቶችና ታሪኮች የመተካት ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ክርስቲያኖች ይህንን አካሄድ ለማስቆም መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

14. **<u>ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ ከመንግሥት ጋር በመተባበር መሥራት</u>** ፡- መረጃዎችን በማቀበልና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ከመንግሥት ጎን መቆም አስፈላጊ ነው፡፡ የፖለቲካ አሰላለፋችን በየትኛውም ጎራ ይሁን ነገር ግን በዚህ ረገድ ከመንግሥት ጋር መተባበር ይኖርብናል፡፡ ከሽብርተኝነት ጋር የሚደረጉ ትግሎችን ፖለቲካዊ ማድረግ በእጅጉ የተሳሳተ አካሄድ ነው፡፡

15. **<u>ክርስቲያኖች በፖለቲካው መስክ እንዲሳተፉ ማበረታታት</u>** ፡- በአሁኑ ወቅት ሙስሊም ወገኖች ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ትልቅ ሩጫ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ዜጎች እንደመሆናቸው መጠን መሳተፍ መብታቸው ቢሆንም ነገር ግን በፖለቲካው ውስጥ ከቁጥራቸው ጋር የማይመጣጠን ድርሻ መያዝ አይገባቸውም፡፡ አክራሪ ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ የክርስቲያኖችን መዘናጋት በመጠቀም የሥልጣን ወንበሮችን የመያዝ አካሄድ አላቸው፡፡ ክርስቲያኖች በሁሉም ረገድ በፖለቲካ ውስጥ በንቃት በመሳተፍ ክፍተቶችን ሁሉ መድፈን ይኖርባቸዋል፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**

# አባሪ - 1

## በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ የደረሱ ጥቃቶች የቅርብ ዘመን ትዝታዎች

- ጥቅምት 6/ 1997 ዓ.ም. አርሲ ቆሬ ውስጥ አክራሪ ሙስሊሞች በፈፀሙት ጥቃት 10 ክርስቲያኖች ተገድለዋል፣ 3 ቆስለዋል፣ 2237 ተፈናቅለዋል፣ 1 ቤተ ክርስቲያንና 194 የክርስቲያን ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተቃጥለዋል፣ 24 የክርስቲያን ቤቶች በከፊል ተቃጥለዋል፣ 304 ከብቶች ተዘርፈዋል፡፡
- መስከረም 16/ 1999 ዓ.ም. በጅማ ዞን በሻሻ በተባለ ቦታ 18 ክርስቲያኖች ተገድለዋል፣ 38 ቆስለዋል፣ 488 በግድ ሰልመዋል፣ ከ2000 በላይ ተፈናቅለዋል፣ 3 አብያተ ክርስቲያናትና ከ850 በላይ የክርስቲያን ቤቶች ተቃጥለዋል፣ 4 አብያተ ክርስቲያናት ተዘርፈዋል፡፡

  *(ከላይ የተቀመጡት መረጃዎች የተወሰዱት "በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን" በሚል ርዕስ በአባ ሳሙኤል ከተዘጋጀው መጽሐፍ ገፅ 28-31 እና "አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በኤፍሬም እሸቴ ከተዘጋጀው መጽሐፍ ገፅ 172-175 ነው፡፡ ዓመታቱ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ናቸው፡፡)*

ተከታዮቹ መረጃዎች በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሱትን እስላማዊ ጥቃቶች በመዘገብ ከሚታወቅ ድረ-ገፅ ላይ የተወሰዱ ሲሆን ዓመታቱ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው፡፡[176]

- ህዳር 8/ 2011 ዓ.ም. በጅማ ዞን አሰንዳቦ በተባለ ቦታ በቁጣ የተሞሉ ሙስሊሞች አብያተ ክርስቲያናትን የማቃጠል ዘመቻ አድርገዋል፣ 2 ክርስቲያኖችንም ገድለዋል፡፡

[176] http://www.thereligionofpeace.com/pages/christianattacks.htm

- ህዳር 1/ 2011 ዓ.ም. በባሌ ዞን ሆማ በተባለ ቀበሌ ለስብከተ ወንጌል በወጡ የመደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ላይ በተፈፀመ ጥቃት 17 ተጎድተዋል፡፡
- ግንቦት 13/ 2010 አፋር ዱብቲ ላይ አንድ ወጣት ልጅ ከእስልምና ወጥቷል በሚል በስለት ተወግቶ ቆስሏል፡፡
- ሚያዝያ 21/ 2010 በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በቁጣ የተሞሉ ሙስሊሞች አንድ ክርስቲያን መሪ በበትር ደብድበዋል፡፡
- መጋቢት 16/ 2010 በአዲስ አበባ ከተማ በቁጣ የተሞሉ ሙስሊሞች ከእስልምና ወጥቷል በሚል አንድ ክርስቲያን ላይ ከባድ ድብደባ ፈፅመዋል፡፡
- ግንቦት 11/ 2009 ሸዋ ሰንበቴ ላይ በቁጣ የተሞሉ ሙስሊሞች ወደ ቤተ ክርስቲያን በመግባት በጸሎት ላይ በነበሩት ክርስቲያኖች ላይ ጥቃት በመፈፀም 3 አቁስለዋል፡፡
- መጋቢት 20/ 2008 በደሴ ከተማ በሚገኝ አንድ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በሥራ ላይ የነበሩ 2 ክርስቲያኖች ድንገት ተኩስ ተከፍቶባቸው ተገድለዋል፡፡
- ግንቦት 20/ 2008 በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድ ክርስቲያን መሪ ለሞት እስኪቀርብ ድረስ በሙስሊሞች ድብደባ ተፈፅሞበታል፡፡
- መጋቢት 19/ 2008 በጅግጅጋ ከተማ ውስጥ እስልምናን ትታችኋል በሚል 2 ክርስቲያኖች በድንጋይ ተወግረው ለከባድ ጉዳት ተዳርገዋል፡፡
- ታህሳስ 30/ 2007 እዚያው ጅግጅጋ ከተማ ውስጥ ሙስሊሞች በድንኳን ውስጥ ተሰብስበው በተቀመጡ ክርስቲያኖች ላይ ቦምብ በመጣል 2 ገድለው 3 አቁስለዋል፡፡
- መስከረም 5/ 2007 አርሲ ኮፈሌ ላይ በቁጣ የተሞሉ ሙስሊሞች አንድ ክርስቲያን በብረት ቀጥቅጠው ገድለዋል፡፡
- ሰኔ 1/ 2006 ጅማ ዞን ውስጥ ሙስሊሞች በፈፀሙት ጥቃት 10 ክርስቲያኖች ተገድለዋል፣ 12 ቆስለዋል፣ 2 አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፡፡
- ታህሳስ 16/ 2006 በጅግጅጋ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ሁለት ምግብ ቤቶችና አንድ ቤተ ክርስቲያን ላይ በሙስሊሞች በተፈፀመ የቦምብ ጥቃት 3 ክርስቲያኖች ሲገደሉ 23 ቆስለዋል፡፡

- ህዳር 22/ 2006 አርሲ ነጌሌ ውስጥ ሙስሊሞች በአንድ የፕሮቴስታን ቤተ ክርስቲያን በር ፊትለፊት ከእስልም ወጥተሃል በሚል አንድ ክርስቲያን በጥይት ገድለዋል፡፡ ሟች የ 7 ልጆች አባት ነበሩ፡፡
- መጋቢት 19/ 2005 የታጠቁ ሙስሊሞች ወደ ጅግጅጋ ሲጓዝ የነበረ አውቶብስ በማስቆም በውስጥ የነበሩትን ክርስቲያኖች ሸሃዳ አስብለዋል፤ ወደ መካም በመዞር እንዲሰግዱ አስገድደዋል፡፡ ይህንን ለማድረግ ፍቃደኛ ያልሆነ አንድ ወጣት ተገድሏል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ጥቃቶች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ሲሆኑ ፍትህን በማዛባት፣ አድማ በማድረግ፣ የክርስቲያን ልጆችን አፍኖ በመውሰድ፣ አስገድዶ በመድፈር፣ አስፈራርቶ አካባቢን በማስለቀቅ፣ የክርስቲያን ይዞታዎችን በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመንጠቅ፣ ወዘተ. የተፈፀሙ የግፍ ሥራዎችን ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት


- Abu Bakr `Abdullah b. abi Da'ud. *Kitab al Masahif;* ed. Arthur Jeffery; Cairo: *1936/1355.*
- Abir, Mordechai. *Ethiopia and the Red Sea: the Rise and Decline of the Solomonic Dynasty and Muslim-European Rivalry in the Region;* Institute of Asian and African Studies, Hebrew University of Jerusalem: 1980
- Akhtar, Shabbir. *Be Cafeful With Muhammad;* London, Bellow: 1992.
- Al-Tabari. *The History of al-Tabari (Ta'rikh al-rasul wa'l-muluk);* Vol. VI: *Muhammad at Mecca:* Translated by W. M. Watt and M.V. McDonald: ____.
- Belteshazzar & Abednego. *The Mosque and Its Role in the Society;* Pilcrow Press: 2006.
- Campo, E. Juan. *Encyclopedia of Islam;* Oxford University Press: 2009.
- Clinton, Bennet. *In Search of Muhammad;* Cassel, London & Newyork: 1998.
- Crone, Patricia. *Meccan Trade and the Rise of Islam;* Princeton University Press: 1987.
- Despalta, Patrick & Terje Østebø. *Muslim Ethiopia: The Christian Legacy, Identity Politics and Islamic Reformism;* Palgrave Macmillan: 2013.
- Dr. Muhammad Taqi-ud-Din al-Hilali and Dr. Muhammad Muhsin Khan. *Interpretation of the Meanings of the Noble Qur'an in the English Language*; Darussalam Publishers and Distributors; Riyadh: 1996.

- Durie, Mark. *The Third Choice, Islam, Dhimmitude and Freedom;* Deror Books: 2010.
- Encyclopedia Britannica; Online Edition: 2016 www.britannica.com
- Erlich, Haggai. *Saudi Arabia & Ethiopia; Islam, Christianity & politics Entwined:* Lynne Rienner Publishers: 2007.
- Fregosi, Paul. *Jihad in the West: Muslim Conquest from 7th to 21st Centuries;* Prometheus Books: 1998.
- Gabriel, Mark A. *Islam and Terrorism: What the Qur'an Really Teaches about Christianity, Violence and the Goals of the Islamic Jihad;* Charisma House Publishers: 2002.
- Gorka, Sebastian. *Defeating Jihad: the Winnable War;* Reginery Publishing: 2015.
- Guillaume, Alfred. *The Life of Muhammad: A Translation of Ishaq's Sirat Rasul Allah;* Oxford University Press: 1955.
- *Holy Qur'an*, *Abdullah Yusuf Ali's translation:* 1975.
- Musnad Ahmad Ibn Hanbal: http://www.kalamullah.com/musnad-ahmad.html
- Ibn Abi Dawud al-Sijistani. *Sunan Abu Dawud:* http://www.sunnah.com/abudawud
- Ibn Abi Dawud al-Sijistani. *Kitab al-Musahif:* (Translated into English by S. Moinul Haqq), Vol. 2: 1972.
- Ibn Sa'd. *Kitab al-Tabaqat al-Khabir:* (Translated into English by S. Moinul Haqq) Vol. 2: 1972.
- Islamic Encyclopedia; Online Edition: 2016 www.islamicencyclopedia.org
- Jalaluddin al-Khudairi as-Shafi'i as-Suyuti. *Al-Itqan fii Ulum al-Qur'an;* Biblio Vergal, Osunabrueck, Germany, (Calcutta Edition): 2 Volumes: 1980.

- ______. *Kitab al-Maghazi:* Translated by Faizer R., Ismail A., & Tayob, A. K.: 2011.
- Maududi, Sayid abul A'La. *The meaning of the Qur'an:* Vol. 5: http://www.tafheem.net/tafheem/surah65.html
- New World Encyclopedia; Online Edition: 2016 www.newworldencyclopedia.org
- Qutb, Sayyid. *Ma'alim fi'l-tareeq (Mile Stone);* Edited by A.B. al-Mehri: 2006.
- *Sahih Albukhari:* Translated by Dr. Muhammad Mushin Khan, Vol. 1-9: 1997.
- *Sahih Muslim:* Translated by Nasruddin al-Khattab, 2007.
- Setian, Shahkeh Yaylaian. *Humanity in the Midst of Inhumanity;* Xlibris publishers: 2011.
- Shaikh, Anwar. *Islam and Terrorism;* The Principality Publishers: 2004.
- Small, Keith. *Holy Books Have History: Textual History of the New Testament and the Qur'an;* Avant Ministries: 2010.
- Solomon, Sam & E. Almaqdisi: *Al Hijra, Islamic Doctrine of Migration: Accepting Freedom or Imposing Islam:* 2007.
- Speer, Albert. *Inside the Third Reich;* ____: 1970.
- Steyn, Mark. *America Alone: the End of the World as We know it;* Regnery Publishing, inc.: 2006.
- Tafsir of Ibn Kathir http://www.qtafsir.com
- *The Cambridge History of Islam:* Vol. 1a: 2008.
- The New York Times: http://www.nytimes.com
- Jalal Abualrub. *The Prophet of Mercy – Muhammad's Role in Islam*; edited by Alaa Mencke; Madinah Publishers and Distributors, First Edition: 2007.
- Trimingham, J. Spencer. *Islam in Ethiopia;* Oxford University Press: 1952.

- Uhlig, Siegbert, et al. *Encyclopedia Aethiopica, A-C;* Harrassowitz: 2003.
- *United States Joint Publications Research Service, Translations on Sub-Saharan Africa:* Issue 1767-1775.
- Walker, J. Christopher*. Armenia: the Survival of Nation;* London, Croom Helm: 1980.
- Ye'or, Bat. *Islam and Dhimmitude: Where Civilization Collide*; Translated from French by Miriam Kochan and David Littman; Fairleigh Dickinson University Press: 2002.
- Ye'or, Bat. *The decline of Eastern Christianity under Islam: from Jihad to Dhimmitude;* Fairleigh Dickinson University Press: 1996.
- Zakaria, Rafiq. *Muhammad and the Quran;* Harmondsworth, Penguin: 1991.
- ሐሰን ታጁ፡፡ *ሰይፉን ፍለጋ፤ ከመካ እስከ ቫቲካን፤* አንደኛ ዕትም፣ 2006፡፡
- ሐሰን ታጁ፡፡ *የሐመረ ተዋሕዶን ቅጥፈት በእስልምና እውነት፤* አልበያን ሊሚትድ፣ አንደኛ ዕትም፣ 2002፡፡
- *መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣* ኢንተርናሽናል ባይብል ሶሳይቲ፣ 1993፡፡
- *መጽሐፍ ቅዱስ፣* የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፣ 1954፡፡
- ሙሐመድ ጦይብ፡፡ *ኢትዮጵያ እና ኢስላም፤* በኢድሪስ ሙሐመድ ወደ አማርኛ የተመለሰ፣1999፡፡
- ሚጉኤል ዴ - ካስታንኳዞ፡፡ *የፖርቱጋሎች ጀግንነት፣* በዶ/ር ሙራድ ከሚልና በዮናስ ቦጋለ ወደ አማርኛ የተመለሰ፣ 1952፡፡
- ሳም ሰለሞንና ኢ. አልመቅዲሲ፡፡ *አል-ሂጅራ፣ እስላማዊ የስደት አስተምህሮ፤ ነፃነትን መቀበል ወይንስ እስልምናን በኃይል መጫን?*፣ በኑረዲን ኢብን አል-መሲህ ወደ አማርኛ የተመለሰ፣ 2008፡፡
- *ቅዱስ ቁርአን፣ የአማርኛ ትርጉም፤* ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ ሁለተኛ ዕትም፣ 1997፡፡

- አሕመዲን ጀበል፡፡ *ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከ615-1700 የጭቆናና የትግል ታሪክ፤* ቅፅ 1፣ 2003፡፡
- አቡ ሱመያ፡፡ *የመስጂዶች ታሪክ በአዲስ አበባ፣* ከምኒልክ እስከ ኢሕአዴግ፤ 2004፡፡
- አባ ሳሙኤል፡፡ *በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን?፤* 2000፡፡
- ኢማም አን-ነወዊ፡፡ *ሪያዱ ሷሊሒን፣* ከሐዲስ ቁጥር 811-1896፣ ቅፅ 2፣ ትርጉም በሐሰን ታጁ _____፡፡
- ኤፍሬም እሸቴ፡፡ *አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ፤* 2000፡፡
- ኑረዲን ኢብን አል-መሲህ፡፡ *ኢይኤስ እስላማዊ ነውን?፣* አንደኛ ዕትም፣ 2008፡፡
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት፣ *አሕመድ አል-ነጋሺ የሚባል ንጉሥ በኢትዮጵያ አልነበረም፣* ክፍል 1 እና ክፍል 2፤ 2000፡፡
- ይልማ ዴሬሳ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፤* 1959፡፡